# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 083 ኅዳር 23 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# “አዋጁ በብቃትና በውድድር ላይ የተመሠረተ፤ ነጻና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ይፈጥራል”

- ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር)

የተወካዮች ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

**አስቴር ኤልያስ**



አዲስ አበባ፡- በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቀው የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ በብቃትና ውድድር ላይ የተመሠረተ ነጻና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስን የሚፈጥር መሆኑን የምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማት ሥራ ስምሪትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር)፤ አስታወቁ። አዋጁ የሠራተኛውንም ጥቅማጥቅም ያካተተ እንደሆነም ገለጹ።

አዋጁ የመንግሥት ሠራተኛው በብቃትና ውድድር ላይ ተመስርቶ ተገቢ የሆነ ጥቅም እንዲያገኝ የወጣ እንጂ የመንግሥት ሠራተኛውን ለመቀነስ ያለመ እንዳልሆነ፣ መረጃን በማጣመም ሕዝብን ለማደናገር የሚደረገውም ጥረት መሠረተ ቢስ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ነገሪ (ዶ/ር)፤ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ አዋጁ የሠራተኛውን ግዴታ ብቻ ሳይሆን መብቱንም የሚያስጠብቅ ፣ ሲቪል ሰርቪሱን ብቁ፣ ነጻና ገለልተኛ የሚያደርግ ነው።

ብቃት ላይ የተመሰረተ ውድድር መኖሩ ለሠራተኛው የሚያስገኘው ውጤት እንዳለው ያመለከቱት ነገሪ (ዶ/ር)፤ ዘመድ ስለሌለኝ ወይም ገንዘብ ስለሌለኝ መቀጠር አልቻልኩም የሚለውን ቅሬታ የሚያስወግድ ይሆናል ብለዋል። ከዚህ አኳያ ሥርዓቶች የሚዘረጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ነጻ እና ገለልተኛ ሲቪል ሰርቪስ ማለት አንድ ሰው የፖለቲካ ፓርቲ አባል ስለሆነ የፈለገውን ያደርጋል ማለት አለመሆኑን የሚያሳውቅ፣ በሃይማኖት እንዲሁም በዝምድና እና ሌላ ሰው በመሀል ገብቶ ተጽዕኖ እንዳይፈጥር የሚከላከል፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያለምንም ልዩነት ፣ ያለማንም ጣልቃ ገብነት እንዲሁም ያለማንም ተጽዕኖ ማገልገል የሚያስችል ማለት ነው ብለዋል።

የአዋጁም ዓላማ ነጻና ገለልተኛ የሆነ ሲቪል ሰርቪስ በመፍጠር ጥራት ያለው፣ ቀልጣፋ አገልግሎት የሚሰጥ ማድረግ ነው ያሉት ነገሪ (ዶ/ር)፤ ይህም የተገልጋዩን ሕዝብ

«አዋጁ በብቃትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ ዘላቂ ሰላም እንደሚያስፈልግ ተገለጸ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማደግና ለመለወጥ ዘላቂ ሰላም በእጅጉ ያስፈልጋል ሲሉ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ ገለጹ።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ከመቄዶንያ በጎ አድራጎት ማህበር ከመቄዶኒያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ጋር ያዘጋጁት የጸሎት መርሀ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንደገለጹት፤ ሰላም የመረዳዳት፣ የመግባባት፣ የመተማመን እና በነጻነት የመኖር መሠረት ነው።

ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ፣ ለመለወጥ እና ለመበልጸግ ሰላም በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ከዚህ አኳያ ሁላችንም በዘርና በሃይማኖት ሳንለያይ ስለሰላም መሥራትና መጸለይ ይጠበቅብናል ሲሉ አስታውቀዋል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሰላምና መተማመን የቀነሰበት፣ ጥላቻ የገነነበት፣

ነገን ከዛሬ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- እዮብ ተፈሪ

## “ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ አካል ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን ነው”

- ሂሩት ገብረስላሴ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር

ገጽ 2

# በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና በኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራር መካከል የሰላም ስምምነት ተፈረመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ ፡- በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና በኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራር ጃል ሰኚ ነጋሳ መካከል የሰላም ስምምነት ተፈራረመ። ስምምነቱ ለኦሮሞ ሕዝብ ትልቅ እፎይታ እንደሚሰጥም ተገለጸ።

ከመከላከያ ሠራዊት ይፋዊ የማኅበራዊ ትስስር ገጽ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የሰላም ስምምነቱ ትናንት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እና በጃል ሰኚ ነጋሳ መካከል ተፈርሟል።

በሰላም ስምምነቱ የፊርማ ሥነሥርዓት ላይ አቶ ሽመልስ አብዲሳ፤ የኦሮሞ ሕዝብ በባህልና በወጉ መሠረት በሬዎቹን ጠምዶና ፈረሶችን ጭኖ በመውጣት ሰላም ይውረድ ባለው መሠረት ጥሪውን ተቀብላችሁ በመምጣታችሁ በራሴና በክልሉ መንግሥት ስም አመሰግናለሁ ብለዋል።

የመከላከያ ሠራዊቱ ለሰላም ስምምነቱ ላበረከተው አስተዋፅኦም ምስጋና አቅርበዋል።

የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ከፍተኛ አመራር የነበሩት ጃል ሰኚ ነጋሳ በበኩላቸው፤ የፖለቲካ ልዩነቶች ይኖራሉ፤እኛም ያለንን የፖለቲካ ልዩነት በጠመንጃ ከመፍታት በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት ወስነን የሰላም ስምምነቱን መርጠናል ብለዋል። ስምምነቱ ለኦሮሞ ሕዝብ ትልቅ እፎይታን እንደሚሰጥም አስታውቀዋል።

በስምምነቱ መርሀ ግብር ላይ የተገኙት የጦር

በኦሮሚያ ክልል ... ወደ ገጽ 12 ዞሯል




ዜና



አቶ ኢሳያስ ለማ

# በኦሮሚያ ክልል በአራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት እየተሠራ ነው

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጋ መስኖ ስንዴን ለማልማት ከታቀደው አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አራት ሚሊዮኑ በኦሮሚያ ክልል የሚለማ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በ2017 ዓ.ም በበጋ መስኖ ልማት ስንዴ በጠቅላላ ለማልማት ከታቀደው አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ አራት ሚሊዮኑ በኦሮሚያ ክልል የሚለማ ነው፡፡

ክልሉ ከአለው የቆዳ ስፋት፤ ለበጋ መስኖ ልማት ከአለው ምቹነት፤ በውሃ ሀብት እና በመሳሰሉት አቅሞች ምክንያት የበጋ መስኖ ልማት በስፋት እንደሚካሄድ ጠቁመው፤ ከኦሮሚያ ክልል ቀጥሎ በአማራ ክልል የበጋ መስኖ ስንዴ በከፍተኛ ሁኔታ የማልማት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡ በክልሉ በመኸር እርሻም ሆነ በበጋ መስኖ ልማት የስንዴ ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እየተመረተ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡

የስንዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሁሉም ክልሎች፤ ቆላማ አካባቢዎች ሳይቀሩ የበጋ መስኖ ስንዴ የማልማት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ኢሳያስ ፤ ቀደም ሲል የበጋ መስኖ ስንዴ በፕሮጅክት እንጂ ትኩረት ተሰጥቶት በስፋት አይሠራበትም፡፡ የተጀመረውም በሶስት ሺህ 500 ሄክታር መሬት ነበር ብለዋል፡፡

ከለውጡ በኋላ የበጋ መስኖ ልማት ከፕሮጀክት አልፎ በስፋት እየለማ ነው፤ በ2017 ዓ.ም አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው፡፡ ለማልማት ከታሰበው አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን ማለትም ህዳር 17/2017 ዓ.ም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታሩ ታርሷል፤ ከታረሰውም አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታሩ ውስጥ እስካሁን ማለትም ህዳር 17/2017 ዓ.ም ሰባት መቶ 80 ሺህ ሄክታሩ በዘር መሸፈኑን ገልጸዋል፡፡

በ2017 ዓ.ም የበጋ መስኖ ልማት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመሸፈን አንድ መቶ 72 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# “ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ አካል ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን ነው”

- ሂሩት ገብረስላሴ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር

ኢያሱ መሰለ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን እንደሆነ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረስላሴ አመለከቱ፡፡ ይህ የተዛባ አስተሳሰብ ወደ ችግር እየከተተን መሆኑን አመለከቱ፡፡

ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረስላሴ በተለይ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳመለከቱት፤ ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ አካል ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባችን ወደ ችግር እየከተተን መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የራስን ብቻ ከመፈለግ ወጥቶ የሌላውን የማህበረሰብ ክፍል /ዜጋ ቁስል ማዳመጥ እና ለመረዳት መሞከር ይገባል ያሉት ምክትል ዋና ኮሚሽነሯ፤ ይህን ማድረግ ከቻልን ሥራችን ውጤታማ ይሆናል ብለዋል፡፡ ጉዳዩ ከሀገር ህልውና ጋር የተያያዘ ነው፤ ሁሉም ነገር የሚኖረው ሀገር ስትኖር እስከሆነ ድረስ ለምክክር ኮሚሽኑ ሥራ ስኬት ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

እያንዳንዱ ሰው በጉዳዮች ላይ የየራሱ አቋም አለው፤ ያ አቋሙ በዝምድና፣ በዝንባሌ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ እንጂ በጥያቄው እውነተኛ መልስ ላይ የተመረኮዘ ላይሆን ይችላል፡፡ ህብረተሰቡ እንዲህ አይነቱን ኋላቀር አስተሳሰብ ትቶ በእውቀትና በእውነት ላይ የተመሰረተ መረጃ እንዲጨብጥና ራሱን በዚህ መልክ እንዲገነባ ምሁራን እውቀትን የመፈለግ ባህል ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰርጽ አበክረው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አመልክተዋል፡፡



ምሁራንም በሚያውቋቸው፣ በሚገምቷቸው እና የኢትዮጵያ ሕዝብን ሳያግባቡ የቆዩት እነዚህ እነዚህ ናቸው በሚሏቸው ነጥቦች ዙሪያ ከስሜትና ከግል ፍላጎት የጸዱ፣ እውነትን፣ እውቀትንና ተጨባጭ መረጃን መሠረት ያደረጉ ጥናቶችን በማጥናት አንዳንድ የሚያወዛግቡ ነገሮችን አብላልተው በማብራራትና ብዥታዎችን በማጥራት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

የሲቪል ማህበራትም ቢሆኑ በሚያምኑባቸውና በወሰዷቸው አቋሞች ላይ ጥናት እያጠኑ ለሕዝቡ ማሳወቅ እንደሚጠበቅባቸው ያመለከቱት ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት፤ ሕዝብን የማደራጀት፣ የማንቃት፣ የማነቃነቅ ሥራ ሊሠሩ ይገባል፤ እያንዳንዱ ግለሰብም ይሁን ተቋም የሚጠበቅበትን ሲያደርግ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ታገዘ ማለት ነው ብለዋል፡፡

ሚዲያዎች አልፎ አልፎ ኮሚሽኑ የሚያካሂዳቸውን ሁነቶች ብቻ መዘገብ ሳይሆን ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት በመስጠትና ቋሚ ፕሮግራም በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራን ሊሠሩ ይገባል፡፡ የሀገር ጉዳይ የእያንዳንዱ ዜጋ ጉዳይ ስለሆነ ሚዲያዎች ራሳቸው የጉዳዩ ባለቤት ሆነው በየጊዜው ሽፋን በመስጠት ወደ ማህበረሰቡም ሆነ ወደሚመለከተው አካል የማስረጽ ሚናቸውን በመወጣት የኮሚሽኑን ሥራ ማገዝ እንደሚጠበቅባቸው አመልክተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ምክር ቤታቸው ስለሀገርና ስለሕዝብ ሰላምና ደህንነት የቆሙና የተመሰረቱ እንደመሆናቸው የሕዝቦች ተግባብቶ መኖርና የሀገር ደህንነት ጉዳይ ያስጨንቃቸዋል፤ በዚያው ልክ መሥራትም ከነሱ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል፡፡

በዚህ ሀገራዊ ምክክር የሚገኘው ውጤት የሚጠቅመው ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች ነው፡፡ ሥራውን የኮሚሽኑ ብቻ አድርጎ መመልከት አግባብነት የለውም፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ እውን የሚሆነው የመላው ሕዝብና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲታከልበት እንጂ ኮሚሽኑ በሚሠራው ሥራ ብቻ አይደለም፡፡ ኮሚሽኑ ከእርሱ የሚጠበቁትን እና መሠራት ያለባቸውን ትልልቆቹን ሥራ ያከናውናል፤ እንደ ዜጋ ፣ እንደ ባለድርሻ አካል፣ ሁሉም ኃላፊነቱን ቢወጣ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ይጠቀማሉ ብለዋል፡፡

ከምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረስላሴ ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ ሙሉቃል ገጽ 8 ይመልከቱ፡፡

# የምግብና የመሬት ሥርዓት ሽግግርን በማቀናጀት አካታች የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት ይገባል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የምግብና የመሬት ሥርዓት ሽግግርን በማቀናጀት አካታች ኢኮኖሚያዊ እድገት ማምጣት እንደሚገባ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር አዘጋጅነት በኢትዮጵያ የመሬት ማሻሻያና በምግብ ሥርዓት ላይ ያተኮረ ውይይት ከትናንት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር አዘጋጅነት በኢትዮጵያ የመሬት ማሻሻያና በምግብ ሥርዓት ላይ እየተካሄደ ባለው ውይይት ላይ ፤በግብርና ሚኒስቴር የሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪና የኢትዮጵያ ሥርዓተ ምግብ ሽግግር ዋና አስተባባሪ ጌታቸው ዲሪባ (ዶ/ር) እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የሕዝቡን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ከፍተኛ ጥረት እያደረገች ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ትልቁን ሚና ይጫወታል፡፡

ከዛሬ 50 ዓመት በፊት መሬት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተብሎ ሲታወጅ ተስፋ የተጣለበት የነበረ ቢሆንም፤ አጋጣሚው ያንን ዓላማ የሚያሟላና ሁሉም ደሃ እንዲሆን የተደረገበት ሁኔታ እንደነበር ጠቁመው፤ ካለፉት ዓመታት ጀምሮ ይህንን አካሄድ ለማስተካከል ብዙ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከወራት በፊት የተደረገው የገጠር መሬት አስተዳደር ማሻሻያ አዋጅም አሁን ላይ ጥሩ ለውጦች እያመጣ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ አማካሪው ገለጻ፤ በዚህም ገበሬው መሬቱን የማስተላለፍ፣ የማስያዝ፣ ለልማት የማዋል፣ ክላስተር አድርጎ የማረስ እድሎችንም አግኝቷል፡፡ የኢትዮጵያ የምግብ ፍላጎት በየቀኑ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ይህንን የሚመጥን የቴክኖሎጂ እድገትና ፈጠራ ይጠይቃል፡፡

የኢትዮጵያ የእርሻ መሬት የተበጣጠሰ በመሆኑ ሜካናይዜሽንን በመተግበር የሚፈለገውን ምርትና



ምርታማነት ለማምጣት አስቸጋሪ ነው ያሉት ጌታቸው (ዶ/ር)፤ በአሁኑ ወቅት መሬትን በክላስተር በማረስ ከፍተኛ ምርት የማግኘት እንቅስቃሴዎች እየታዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ምክትል ዳይሬክተር ፍሬው ተገኝ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የሙያ ማህበራት ጽንሰ ሃሳቦችን ወደ ተግባር በመተርጎም በጥናትና ምርምር ውጤቶች በማስደገፍ ለለውጥ ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን እንደሚያመነጩ በመግለጽ፤ ተቋማቸው የተለያዩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማከናወን ለሚመለከታቸው አካላት የመፍትሄ ሃሳብ እንደሚያቀርብ ጠቁመዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በግብርናና በሌሎችም ዘርፎች 400 የሚጠጉ ተግባር ላይ ያተኮሩ የምርምር ሥራዎችን ሠርቷል፡፡ ከእነኝህ ጥናቶች ውስጥም 26 በመቶ የሚሆነው ለሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ እቅድ ዝግጅት ድጋፍ ያደረገ ነው፤ የተቀረው ለመንግሥት ውሳኔ ሰጭነት ማገልገሉን ምክትል ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የመሬትን ምርታማነት ማሳደግ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ በሰፊው እየሠራበት ይገኛል ያሉት ፍሬው (ዶ/ር)፤ በኮሜርሻላይዜሽንና በክላስተር ዘርፍ የሚስተዋለው የመሬት መበጣጠስ፣ ቴክኖሎጂዎችን አለመተግበርና ሌሎችም ክፍተቶችን ለመሙላት አዲሱ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ያግዛል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የግብርና ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት እንደሻው ሀብቴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የምግብና የሥርዓተ ምግብ ደህንነትን በማረጋገጥ ዜጎችን መመገብ የመንግሥት ቀዳሚው የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡ በዚህም የመሬት ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

መሬት ለኢትዮጵያውያን ኢኮኖሚም ፖለቲካም ጭምር መሆኑን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ መሬት ባለፉት ጊዜያት በፖለቲካ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ለውጥ እንዲመጣ ማድረጉን አስታውሰዋል፡፡

ማህበሩ አቅምን ለማጎልበትና በግብርናው ዘርፉ ላይ የሚያተኩሩ መድረኮችን በማዘጋጀት ተገቢ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ለማዘጋጀት አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ አመልክተዋል፡፡

# ከነጭ ወርቁ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ለማሳደግ

**ማህሌት አብዱል**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ አቅርባ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከምታገኝባቸው የግብርና ምርቶች አንዱ የሆነው የሰሊጥ ገቢ እያንሰራራ መሆኑን ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ ሰሊጥ በዓለም ገበያ ተፈላጊ ቢሆንም፣ ባለፉት አምስት ዓመታት በተለያዩ ሀገራዊ ችግሮች ምክንያት በምርት መጠን ቀንሷል፤ ገበያውም የመቀዝቀዝ ሁኔታ ታይቶበታል።

በቅርቡ በተካሄደው የጥራጥሬና ቅባት እህሎች ዓለም አቀፍ ጉባኤ ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ ጥራጥሬና ቅባት እህል ላኪዎች ማህበር የቦርድ አባል ሙሉጌታ ኪ/ማርያም (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት በፊት ከ300 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ሰሊጥ አምርታ ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት ትልክ ነበር። ባለፉት አምስት ዓመታት ግን ምርቱ እየቀነሰ በመምጣቱ የምትልከው ምርት ከ200 ሺ. ሜትሪክ ቶን በታች ነው።

ይህ የምርት መቀነስ የተወሰነ መሻሻል አሳይቶ አምና ከነበረበት 125 ሺህ ሜትሪክ ቶን አሁን ወደ 163ሺህ ሜትሪክ ቶን ከፍ ብሏል። ለዓለም ገበያ አቅርባ በቶን የምታገኘው አንድ ሺህ 500 ዶላርም ወደ አንድ ሺህ 800 ዶላር አድጓል ይላሉ።

ለምርቱ መቀነስ በዋናነት የሚጠቀሰው ሰሊጥ በስፋት የሚመረትባቸው እንደ ሁመራ ባሉ አካባቢዎች የተካሄደው የሰሜኑ ጦርነትና ከእሱ ጋር የተያያዙ ግጭቶችና አለመረጋጋት መከሰቱ፤ የአየር ንብረት ለውጥና አርሶ አደሩ የበለጠ አዋጪነት ወደ አላቸው ሰብሎች ማምረት መግባቱ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ሙሉጌታም (ዶ/ር) አርሶ አደሮች ሰሊጥ ከማምረት ወደ ሌሎች ሰብሎች ፊታቸውን ማዞራቸውን ይጠቅሳሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ያልታረሰ መሬት መኖሩንም ያመለክታሉ።

ስልጡን ያልሆነው የሰሊጥ ንግድ ሥርዓት ሀገሪቱ ከቅባት እህሉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳሳጣትም ይናገራሉ። ‹‹ምርቱን ላኪዎች በተባለው ወቅት ያለመጫን፤ የሎጅስቲክስ ችግርና ኮንትራትን በአግባቡ አለመፈፀም የመሳሰሉት ጉድለቶች መኖራቸውም ሀገሪቱ ከምርቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንዳትሆን አድርገዋታል›› ብለዋል።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ምርምር ዳይሬክተር ታደለ ማሞ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት በፊት በዓለም የሰሊጥ ገበያ ከምርጥ አስር ሀገራት አንዷ ነበረች። ከሁለት ዓመት በፊትም 11ኛ ደረጃ ላይ ነበረች፤ በተለይም ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ የምርት መቀነስ መከሰቱ ደረጃዋን ለማስጠበቅ አዳጋች ሆኖባታል። የሰሊጥ ምርታማነት ዝቅተኛ መሆኑም የጥራቱን ያህል በብዛት በማምረት ገበያውን መቆጣጠር አልተቻለም ይላሉ።

እንደ ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ ያሉ ሰሊጥ በስፋት የሚያመርቱ ሀገራት በሄክታር 48 ኩንታል እንደሚያመርቱ ታደለ (ዶ/ር) ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ እያመረተች ያለችው በአማካኝ ከስምንት ኩንታል እንደማይበልጥ ይናገራሉ።

በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ዝርያዎችን ማሻሻልና ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ማድረግ ላይ ውስንነት እንደሚስተዋሉ ጠቅሰው፤ አሁንም የኢትዮጵያ ሰሊጥ በዓለም ገበያ ተፈላጊ መሆኑን አስታውቀዋል።

ከኢትዮጵያ ሰሊጥ መዳረሻ ሀገራት መካከልም ቻይና፣ እስራኤል፣ ቬትናም፣ ቱርኪዬና ሳዑዲ አረቢያና ጃፓን ዋነኞቹ ናቸው። ይሁንና ከፍላጎቱ አንፃር በሚፈለገው ደረጃ ሰሊጥ እየተመረተ አይደለም ነው ያሉት።

ታደለ (ዶ/ር) አብነት አድርገው እንደሚጠቅሱት፤ ቻይና በየዓመቱ እስከ 382 ሚሊዮን ዶላር ወጪ በማድረግ ኢትዮጵያ ሰሊጥ የመግዛት ፍላጎት ቢኖራትም በአሁኑ ወቅት እየተሸጠ ያለው ከ70 ሚሊዮን ዶላር አይበልጥም። ይህም መላክ ከሚገባው አንድ አራተኛ ብቻ መሆኑን ያመላክታል።

ሙሉጌታ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የምትልከው ሰሊጥ እሴት ያልተጨመረበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ መሆኑም የምርቱ ባለቤት እሷ ሆና እያለች ሌሎች ሀገራት በምርቱ ላይ እሴት እየጨመሩ ለገበያ እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

ይህም ሀገሪቱን የበይ ተመልካች አድርጓታል። በተለይ እንደ እስራኤል ያሉ ሀገራት ከኢትዮጵያ የገዙትን ሰሊጥ እሴት ጨምረው ወደ ተለያዩ የዓለም ሀገራት በመላክ ከፍተኛ ዶላር ያገኛሉ ሲሉ ይገልጻሉ።

አሁንም የኢትዮጵያ ሰሊጥ በዓለም ገበያ ላይ የጥራትና የዋጋ መለኪያ መስፈርት ተደርጎ እንደሚወሰድ በመጥቀስም ታደለ (ዶ/ር)፤ የኢትዮጵያ ሰሊጥ አሁንም ተፈላጊ ነው ሲሉ የጠቀሱትን ሃሳብ የሚያጠናክር ሃሳብ አንስተዋል።

‹‹ኢትዮጵያ ሰሊጥ አንድ ሺህ 700 ዶላር ሲሸጥ የሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሰሊጥ አንድ ሺህ 600 ዶላር ይሸጣል። ሌሎች ሀገራት የሚወስዱት ከእኛ የተረፈውን ገበያ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ የገበያ ችግር ሳይሆን በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አለመቻሏ ነው ችግሯ ሲሉ ጠቅሰው፤ ከሁሉም በላይ ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

መንግሥት ለስንዴ የሰጠውን ትኩረት በሰሊጥም እንዲደግም ጠይቀው፤ ለሰሊጥ ተስማሚ በሆኑ አካባቢዎች በዓመት ሁለትና ከዚያ በላይ ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚገባም አመልክተዋል። ምርታማነትን ከማሳደጉ ጎን ለጎንም እሴት ጨምሮ ለዓለም ገበያ በማቅረብ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ሊሰራ ይገባል ሲሉም መክረዋል።

እንደ ታደለ (ዶ/ር) ማብራሪያም፤ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ አንዱና ወሳኙ ቁልፉ ነገር ምርታማነትን መጨመር ነው። ዘመኑን የዋጁ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና ምክረ-ሃሳቦችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ሰሊጥ ያለውን ተቀባይነት ለማስቀጠል እንዲቻል ምርቱ ከማሳ እስከ ገበያ መዳረሻ ድረስ ጥራቱን ጠብቆ እንዲላክ ማድረግ ይገባል።

በተለይ ለአፍላቶክሲን እንዳይጋለጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። ለዚህ ደግሞ የዘመነ የአመራረት ሂደትን መከተል የሚያስፈልግ ሲሆን፤ አጠቃላይ አሰራሩንም ዲጂታላይዝ ማድረግ ወሳኝ ነው ይላሉ።

ዋነኛ የገበያ መዳረሻ ሀገራትን የመግዛት አቅም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መለየትም ይገባል። ፍላጎታቸውን ያማከለ ስራ መስራት በዓለም ገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችላል። የተወዳዳሪ ሀገራትን የግብይት ስልትና ስትራቴጂ ማጥናት፣ አዳዲስ ስልቶችን መንደፍ ይጠቅማል።

በአቅም ደረጃ እንደ ህንድ ፣ ሱዳንና ናይጄሪያ ተወዳዳሪዎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ሀገራት እንዴት ስኬታማ ሊሆኑ ቻሉ? የማምረት ስልታቸው ምንድን ነው? የጥራት መስፈርታቸውን እንዴት ነው የሚያሟሉት? የሚሉትን ጉዳዮች በጥልቀት ማወቅም ይገባል ነው ያሉት።

‹‹ከሁሉ በላይ ለምርት መቀነስ ዋነኛ ምክንያት የሆነውን የፀጥታ መደፍረስ ማስወገድ ይገባል›› ሲሉ ታደለ (ዶ/ር) አስገንዝበው፤ በተለይም ከፍተኛ አምራች በሆኑት እንደሁመራ ባሉ አካባቢዎች ለአምራቹ ምቹና ሰላማዊ ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስፈልግ አስታውቀዋል።

በቅርቡ የተመረቀው ብሔራዊ የጥራት መንደርም እንደ ሰሊጥ ያሉ የግብርና ምርቶችን ጥራት በማረጋገጥ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ምርት ለማቅረብ ትልቅ ዕገዛ የሚያደርግ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

# የሆቴል አስተናጋጆች የአለባበስ ሥርዓት ደንብ አንድምታዎች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

**ዜና ትንታኔ**



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ቱሪዝምና ኪነጥበብ ቢሮ በመስተንግዶ እና ተመሳሳይ ጉዳዮች ዙሪያ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በሕግ ለመፍታት የሆቴል እና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች አለባበስ ደንብ ቁጥር 178/2016ን ተግባራዊ ማድረጉ ይታወሳል።

ደንቡ ፀድቆ ተግባር ላይ መዋሉን ተከትሎ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትና እሴትን የጠበቀ የመስተንግዶ አገልግሎት ከማስፈንና የሀገሪቱን ገፅታ ከመገንባት አንፃር ምን ፋይዳ ይኖረዋል? ስንል የዘርፉን ምሁራን አነጋግረናል።

ወይዘሮ ቱሩፋት በላይነህ በሕግ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ጋዜጠኛ፣ ጠበቃና የሕግ አማካሪ ናቸው። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ እስከ አሁን ያለው የሆቴልና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት አለባበስ ሥርዓት የኢትዮጵያውያን ባህል፣ እሴት የሚመጥን አልነበረም።

በተለይ ሴት የመስተንግዶ ሠራተኞች ሰውነታቸውን የሚያጋልጥ አለባበስ እንዲከተሉ ይደረጋል፤ ወንዶችም ቢሆን በአንዳንድ የሰውነት ክፍሎቻቸው ደንበኞችን በማይመጥን አለባበስ ይታያሉ። ትርጉማቸው ምን እንደሆነ የማይታወቅ ንቅሳቶችንም እንዲሁ ያደርጋሉ።

የሕግ አማካሪዋ፤ ድርጊቱ የተጠቃሚዎችን መብት ከመጋፋት በላይ የሀገርን ገጽታ በብዙ መልኩ እንደሚያበላሽ፣ ኢትዮጵያዊነትንም እንደሚያሳንስ ያምናሉ። አለባበሳቸውም ሆነ የሚጠቀሟቸው ጌጣጌጦች በዚህ ድርጊት የማይታሙትንም ጭምር በሌሎች ባህል እንዲዋጡ ያደርጋል ይላሉ። ይህንን ድርጊት ለመከላከል የሚያስችል ሀገር አቀፍ ሕግ ባይኖርም ዓለም አቀፉን ደረጃ እንኳን ያሟላ አለባበስ ሥርዓት በስፋት እየተለመደ መሆኑን ያነሳሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ የበርካታ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች የሚደረግባት እንደ መሆኗ መጠን ኢትዮጵያን ማየት የሚቻልበት እድል ሰፊ እንደሆነ የጠቆሙት የሕግ አማካሪዋ፤ የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ የከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀፅ 95 መሠረት ይህንን ደንብ ማውጣቱ ፋይዳው ብዙ እንደሆነ ተናግረዋል።

ደንቡ ከላይ የተጠቀሱት ኢትዮጵያዊ እሴትን የሚፃረሩ የመስተንግዶ ሥርዓትን ያልተከተሉ ጥሰቶችን ከማስተካከሉም ባሻገር የሀገርን ገጽታ ከመገንባት አኳያ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነም ያብራራሉ። በተለይም ኢትዮጵያዊ ሥነ-ሥርዓትን፣ እሴቶችንና የአለባበስ ሥርዓትን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ያነሳሉ።

የመስተንግዶ ሠራተኞችን አለባበስ የሚወስን ምንም ሕግ እንደሌለ የሚናገሩት ወይዘሮ ቱሩፋት፤ ይህ ደንብ ሕግ ሆኖ ለማገልገል ጭምር እንደሚረዳ ያስረዳሉ። ኢትዮጵያ የራሷ የሕግ ሥርዓት እንዲኖራት መሠረት የሚጥል መሆኑንም ይናገራሉ። የኢትዮጵያን ትክክለኛ ገፅታ ለማሳየት እንደሚረዳ ባህልና እሴቶችን ለማወቅ የሚመጡ ጎብኚዎችን ቁጥር በማሳደግ በቱሪዝም ዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ከፍ ያደርጋል ይላሉ።

እንደ ሕግ አማካሪዋ ገለጻ፤ ደንቡ ሀገራችንን በብዙ መስኩ የሚያስተዋውቅ ነው። አንዱ ጥሩ ማሳያ የብሔር ብሔረሰቦች የአለባበስ ባህል ለቀሪው ዓለም ማስተዋወቅና ኢትዮጵያዊ ሥነሥርዓትን ማስረፅ ነው።

‹‹በመስተንግዶ ባለሙያዎች የሚለበሱና የማይለበሱ ነገሮችን ደንግጓል›› የሚሉት የሕግ አማካሪዋ፤ የደረት ክፍልን ያልሸፈነ ወይም ከአንገት በታች ያለውን የሰውነት ክፍል የሚሸፍን ሸሚዝ ያለበሰ፣ የሴቶች ጉርድ ቀሚስ ቁመቱና ቅዱ ከጉልበት በላይ ከሆነ፣ ከጋብቻ ቀለበት ውጪ ጌጣጌጦችን በሚታዩ የሰውነት ክፍሎች ላይ ከተደረገ በደንቡ መሠረት የሚያስቀጣ መሆኑን አንስተዋል። በደንቡ የተቀመጡት ቅጣቶች የተለያዩ ሲሆኑ፤ ሕግ ተላልፎ የተገኘ አሠሪ (አካል) በድንጋጌው መሠረት ከአምስት ሺህ ብር ጀምሮ ተቋሙን እስከ ማሸግና የንግድ ፈቃዱን እስከመንጠቅ የሚደርስ እርምጃ እንደሚወሰድበት ተጠቁሟል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች የማህበራዊና አካቶ ትግበራ ባለሙያ ወይዘሮ ምህረት መኩሪያ ደንቡ መውጣቱ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን የወይዘሮ ቱሩፋትን ሃሳብ ደግፈው ያብራራሉ። እርሳቸው እንዳሉት፤ የደንቡ መውጣት ባህላዊና ኢትዮጵያዊ ሥርዓትን የተላበሱ አልባሳት እንዲዘወተሩ ያግዛል፤ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ለሚሠሩ ባለሙያዎችም የሙያ ክብር እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤ ወጥ የሆነ የአለባበስ፣ የጌጣጌጥ እና የመዋቢያ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲፈጠርም እድል ይሰጣል። ከሁሉም በላይ የሀገር ባህልና እሴት እንዲጠበቅ በማድረግ በዘርፉ ተሰማርተው የሚሠሩ ሙያተኞችን ከአካላዊ፤ ሥነ-ልቦናዊና ጾታዊ ጥቃት እንዲጠበቁ ያደርጋል።

ሁለቱም ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ደረጃ ፀድቆ ሥራ ላይ የዋለው ደንብ በአግባቡ መተግበር ከቻለ በቀጣይ ወጥ የሆነ የአስተናጋጆች አለባበስ ይሰፍናል።

ባህላዊ እሴቶቻችንን ያስተዋውቃል፤ ቱሪዝሙን በማነቃቃት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ከፍ ያደርጋል። ከሁሉም በላይ ሙያው የተከበረ የሆቴልና የአገልግሎት ተቋማት ሠራተኞችን ይፈጥራል። ሕጋዊ አሠራሮችን ከመዘርጋት አኳያም የማይተካ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

# በማእከላዊ ኢትዮጵያ የእንስሳት ልማትን ለማረጋገጥ በመኖና ጤና ላይ መሠራት እንዳለበት ተገለጸ

**ቤዛ እሸቱ**

አዲስ አበባ፡- የእንስሳት ልማትን ለማረጋገጥ የመኖ አቅርቦትና የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ የማእከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ። በተለያዩ ጊዜያት እየተከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት እያደረሱ ያሉ የእንስሳት በሽታዎች መኖራቸውም ተመላክቷል።

በክልሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ስሩር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የእንስሳት ልማትን ለማረጋገጥ የእንስሳት ጤናና መኖ ላይ በስፋት መሥራት ይገባል።

መኖና ጤና በሌለበት የእንስሳት ሀብትን ውጤታማ ማድረግ አይቻልም ያሉት የቢሮ ኃላፊው፤ የእንስሳትን ጤና ለመጠበቅና በቂ መኖ ለማቅረብ በክልሉ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ግለሰቦች የሚያመርቱት መኖ ከእንስሳት ፍጆታ የተረፈ እንዲሆንና የተረፋቸውን መኖ ለገበያ አቅርበውት የገቢ ምንጭ እንዲሆናቸው ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን ጠቁመዋል።

በክልሉ በርካታ የአርሶአደር ኅብረት ሥራ ማህበራት የመኖ ማቀነባበሪያ እንዳላቸው የገለጹት አቶ ኡስማን፤ ኢንዱስትሪዎቹ አቅማቸውን እንዲያጠናክሩ እየተሠራ ነው። ኢንዱስትሪዎቹ መኖን ለዶሮ፣ ለወተት ላም አርቢዎችና የማድለብ ሥራ ለሚሰሩት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርቡ እየተደረገም ነው ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁ ወጣቶችን በማደራጀት የመኖ ማቀነባበሪያ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ተዘጋጅቶላቸው እየሠሩ ነው። በዚህም ተስፋ የሚሰጥ ውጤት እየታየ ነው። በየአካባቢው ካሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚገኙ ምርቶችን በማቀናጀትና በኢንዱስትሪዎች መኖን ማምረት የሚቻል ቢሆንም የአፈጻጸም ችግር ስላለ አቅም ለማጎልበትና ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው።

በክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእንስሳትና የአሳ ሀብት ዘርፍ ኃላፊ አቶ እያሱ ተረፈ በበኩላቸው፤ በክልሉ መከላከልን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ሥራ በስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደክልል በተለያዩ ጊዜያት እየተከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳት እያደረሱ ያሉ የእንስሳት በሽታዎች መኖራቸውን ጠቁመው ፤ ሁሉንም እንስሳት ያማከለና የጊዜ ካሌንደርን መሰረት በማድረግ ክትባቶችን ተደራሽ ለማድረግ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ እያሱ ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ አራት ወራት አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን እንስሳት ይከተባሉ ተብሎ ታቅዶ አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን እንስሳት ተከትበዋል። ክትባት ቢኖርም እንስሳት መታመማቸው ስለማይቀር የህክምና አገልግሎት እንደሚሰጥና በዚህም የታመሙ እንስሳትን ማከም የሚያስችል መሰረተ ልማት የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል። የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በቢሮው የክሊኒክ አገልግሎት ክፍል መኖሩንና በዛም ሸኮና ቀንድና ሌሎች ነገሮችን የማስተካከልና መሰል ሥራዎች ሥራ ይሠራል።

በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰትና ምርታማነት ላይ ጉዳት የሚያደርስ የገንዲ በሽታ መኖሩን የሚገልጹት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በሽታውን ለመከላከል 2ሺ 200 እንስሳትን ኬሚካል መቀባት መቻሉን ገልጸዋል። ያም ቢሆን በሽታውን ለመከላከል የሚያስችል የኬሚካል አቅርቦት እጥረት መኖሩንና ግዢ ለመፈጸምም በሀገር ውስጥ በቂ አቅርቦት አለመኖሩ ችግር እንደሆነባቸው ተናግረዋል።

በሌማት ትሩፋቱ የታቀዱ እቅዶችን ለማሳካት በሚያስችል መንገድ አርሶአደሩ እንስሳቱን በሞት እንዳያጣና በበሽታ ምክንያት ምርት እንዳይቀንስ አስፈላጊውን ግብዓት የማቅረብና የባለሙያ አቅም በስልጠናዎች ማሳደግ ጥኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

## “አዋጁ በብቃትና በውድድር ላይ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እርካታ የሚጨምር ከመሆኑም በተጨማሪ ኢትዮጵያን የሚመስል ሲቪል ሰርቪስ መገንባት የሚያስችል ፣ የሀገርንም እድገት የሚያሳልጥ እንደሆነ አመልክተዋል።

ብቃትንና ውድድርን መሠረት ያደረገ ቅጥር መኖሩ ለሠራተኛው ተስፋ የሚሰጥ እንደሆነ የገለጹት የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው፤ አዋጁ በሥራ ላይ ላሉትም ሆኑ በቅጥር ላይ ለሆኑትም መልካም ተስፋ ይዞ የመጣ እንደሆነ አስታውቀዋል።

አዋጁ የመንግሥት ሠራተኛው በብቃትና ውድድር ላይ ተመስርቶ ተገቢ የሆነ ጥቅም እንዲያገኝ የወጣ እንጂ የመንግሥት ሠራተኛውን ለመቀነስ ያለመ እንዳልሆነ ያስታወቁት ነገሪ (ዶ/ር)፤ መረጃን በማጣመም ሕዝብን ለማደናገር የሚደረገውም ጥረት መሠረተ ቢስ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው፤ አዋጁ በሠራተኛው ትጋትና ጥንካሬ ላይ ተመስርቶ ጥቅማጥቅሙን እንዲያገኝና ብሎም ተወዳድሮ የተሻለ ሲያመጣ እንዲሸለምም ጭምር እንጂ እንዲቀነስ የጸደቀ አዋጅ አለመሆኑንም ተናግረዋል።

ከሠራተኛ ጥቅማጥቅም ጋር በተያያዘ የሠራተኛው ደመወዝም ሆነ በየጊዜው ይጨመርለት የነበረው እርከን መቆሙ የሠራተኛውን ተነሳሽነት መቀነሱን አስታውሰው፤ ይህ መሆኑ የሲቪል ሰርቪስ ሴክተሩ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎ መቆየቱን ገልጸዋል። ይሁንና አዋጁ ይህን የሠራተኛውን ጥቅም የሚያስከብርና ብቃትንም የሚያበረታታ ነው ብለዋል።

አዋጁ፣ ኢትዮጵያን የሚመስል የመንግሥት ሠራተኞች ስብጥር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑንና ለሴት ሠራተኞች የሚጠበቁ የሥራ ሁኔታዎች በማመቻቸት ረገድ ሚናውን የሚወጣ እንደሆነ አስረድተዋል። ለአካል ጉዳተኞች የሚጠበቁ የሥራ ሁኔታዎችንም የሚያገናዝብ እንደሆነ ገልጸዋል።

## ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መለያየት የሰፈነበት ከመተባበር ይልቅ መጠላለፍ በስፋት የሚታይበት መሆኑን ገልጸዋል።

እነዚህ አሉታዊ መስተጋብሮች በማህበረሰቡ ያለውን መተማመንና አብሮነት የሚያፈርሱ፣ የሀገሪቱን እድገት ወደኋላ የሚጎትቱ በመሆኑ፤ ከግጭት፣ ከጥላቻ፣ ከቂምና በቀል፣ ከመለያየት እና ከግጭት በመራቅ ሰላምን ማስፈን ከሁላችንም ይጠበቅብናል ብለዋል።

ከግጭት ወደ ውይይት፣ ከቂምና ጥላቻ ወደ ሰላምና ፍቅር በመመለስ የጋራ መኖሪያችን የሆነችውን ኢትዮጵያን በአንድነትና በመተባበር እንጠብቅ ሲሉ ተናግረዋል።

ከተባበርን የማንሻገረው ነገር የለም፤ ያቀድነውን እንተገብራለን፤ ያለምነውን እናሳካለን፤ ሰላማችን የበዛና የተትረፈረፈ ይሆናል ሲሉ ጨምረው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ የሃይማኖት አባቶች ለሀገር ሰላም፣ ለሕዝብ አንድነት ለመጸለይ አንድም ቀን እንደማይታክቱ አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል የተቸገሩትን መርዳት የአምላክን ትዕዛዝ መጠበቅ በመሆኑ በመቄዶኒያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የሚገኙ ወገኖችን መርዳትና ከጎናቸው መቆም እንደሚገባ ተናግረዋል።

የመቄዶንያ በጎ አድራጎት ማህበር ከመቄዶኒያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል መስራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ በበኩላቸው፤የሃይማኖት አባቶች በቦታው ተገኝተው ላደረጉላቸው የጸሎትና ጉብኝት መርሀ ግብርን አመስግነዋል።

መቄዶንያ ከስምንት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ድጋፍ እያደረገ ያለ ማዕከል መሆኑን ገልጸው፤ ሁሉም ሰዎች ለማዕከሉ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**ከኢትዮጵያ ደን ልማት**
**ጋር በመተባበር በየ15ቀኑ የሚታተም**


# በደን ሀብት የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችና ምቹ ሁኔታዎች

**ሰላማዊት ውቤ**

ተፈጥሮ የራሷን ሥነ-ምህዳርና ደህንነት ከሚያስጠብቅላት የአረንጓዴ አካላት መካከል የደን ሀብት ትልቁን ሥፍራ የሚይዝ መሆኑ እሙን ነው። ስለሆነም ደን የብዝሀ-ሕይወት መሠረት እና ሁሉን አቀፍ ሀብት ነው ማለት ይቻላል። ደን ውስጥ ከደቂቅ አካላት(ፈንገሶች፣ ጀርሞች) እስከ ግዙፍ አጥቢ እንስሳትና አዕዋፋት ድረስ መጠለያ ሆኖ በማገልገል፣ የእንስሳት ዝርያዎቻቸውን ተከተው ትውልዳቸውን እንዲያቀጥሉ፣ እንስሳዊ መስተጋብርን በመተግበር ምድር ሚዛኗን ጠብቃ እንድትቀጥል በማስቻል፣ የተለያዩ ዝርያና ባህሪ ያላቸውን እንስሳት አቅፎ በመያዝ፣ የምግብ ሰንሰለት ተፈጥሯዊ ሂደቱን ጠብቆ እንዲቀጥል በማስቻል የደን ሀብት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በሌላ በኩል ስለ ድርቅና በረሃማነት ስናስብ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው የደን መመንጠር፣ ቃጠሎና መመናመን ነው። ምክንያቱም ደን ውሃ ነው፤ ደን ንፁህ አየር ነው፤ ደን እፅዋትም እንስሳትም ነው፤ ደን መጠለያ ነው፤ ደን አንዱን ለሌላው ጠብቆ የሚያቆይ፣ አቆይቶ የሚለግስ የሕይወት ባንክ፣ ማህደር ነው፤ ደን መዝናኛና ተፈጥሮን የምንናደንቅበት ነው፤ በአጠቃላይ ደን ለሰው ልጆች ሕይወት ለማያቋርጥ የዘመናት ፍሰት፣ ምድራዊ ፋይዳው መጠነ- ሰፊ ነው። ከኢኮኖሚ ጠቀሜታው ባሻገር ለማህበራዊ እሴቶች እድገት ሁነኛ ሚና የሚጫወት ትልቅ ሀብት ነው።

ይህን የተረዳው የኢትዮጵያ መንግሥት የደን



**አቶ ዘሪሁን ላቀው፤**

ሀብቱን በማልማትና በመጠበቅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲያስገኝ በዘርፉ ሰፊ የሥራ ዕድል በሚፈጠርበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። በ2017 በጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በደኑ ዘርፍ ስለተፈጠረው የሥራ ዕድልን በተመለከተ በኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ውጤቶች ንግድ ማብቃት ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ዴስክ ባለሙያ አቶ ዘሪሁን ላቀው መረጃ ሰጥተውናል።

ባለሙያው አቶ ዘሪሁን እንደጠቀሱት በ2017 በጀት ዓመት አንደኛ ሩብ ዓመት ብቻ በኢትዮጵያ ደን ልማት ዘርፍ ለ35 ሺህ 205 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል። የሥራ ዕድሎቹ የተፈጠሩት በደን ጥበቃ፤ በደን ምርት መጨንና ማውረድ፤ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፣ በኢንተርፕራይዞችና ኢንዱስትሪዎች በእንጨት ማቀነባበሪያ ተቀጥሮ በመሥራት፣ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፤ ወደ ውጭ በመላክና በችርቻሮ ሀገር ውስጥ በመሸጥ እና በከሰል ማክሰል የሥራ ዘርፎች ነው።

በእነዚህ የደን ልማቱ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው መካከል 27 ሺህ 179 ወንዶች ሲሆኑ 8 ሺህ 26 ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን ባለሙያው አስረድተዋል።

እንደባለሙያው ገለፃ የሥራ ዕድሉን መፍጠር የተቻለው በኢትዮጵያ ደን ልማት ተቋም አስቀድሞ በተፈጠሩት ምቹ ሁኔታዎች በመፈጠራቸው ነው። ከተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች መካከል ደግሞ ከዘርፉ ሕጋዊነት ጋር ተያይዞ የተሠሩት ሥራዎች ይጠቀሳሉ።

ባለሙያው እንደሚሉት የዘርፉ አዋጅ 542 በ1999 ዓ.ም የወጣ ሲሆን አዋጁ የደን ባለቤትነትን የሰጠው ለግለሰብና ለመንግሥት ነበር። ከዚህ በኋላ በ2010 ዓ.ም 1065 የሚባለው የደን አዋጅ ተሻሽሎ ወጥቷል። ይህ አዋጅ የደን ባለቤትነት የግለሰብ፤ የማህበራት፤ የማህበረሰብና የመንግሥት በሚል ባለቤትነትን ወደ አራት ከፍ እንዲል አድርጓል። ይህም ግለሰቦችና ማህበራት ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደግሞ 2016 ዓ.ም 544 የተሰኘ ደንብ የወጣለት ስለመሆኑ አቶ ዘሪሁን ያስረዳሉ።

አቶ ዘሪሁን እንደሚገልፁት ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ህጋዊነት ላይ ለነበረው የአሠራር ክፍተት ምላሽ የሰጠ ነው። የማህበራትና የመንግሥት ደን እንዴት እንጠቀማለን፤ እንዴት እናለማለን፤ ምን ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ በዝርዝር ያስቀመጠ ነው። ብዙ በግል ሊሰማሩ የሚችሉ ሰዎችን የሚያበረታቱ ማሕቀፎችንም በውስጡ አካትቷል። ደኖች በመጠበቅና በማልማት ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲውሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። እንደ ኢትዮጵያ ደን ልማትም ሆነ እንደ ሀገር አዋጁን መሠረት በማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በዚህ ረገድ የደን ተከላ፣ የደን እንክብካቤ ሥራዎችና የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ተግባራት በማሳያነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ባለሙያው እንደሚያስረዱት የተተከለውን ደን ለምርት አድርሶ እንደገና ወደ ምርት እንዲገባ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልገዋል። ይህ የሚደረገው የደን ሀብቱን ውጤታማ ከማድረግ ጎን ለጎን ከዘርፉ ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ነው። ሀገርም በኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን ስለሚገባት በዴስኩ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ደን ወደ ምርት ገብቶ ኢኮኖሚ አመንጪ መሆን አለበት። ምርታማ የሆኑ ደኖቻችንና እንክብካቤያቸውን በማሻሻል ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ማስፈለጉ ታምኖበት እየተሠራ ነው።

የኢትዮጵያ ደን ልማት የደን ውጤቶች ንግድ ማብቃት ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ዴስክ እንደ ሀገር ይህን መሠረት አድርጎ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ዴስኩ የደን አመራረት ሂደትን ይከታተላል፤ ደኖች ወደ አጠቃቀም እንዲገቡ ሥርዓቶችን ያስተካክልና ያዘጋጃል። የፋብሪካ ቁጥሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞም ድጋፍና ክትትሎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። ወደ ውጭ የሚላኩ በደን ውጤቶች ምርቶችን የሚያመርቱ ፋብሪካዎችን የቁጥጥርና ክትትል ሥራ ይሠራል። ከደን ውጤቶች ጋር በተያያዘ ወደ ንግዱ ዓለም ለሚገቡ የሕብረተሰብ ክፍሎች የብቃት ማረጋገጫ ድጋፍ ይሰጣል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በግብርናው ዘርፍ የታዩ ስኬቶች የኢትዮጵያን ብልፅግና አይቀሬነት የሚያረጋግጡ ናቸው!

በዚህ በያዝነው ዓመት ኢትዮጵያ 8 ነጥብ 4 በመቶ እድገት ለማስመዝገብ ጠበቅ ያለ እቅድ ይዛለች። ለዚህ ዕቅድ መነሻ ደግሞ በግብርናው ዘርፍ እየታየ ያለው ምርታማነት ተጠቃሽ ነው፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም ግብርናው የ6 ነጥብ 1 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ይጠበቃል፡፡ ክረምት ከበጋ ሰላሳ ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማረስ 1ነጥብ4 ቢሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብም ዕቅድ ተይዟል፡፡

ከዚህ ቀደም በነበረው ሁኔታ ከ15 ሚሊዮን ሄክታር የዘለለ መሬት ታርሶ አያውቅም፡፡ የሚገኘውም ምርት ከ600 ሚሊዮን ኩንታል ብዙም የዘለለ አይደለም፡፡ ዘንድሮ የታቀደው ዕቅድ ግን በሀገሪቱ ታሪክ ታቅዶ የማያውቅ እና ከፍተኛ የሆነ ጥረትንም የሚጠይቅ ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሊሳካ እንደሚችል የሚያመላክቱ ውጤቶች ከወዲሁ እየተገኙ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ በመኸር አዝመራ 20 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላይ በዘር መሸፈኗን እና አፋርን የመሳሰሉ ከዚህ ቀደም በጤፍ ምርት የማይታወቁ አካባቢዎች በከፍተኛ ሁኔታ ምርታማ መሆን መጀመራቸው ግብርናው እየሄደበት ያለውን ግስጋሴ የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

ጤፍ በርካታ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ የሚመገበው እና አብዛኛውን የእርሻ መሬት የሚሸፍን ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት ይሄ ነው የሚባል የምርት ዕድገት ሳያሳይ ቆይቷል፡፡ የለውጡ መንግሥት እውን እስከ ሆነበት ጊዜ ድረስ በአጠቃላይ የነበረው ዓመታዊ ምርት ከ300 ሚሊዮን ኩንታል ብዙም የዘለለ አልነበረም፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ጤፍን በክላስተር ማረስ በመቻሉ ምርቱ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ዓመታዊ ምርቱ 639 ሚሊዮን ኩንታል ሊደርስ ችሏል፡፡ ዘንድሮ ይህንን ምርት ወደ 800 ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ የግብዓት እና የሙያ ድጋፎች እየተደረጉ ነው፡፡ በተለይም ማዳበሪያ ቀደም ብሎ አርሶ አደሩ ጋር መድረሱ የተቀመጠውን ዕቅድ ለማሳካት በእጅጉ እንደሚረዳው ይታመናል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ስንዴ ሸማች ከሆኑ ሀገራት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የምትታወቅ ሀገር ነበረች፡፡ በየዓመቱም እስከ 107 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በማስገባት 1 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ስትገፈግፍ ኖራለች፡፡ ሆኖም ባለፉት ዓመታት መንግሥት ለስንዴ ምርት በሰጠው ትኩረትም ኢትዮጵያ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ከማቆሟም ባሻገር ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች፡፡ ይህ ጥረቷም በዓለም ላይ ስንዴ በማምረት ተጠቃሽ ከሆኑ 18 ሀገራት ተርታ አሰልፏታል ፡፡ በአፍሪካም የቀዳሚነቱን ቦታ ተቀዳጅታለች፡፡ ዘንድሮም የስንዴ ምርቱ እመርታዊ ለውጥ አሳይቶ ሶስት መቶ ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት ዕቅድ ተይዟል፡፡

የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ከ35-40 በመቶ የሚሸፍነው ቡናም ምርታማነቱ ጨምሯል፡፡ 500ሺ ቶን የነበረው ዓመታዊ ምርትን ወደ 800 ሺህ ቶን ማሳደግ ተችሏል፡፡ በዚህም 700 ሚሊዮን ዶላር የነበረው ዓመታዊ የወጪ ንግድ ገቢ ወደ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ ችሏል፡፡ የሻይና ቅመማ ቅመም ዘርፍን ምርታማነት ማሳደግ በመቻሉ ለሀገሪቱ እስከ 20 ሚሊዮን ዶላር የማምጣት አቅም ላይ ደርሷል፡፡

በቡና የተገኘውም ውጤት የኢትዮጵያ መጻኢ ጊዜ ብሩህ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከብራዚልና ከቬየትናም ቀጥሎ ሦስተኛዋ ትልቅ ቡና አምራች ሀገር ለመሆን በቅታለች። በዚህ ዓመት ሁለት ቢሊዮን ዶላር ገደማ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ የግብርናው ዘርፍ በውጤቶች እየታጀበ ለኢትዮጵያ ብልፅግና መሰረት በመጣል ላይ ይገኛል፡፡ የሀገሪቱን መልክዓ-ምድርና የአየር ጸባይን መሰረት ያደረጉ ሥራዎች በመሰራታቸው ጤፍን የመሳሰሉ ምርቶች ምርታማነት ከመጨመሩም ባሻገር ኢትዮጵያ በታሪኳ በበቂ ሁኔታ አምርታቸው የማታውቃቸው የበጋ ስንዴና ሩዝን የመሳሰሉ ሰብሎች ከራስ ፍጆታ አልፈው ለውጭ ገበያም ለመቅረብ ችለዋል፡፡

በአጠቃላይ በግብርናው ዘርፍ ያለው መሻሻል ስንዴን፤ሩዝንና አቦካዶን የመሳሰሉ ምርቶችን ከሀገር ውስጥ አልፎ ለውጭ ገበያም እንዲቀርብ ያደረገ ነው፡፡ ቀደም ሲል ይላክ የነበረውንም የቡና መጠን እና ጥራት በመጨመርም በዓለም ላይ ተፈላጊ እንዲሆንም በር ከፍቷል፡፡ ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ በምግብ ሰብል ራሷን ከመቻል አልፋ ወደ ሁለንተናዊ ብልፅግና የምታደርገው ጉዞ አይቀሬ መሆኑን የሚያመላክት ነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በትግራይ ሰላምን ለማጽናት የተጀመረው ታጣቂዎችን ትጥቅ የማስፈታት ሥራ

ግርማ መንግሥቴ

መቼም "ፕሪቶሪያ" የሚለው ቃል (ስያሜ) ሲነሳ ማንም ምራቁን የዋጠ ሰው ልብ እንደሚለው፤ በተለይ ለእኛ፣ ለኢትዮጵያውያን አንድ ራሱን የቻለ፤ ወደድንም ጠላንም የወደፊት ታሪካችን አካል የሆነ አስከፊ ክስተት ወደ አእምሯችን ጓዳ ዘው ብሎ የመግባቱ ነገር ሳይታለም የተፈታ ነው።

በተለይ ከጉዳዩ የቅርብ ጊዜነትና በፍፁም አይረሴነት አኳያ "ፕሪቶሪያ" እና "ስምምነቱ" (አንድ ላይ "የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት") ጉዳይ በማንኛችንም ዘንድ ተገቢውን ታሪካዊ ስፍራ ይዞ ስለመኖሩ እማኝ መጥራት አያስፈልግም።

ክስተቱ በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተካሄደው ጦርነት ነው።ጦርነቱ እጅግ ዘግናኝ ሀገር እና ሕዝብን አላስፈላጊ ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈለ ነው፤ መቼም መቼም ሊደገም የማይገባው፣ ሰብአዊ ፍጡር ሁሉ ሊማርበትና በሩቁ ሊርቀው የሚገባ፣ 21ኛውን ክፍለ ዘመን የማይመጥን ነው።

ክስተቱ ከዲሞክራሲ ሥርዓትና ወግ የተጣላ፣ ክቡር ለሆነው የሰው ልጅ ኢምንት ያህል ዋጋን እንኳን ያልሰጠ፣ የኖረ አብሮነትን ከስሩ ለመናድ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ የጣረ ፣ ያለችንን ሁሉ አውድሞ በድህነት ላይ ሌላ የከፋ ድህነትን ያፈራ … ወዘተርፈ እንደነበር ለማንም ግልፅ ነው። ዛሬ ላይ ሆነው ሁሉም ወገኖች (ተዋናይና ፊት መሪ የነበሩትን ጨምሮ) ድርጊቱ ፍፁም ስህተት እንደነበር እየተናገሩት ያለ መራር እውነት ነው።

ይህ መጨረሻውን በደቡብ አፍሪካ "የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት" ያደረገ (ጥቅምት 23/2015 ዓ.ም ደቡብ አፍሪካ ውስጥ በኢትዮጵያ መንግሥት እና በሕወሓት መካከል የተደረገ) የጦርነት ክስተት "የተደመደመው" ከእልህ አስጨራሽ ውይይት በኋላ ነው።

በተባበሩት መንግሥታት ድጋፍ፣ በአፍሪካ ኅብረት አሸማጋይነት እና በናይጄሪያው የቀድሞ ፕሬዚዳንት ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ መሪነት የተደረሰው የፕሪቶሪያው ስምምነት የተለያየ መልክ እና የተደበላለቀ ስሜት ይዞ ለአንድ ዓመት ከርሟል።

ስምምነቱ ለመላው ሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላ ቀጣናውና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያስገኘው እረፍት፣ ተስፋና በሰላም አብሮ የመኖር ህልም እዚህ በቃላት ሊገለፅ የሚችል አልነበረም፤ ወይም ልንገልጸው የምንችለው አይደለም። ባጭሩ፣ ፀረ-ጦርነት አቋም ያላቸውን ወገኖች ሁሉ "እፎይ!!!" አሰኝቷል።

> **ስምምነቱ ለመላው ሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላ ቀጣናውና ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያስገኘው እረፍት፣ ተስፋና በሰላም አብሮ የመኖር ህልም እዚህ በቃላት ሊገለፅ የሚችል አልነበረም፤ ወይም ልንገልጸው የምንችለው አይደለም፡፡ ባጭሩ፣ ፀረ-ጦርነት አቋም ያላቸውን ወገኖች ሁሉ "እፎይ!!!" አሰኝቷል**

እፎይ ብቻ አይደለም፣ ከስምምነቱ በኋላ በክልሉ እና በፌዴራል መንግሥት መካከል መደበኛ ግንኙነት ተጀምሮ ጊዜያዊ አስተዳደር ተቋቋሞ፤ ለረጅም ጊዜ ተቋርጠው የነበሩት የስልክ፣ የባንክ እና የመብራት አገልግሎቶች በሂደት ሥራቸውን ጀምረዋል፤ ሌሎች ተግባራትም እንደዛው። ከሁሉም በላይ በክልሉ ጦርነት እና የጦርነት ወሬ ሳይሰማ አንድ ዓመት ተቆጥሯል።

ከዛስ? በራሱ በሕወሓት መካከል የተፈጠሩ፣ ሰላም የማይሰጡ፣ ከጦርነት ያልተናነሱ ውዝግቦች በስፍራው ተተክተዋል። ሁኔታውን በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ መብት እና የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁር ረዳት ፕሮፌሰር መኮንን ፍስሃ፤ "ጦርነት በድሮን እና በሚሳይል ብቻ አይደለም፤ ሰላም ማለት የሰው ልጅ አእምሮ ነፃ ሆኖ ብዙ ሰዎች በሰላም ወጥተው በሰላም ሲገቡ እና ወደ ተለመደው ኑሯቸው ሲመለሱ ነው። በተግባር ግን የትግራይ ሕዝብ የቀጥታ ጦርነት ቀረለት እንጂ አሁንም መከራ ውስጥ ነው ያለው" ሲሉ ገልጸውታል።

የትግራይ ብሔራዊ ምክር ቤት ሊቀመንበር አቶ ክብሮም በርሄ ከቢቢሲ ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ "በስምምነቱ አተገባበር የሚሰማኝ ነገር የተደበላለቀ ነገር ነው። የሰላም ተስፋ ነው። በሌላ በኩል፣ የቀረው ተኩሱ ወይም ውጊያው ነው እንጂ ጦርነቱ እንደቀጠለ ነው" በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በርግጥ ስምምነቱ ፀረ-ጦርነት አቋም ያለውንና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ (በተለይ የአካባቢውን ምስኪን ሕዝብ) እልል ያሰኘው ያለ ምክንያት ሳይሆን፣ ስምምነቱ ሁለቱ ወገኖች ባለ 12 ነጥብ የሰላም ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ ተኩስ በቋሚነት እንደሚቆምና ሁሉም ነገር ወደ ነበረበት ሰላማዊ ሁኔታ ይመለስ ዘንድ አስገዳጅ በመሆኑ ነው።

በጦርነቱ ወቅት በሺዎች የሚቆጠሩ ለሞት እና ለአካል ጉዳተኝነት ተዳርገዋል። ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ነዋሪዎችም ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለከፋ ችግር ተጋልጠዋል፤ በረሃብ እና በመድኃኒት እጦት ችግር ለአደጋ የተጋለጡ ዜጎችም ቁጥር ትንሽ የሚባል እንዳልሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በክልሉ የሚስተዋሉ አሁናዊ ችግሮች ፀረ-ጦርነት አቋም ያለውንና ሰላም ወዳዱን ሕዝብ እየረበሸው፣ እየፈተነውና ለቀቢፀ-ተስፋነት እየዳረገው ቢሆንም፤ ዛሬ ላይ ይህ ሕዝብ የትዕግስቱን፣ የፀሎቱን፣ የምኞቱንና የፍላጎቱን ፍሬ ያይ ዘንድ ሊያበቃው የሚችል ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፤ ትጥቅን በሰላም አስረክቦ ወደ መደበኛ ሕይወት የመመለስ ሰብአዊ ተግባር።

አስከፊውን ጦርነት ከተመለከቱና እስከ ዛሬም ብዙ ሲነገርላቸው ከነበሩት ርዕሰ ጉዳዮች ሁሉ የበለጠ ጆሮ ገብ የሆነው የሰሞኑ የሕወሓት ታጋዮች ከጦርነቱ መልስ፤ በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ትጥቃቸውን ለመከላከያ ሠራዊት እያስረከቡ ወደ ሰላማዊ ሕይወታቸው እየተመለሱ የመሆናቸው ጉዳይ ነው።

እርግጥ ባለ 12 አንቀፁ የፕሪቶሪያው ስምምነት የሕወሓት ሠራዊትን ትጥቅ መፍታትን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የሕዝቡን መሰረታዊ ጉዳዮች ማለትም ጦርነቱን ከማስቆም ባለፈ የዜጎች ደኅንነት እንዲረጋገጥ፣ መልሶ ግንባታ እንዲካሄድ፣ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ...ወዘተ የሚሉ ጉዳዮችን ያካተተ ነው።

አሁን እየተካሄደ ያለው የትግራይ ታጣቂ ኃይሎችን ትጥቅ የማስፈታት ሥራ በፕሪቶሪያው ስምምነት ሰነድ ውስጥ በዋነኛው የተቀመጠ ነው፤ በክልሉ ሆነ በአጠቃላይ በአካባቢው ሰላም እና መረጋጋት በመፍጠር ሂደት ውስጥም ትልቅ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

በዚሁ መሠረትም (ቢዘገይም) እየተከናወነና ትጥቃቸውን እየፈቱ ያሉት የቀድሞ ተዋጊዎች ወደ ሰላማዊ ህይወታቸው የሚመለሱበትን የተሀድሶ ስልጠና ይወስዳሉ፤ ይህም የተሟላ ሰላምና ፀጥታ በክልሉ እንዲሰፍን በጎ ህሊና እና የተግባር ቁርጠኝነት ላላቸው ኃይሎችም ተገቢውን ምላሽ መስጠት እንዲችሉ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል።

ፖስቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# የእግር ኳሳችን ችግር ፈርጀ ብዙ ነው!

**ልዑል ከካምቦሎጆ**

እንደ ሀገር እጅግ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚፈስበት እግር ኳሳችን ከሚንቀሳቀሰው ገንዘብ በዘለለ ሌላ ትኩረትን የሚስብ አዎንታዊ ርዕሰ ዜና መፍጠር ከተሳነው ዓመታት ተቆጥረዋል:: ይባስ ብሎም የእግር ኳሳችን ዓይነተኛ ነፀብራቅ የሆነው ብሔራዊ ቡድናችን በፉክክር ጨዋታዎች ለመጨረሻ ጊዜ ሰኔ 2/2014 ግብጽን ሁለት ለባዶ ከረታ በኋላ ዳግም ወደ ድል ለመመለስ 893 ቀናት ፈጅተውበታል።

ብሔራዊ ቡድናችን(ዋልያዎቹ) በቅርቡ በ2025 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ የመጨረሻ ጨዋታ ዲሞክራቲክ ኮንጎን 2ለ1 እስከረታበት ፍልሚያ ድረስ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ 17 የነጥብ ጨዋታዎችን ቢያደርግም ማሸነፍ የቻለው ይህን የመጨረሻ ፍልሚያውን ብቻ ነው። በእነዚህ አስራ ሰባት ጨዋታዎች ቡድኑ ሰባት ግቦችን ሲያስቆጥር በተቃራኒ ሃያ ስድስት ግቦች ተቆጥረውበታል።

የሀገር ውስጥ እግር ኳስ ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚሰራው ድሬ-ገፅ ሶከር ኢትዮጵያ በቅርቡ ባደረገው እና በርካታ የእግር ኳስ ቤተሰቡ በተሳተፈበት የሕዝብ መጠይቅ ከወቅታዊ የብሔራዊ ቡድኑ የውጤት አልባ ጉዞ በስተጀርባ አለ ስለሚሉት ምክንያት ባቀረበው የሕዝብ መጠይቅ 68% የሚሆኑት ምላሽ ሰጪዎች አሁናዊው የብሔራዊ ቡድኑ ውጤት ማጣት የአጠቃላይ የሀገራችን እግር ኳስ ነፀብራቅ ስለመሆኑ ሃሳባቸውን ሲሰጡ፣ ከምላሽ ሰጪዎቹ 28% የሚሆኑት ደግሞ ለቡድኑ ውጤት ማጣት ምክንያት ነው ብለው ያነሱት ጉዳይ የተጫዋቾች ብቃት ማነስን ሲሆን 18% ደግሞ በሜዳችን ያለመጫወታችን ለውጤት ማጣቱ እንደ ምክንያትነት ይቀርባል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። የተቀሩት 6% የሚሆኑ ድምፅ ሰጪዎች ደግሞ ከውጤት መጥፋቱ በስተጀርባ ሌላ ምክንያት ስለመኖሩ ጠቁመዋል።

ርግጥ እግር ኳሳችን ፈርጀ ብዙ በሆነ የሜዳ እና የሜዳ ውጭ ጉዳዮች የታሰረ መሆኑ የአደባባይ ሀቅ ነው። የተሰበሰበው የሕዝብ መጠይቅም እነዚህ ስር የሰደዱ የእግር ኳሳችን ችግሮች ተፅዕኗቸው በሁለንተናዊ የእግር ኳሳችን መልክ ላይ ስለማረፉ ዓይነተኛ ማስረጃ ነው።

የአሉታዊ ተፅዕኖ ደረጃቸው የሚለያይ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች የብሔራዊ ቡድኑ ተግዳሮቶች መሆናቸው ነጋሪ አያስፈልገውም። ሆኖም አጠቃላይ የሀገራችን እግር ኳስ ሁኔታ ለውጤት መጥፋቱ ዋነኛ ምክንያት መሆኑ እሙን ነው። ችግሩ ከክለቦች ውጤት ተኮር፣ ራዕይ አልባ ጉዞ እና ደካማ አደረጃጀት እንዲሁም በአጠቃላይ በሀገሪቱ በተለያዩ ደረጃዎች የሚታየው የእግር ኳስ አስተዳደር መዋቅራዊ የተቋማት ችግር የመነጨ ነው። አንድ ሀገርን የሚወክል ብሔራዊ ቡድን የክለቦች ነፀብራቅ ነው። በክለቦች አደረጃጀት ላይ ስር ነቀል ለውጥ ማድረግም እግር ኳሱን የሚያድነው ቀዳሚ ተግባር ነው። ሆኖም የክለቦቹን አሁናዊ ሁኔታ ሂደቱ የተወሳሰበ ያደርገዋል፤ የክለቦቹ አካሄድ ከታመመ ሰንበትበት ቢልም በተለይም ቅጥ ያጣው የገንዘብ አወጣጥ መንገዳቸው ከመንገዳገድ አልፎ ጠልፎ እንዳይጥላቸው ያሰጋል። ለዚህም የከሸፈውን የቻይና የእግር ኳስ አብዮት መለስ ብሎ መመልከት ተገቢና ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡

ባለፉት ቅርብ ዓመታት በቻይና የተነሳው የእግር ኳስ አብዮት የዓለምን ትኩረት ስቦ ነበር። የሩቅ ምስራቋ ሀገር ቻይና ሱፐር ሊጓን የዓለም ከዋክብት ተጫዋቾች መገኛና የድንቅ የእግር ኳስ መናኸሪያ የመሆን ውጥን ይዛ ነበር የተነሳችው። ሀገሪቷ ይህን ውጥኗን እውን ለማድረግ ከስምንት መቶ ቢሊየን ዶላር በላይ ለስፖርቱ ኢንዱስትሪ አፍስሳለች፡፡

እግር ኳስን በእጅጉ እንደሚወዱ የሚነገርላቸው በሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ዢ ጂፒንግ ድጋፍ ፤ ቻይና የዓለማችን ታላላቅ ከዋክብትን በገንዘብ በማማለል ሊጓን የማጠናከር ሥራን "ሀ " ብላ ጀመረች። የዓለማችን ስመጥር ከዋክብት በቻይና ክለቦች ከፍተኛ የገንዘብ ክፍያ ወደ ሱፐር ሊጓ መትመም ጀመሩ። ከነዚህም መካከል ብራዚላዊው ኦስካር ፣ አርጀንቲናዊው ካርሎስ ቴቬዝ እና ቤልጂዬማዊው አክስል ቪትዝል ይገኙበታል። የነዚህ ተጫዋቾች ሊጉን መቀላቀል ለሌሎች ታላላቅ ተጫዋቾች መምጣት ምክንያት ሲሆኑ ጊዜ አልወሰደም። በ2016 በቻይና የፈነዳው ይህ የእግር ኳስ አብዮት በአውሮፓ እግር ኳስ ላይም ትልቅ ስጋት እስከመደቀን ደርሶም ነበር።

የሱፐር ሊጉ እንቅስቃሴ ጠንካራ ወደሚባል ደረጃ መድረስ ቢችልም ፤ የእግር ኳስ አብዮቱ የታሰበውን ግብ መምታት እንደማይችል ምልክቶች መታየት ጀመሩ። አንዳንድ ክለቦች በዕዳ ውስጥ የመዘፈቃቸው ዜና ይሰማ ጀመር። እአአ በ2017 የቻይና ስፖርት ሚኒስቴር የሊጉን ወጪን በተመለከተ ጥያቄ ማንሳት ጀመረ። ወጪዎችን ለመግታት እና "ምክንያታዊ ያልሆነ ኢንቨስትመንት" ለመቆጣጠር እንቅስቃሴ ጀመረ። ክለቦች "ገንዘብ ያባክናሉ" እና ለውጭ ተጫዋቾች "ከልክ በላይ ደመወዝ" ይከፍላሉ ሲል ወደ መክሰስ ተሻገረ። በዚህ ፈታኝ መንገድ ውስጥም ቢሆን በ2019 ሱፐር ሊጉ በጣም ትልቅ ደረጃ ላይ ደረሰ።

ያም ሆኖ በብዙ የተጠበቀው የቻይና እግር ኳስ አብዮት አስር ዓመት ሳይሞላው ጉዞው በተቃራኒው አቅጣጫ ሆኖ ተስፋው መፈረካከስ ጀመረ። የቻይና ክለቦች ተጫዋቾችን ወደ ቻይና ሱፐር ሊግ ለመሳብ በሚል ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ቢከፍሉም ፤ ትርፋማ መሆን አልቻሉም። ቻይና የጀመረችው መንገድ የተሳሳተ መሆኑን የተረዳችው ግን ዘግይታ ነበር።

የእኛም ሀገር ክለቦች እጣ ፋንታ ከዚህ የተለየ እንደማይሆን ምልክቶች መታየት የጀመሩት ዛሬ አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ፈር የሳተውን አካሄድ ለማስተካከል አሁንም እድሉ ዝግ አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ክለቦች ለተጫዋቾች የሚከፍሉት ደመወዝ በአፍሪካ ትልቅ ከሚባሉት ቀዳሚ ደረጃዎች ውስጥ ቢመደብም የተጫዋቾች ብቃት እዚህ ግባ የሚባል እንዳልሆነ በየእለቱ የምናየው ነው፡፡ ብሔራዊ ቡድኑ ላይ የሚታየውም ችግር የዚሁ ነፀብራቅ ነው፡፡ በሶከር ኢትዮጵያ መጠይቅ ላይ ምላሽ ከሰጡ 28% የሚሆኑት ለብሔራዊ ቡድኑ ውጤት ማጣት ምክንያት ነው ብለው ያነሱት የተጫዋቾች ብቃት ማነስ ሌላው የብሔራዊ ቡድኑ ተግዳሮት የሆነውም ለዚህ ነው።

እዚህ ላይ አሰልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ በብሔራዊ ቡድን አሰልጣኝነት መንበር በቆዩባቸው ጊዜያት በጋዜጣዊ መግለጫዎች ላይ ካነሷቸው አንኳር ሃሳቦች መካከል በየሳምንቱ የተለያየ የብቃት ደረጃ ላይ ስለሚገኙት ተጫዋቾቻችን የገለፁት እንደ ማሳያነት ማንሳት ይቻላል።

አሰልጣኙ ደጋግመው እንደተናገሩት ተጫዋቾቻችን "በትንሽ ጭብጨባ" ከመንገድ ይስታሉ። የተጫዋቾቻችን የብቃት እንዲሁም የወጥነት ችግር ለማጠናከር የሶከር ኢትዮጵያን የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ የጨዋታ ሳምንቱን ምርጥ ቡድን መመልከት ዓይነተኛ ምስልን ይፈጥራል። በቀናት ልዩነት በሚደረገው በዚህ ምርጫ በተከታታይ ሳምንታት በወጥነት የሚመረጡ ተጫዋቾችን ማግኘት እምብዛም የተለመደ አይደለም።

ታዲያ ይህ ጉዳይ የእግር ኳሳችን ሀቅ በሆነበት የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞች በእዚህ የተጫዋቾች ብቃት የወጥነት ችግር እና መውጣት መውረድ ውስጥ ሆነው ተጫዋቾችን እንዴት ባለ ሁኔታ ይመርጣሉ የሚለው ጉዳይ ሌላው መፍትሔ የሚሻ ጉዳይ ነው።

ሌላኛው ምክንያት በሜዳችን ያለመጫወታችን ጉዳይ ነው፡፡ እግር ኳሳችን ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚንቀሳቀስበት ቢሆንም ይህ የገንዘብ ፍሰት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዛሬ ላይ ያተኮሩ ወይም ተቋም የማይገነቡ እና በእቅድ የማይመሩ ወጪዎች መሆናቸው የእግር ኳሳችን መሠረተ ልማት ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ፈቀቅ እንዳይል ምክንያት ሲሆን እየተመለከትን እንገኛለን። እግር ኳሳችን በቢሊዮኖች የሚገመት በጀት የሚንቀሳቀስበት ቢሆንም በዘርፉ ያለው ስር የሰደደ ሙስና እና የገንዘብ አጠቃቀም ችግር በመሠረተ ልማት ላይ በቂ የሆነ ኢንቨስትመንት እንዳይደረግ ምክንያት ሆኗል። በዋነኝነት በልማት እና የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ግንባታ ላይ መዋል የነበረበት ገንዘብ በጊዜያዊ እና ራዕይ የሌለው የበጀት አጠቃቀም ድክመት ምክንያት ብሔራዊ ቡድኑ ለስደት ከመዳረጉ ባለፈ የፌዴሬሽኑን ካዝና አራቁቶታል። ለዚህም የፌዴሬሽኑ የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሰሞኑን በአንድ የቴሌቪዥን የምርመራ ዘገባ ላይ የተናገሩትን ማስታወስ በቂ ማሳያ ነው። ብሔራዊ ቡድኑ በሜዳው ማድረግ የነበረበት ጨዋታዎች በሌሎች ሀገራት ባደረገባቸው ባለፉት አራት ዓመታት ፌዴሬሽኑ ማውጣት ያልነበረበትን ከ85 ሚሊየን ብር በላይ ለማውጣት እንደተገደደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ ጅራም በቅርቡ በአንድ የሬዲዮ መሰናዶ ላይ ለአብነት ሲገልፁ እንደተደመጡት፣ ብሔራዊ ቡድን በቅርቡ ታንዛኒያ ዳሬ ሰላም ላይ ላደረገው ጨዋታ ለሜዳ ኪራይ 20,000 ዶላር እንዲሁም ደቡብ አፍሪካ ላይ ላደረጉት ጨዋታም እንዲሁ 90,000 ራንድ ወጪ ማድረጋቸውን አንስተዋል።

ታዲያ አሁንም በስደተኝነቱ የቀጠለው ብሔራዊ ቡድናችን በሜዳው እና በደጋፊው ፊት ሲጫወት ያገኝ የነበረውን ተጠቃሚነት የማጣቱ ጉዳይ ምናልባት በቁጥራዊ መለኪያዎች መለካት ባይቻልም ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ የብሔራዊ ቡድናችንን የቅርብ ዓመታት ውጤቶች መመልከት በቂ ነው።

በሌላ በኩል ለውጤት መጥፋቱ አሰልጣኞችን ተጠያቂ ማድረጉም ተገቢ ነው፡፡ በአንድ ሀገር የእግር ኳስ እድገት የአሰልጣኞች ሚና ትልቅ ነው። አንጋፋው ኔዘርላንዳዊው አሰልጣኝ ሪኑስ ሚሸየልስ በ1970ዎቹ የኔዘርላንድን እግር ኳስ ገፅታ የቀየሩበት አብዮታዊ ለውጥ እንዲሁም ስኬታማው አሰልጣኝ አሪጎ ሳኪ የጣሊያንን እግር ኳስ ባሕል፣ የጨዋታ መንገድ እና የሥልጠና ዘዴዎች የለወጡበት መንገድ በጥልቀት ላስተዋለ የአሰልጣኞች ሚና ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግተውም። ይህንን በመንተራስ በጥቅሉ ስናየው በሀገራችን እግር ኳስ ውድቀት የአሰልጣኞች ድርሻም ቀላል እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል። አሰልጣኞች የደካማው የክለባችን አደረጃጀት ሰለባ መሆናቸው የማይታበል ሀቅ ቢሆንም ዘመኑን የዋጀ የሥልጠና እና የአጨዋወት መንገድ በማበጀት ረገድ ያላቸው ውስንነት በእግር ኳሱ እድገት አሉታዊ ተፅዕኖ አሳርፏል።

ይህ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ችግር በብሔራዊ ቡድኑ ውድቀትም የራሱ ድርሻ አለው። ከዚህ በተጨማሪ ብሔራዊ ቡድኑ በቅርብ ዓመታት በአንፃራዊነት የተሻለ ለኳስ ቁጥጥር ቅድሚያ ከሚሰጡ አሰልጣኞች ወደ ቀጥተኛ አጨዋወት የቀረበ የጨዋታ ዕቅድ ያላቸው አሰልጣኞች መሸጋገሩም ወጥነት ያለው እና የተቀናጀ አጨዋወት እንዳይኖረው እንዲሁም የውህደት ደረጃው እንዲዋዥቅ አድርጎታል።

እግር ኳሳችን በፈርጀ ብዙ ችግሮች የተተበተበ እንደመሆኑ ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት ሰፊ ጥናት እና ምርምር የሚጠይቅ የዓመታት ሥራ ቢሆንም የአብዛኞዎቹ ችግሮቹን መነሻ የሆነው እና የእግር ኳሱ ባለቤት የሆኑትን ክለቦች አደረጃጀት ላይ ስር ነቀል ለውጥ ማድረግ ግን ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ወሳኝ ተግባር ነው። ክለቦቹ በጥቂት ግለሰብ ላይ ጥገኛ የሆነ እና ተቋማዊ ባልሆነ አደረጃጀት መመራታቸውም በሜዳም ይሁን ከሜዳ ውጭ ያለውን የእግር ኳሱ ሁኔታ ክፉኛ ደቁሶታል። የአንድ ሀገር ብሔራዊ ቡድን ውጤታማነት ከክለቦች እድገት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ትስስር አለው። የክለቦቹ ኋላ ቀር አደረጃጀት ላይ ለውጥ ማድረግም የወጣት ተጫዋቾች እድገት ማሳለጥ፣ የምልመላ ሥርዓት ለማስተካከል፣ ለአሰልጣኞች ምቹ የሥራ ከባቢ መፍጠር እንዲሁም በክለቦቹ አሰራር የተጠያቂነት እና ፍትሐዊ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር ያስችላልና ትኩረት ይሰጠው።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የሀገራችንን እግር ኳስ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ የዝግጅት ሥራዎች ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠውን የ6 ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ በድጋሚ ለመከለስ ስላስፈለገ በስፖርቱ እና በስትራቴጂክ እቅድ ዙሪያ እውቀት እና ልምድ ያላቸው እንዲሁም በበጎ ፈቃድ ለማገልገል ፈቃደኛ የሆኑ ሁሉ ማመልከቻቸውን እና የሥራ ልምዳቸውን በማስገባት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አድርጓል፡፡ ይህ ባለሙያዎችንና እውቀቱ ያላቸውን ሰዎች ወደ ስፖርቱ ለማቅረብ የሚደረግ ጥረት የእግር ኳሱን ስንክሳሮች መልክ ለማስያዝ አበረታች ጅምር ነውና ሊበረታታ ይገባል፡፡

> **እግር ኳሳችን ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ የሚንቀሳቀስበት ቢሆንም ይህ የገንዘብ ፍሰት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዛሬ ላይ ያተኮሩ ወይም ተቋም የማይገነቡ እና በእቅድ የማይመሩ ወጪዎች መሆናቸው የእግር ኳሳችን መሠረተ ልማት ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ፈቀቅ እንዳይል ምክንያት ሲሆን እየተመለከትን እንገኛለን**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## አህጉራዊ ቅንጅት - ለአፍሪካ ቡና ተወዳዳሪነት

**ማህሌት አብዱል**



አፍሪካ የቡና መገኛና በስፋት የምታምርት እንደመሆኗ ከዘርፉ የሚገባትን ያህል ጥቅም እያገኘች አለመሆኗን የዘርፉ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ በርካታ ቡና አምራች ገበሬዎች ላሉባቸው እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ቡና የኢኮኖሚያቸው የጀርባ አጥንት ተደርጎ እስከ መወሰድ ቢደርስም፣ ከብራዚል እና ከሌሎች የዓለም ሀገራት ጋር ሲነፃፀር ተጠቃሚነታቸው እምብዛም ስለመሆኑ ይገለጻል፡፡

ለዚህ ምክንያቶቹ ከእርሻ እስከ ገበያ ድረስ ያሉ ችግሮች መሆናቸው የሚጠቀስ ሲሆን፣ በዋናነት ደግሞ ሀገራቱ በቅንጅት አለመሥራታቸውን ተከትሎ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው አለመገኘታቸው ይነሳል፡፡

64ኛው የበይነ- አፍሪካ የቡና ድርጅት ከፍተኛ የፖሊሲ መድረክ ሰሞኑን በአዲስ አበባ በተካሄደበት ወቅት እንደገለጸውም፤ አህጉሪቱ በዓለም የቡና ገበያ ውድድር ዘልቃ እንድትገባም ሆነ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሀገራቱ ትብብርና በቅንጅት መሥራት ወሳኝ ሚና አለው። በተለይም ቡና በጥሬው ከመላክ በዘለለ እሴት ጨምሮ በመላክ ተጠቃሚ እንድትሆን የሀገራቱ መንግሥታት ሊረባረቡ ይገባል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳይሆን ምርታማነትና የምርት ጥራትን በመጨመር የዓለም የገበያ መሪ መሆንን ትሻለች፡፡፡ ለዚህም ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶችን የሚቋቋም የቡና ምርታማነትን ለማረጋገጥ እየሠራች ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የአፍሪካ ቡና ምርት ተወዳዳሪ እንዲሆን የበኩሏን ሚና ትወጣለች። በተለይም የአፍሪካ የቡና ምርት ከማሳ እስከ ገበያ ተወዳዳሪና ለችግር የማይበገር ዘርፍ እንዲሆን እየሠራች ትገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት የቡናን ምርታማነት ለማስቀጠልና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ባስቀመጠችው አቅጣጫና ባዘጋጀችው እቅድ መሠረት በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ የቡና ችግኞችን መትከሏን ዶክተር ግርማ ይናገራሉ፡፡ ቡናን በጥራትም ሆነ በብዛት በማምረት የወጪ ንግድ ገቢዋን መጨመር መቻሏንም ጠቅሰዋል፡፡

በተያዘው 2017 በጀት ዓመት ወደ ውጭ ከሚላክ የቡና ገቢ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ማቀዷን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ በምርት ጥራት፣ በገበያ ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ላይ አበክራ እየሠራች መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ በተለይም እሴት ያልተጨመረበት ቡና ለውጭ ገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት በመጨመር ዘርፉ የሚያመነጨውን እድል ለመጠቀም መሥራቱን እንደተያያዘችው አስገንዝበዋል፡፡

የአፍሪካ የቡና ዘርፍ ለሚያጋጥሙት ችግሮች በዘላቂነት መፍትሔ ለማስቀመጥም ከሀገራት ጋር በትብብር እንደምትሰራ ያስታወቁት ዶክተር ግርማ፤ ከማሳ እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ ባለው የቡና እሴት ሰንሰለት ከፖሊሲ ትግበራ ጀምሮ አስፈላጊውን ሥራ ማከናወን ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በዋናነትም በዓለም ገበያ የአፍሪካ ቡና ተወዳዳሪ እንዲሆን እና ለችግሮች የማይበገር ሆኖ እንዲቀጥል በትብብር መሥራት እንደሚያሻም ይናገራሉ፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ከአምራቹ እስከ ቡና ላኪዎች ባሉት ሰንሰለቶች ሁሉ ተጠቃሚነትን ማጎልበት እና የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋት እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ዘላቂ እና ጥራት ያለው የቡና ምርት በማምረት የአፍሪካን የቡና የወጪ ንግድ ለማሳደግ የተቀናጀ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ በቡና ምርት ላይ እሴት በመጨመር የዓለም አቀፍ ገበያ ዕድሎችን ማስፋት ያስፈልጋል፡፡ ለአፍሪካ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ተጨማሪ ዕድሎችን ለመፍጠር እሴት መጨመር ይገባል፡፡ በተለይም የየሀገራቱ መሪዎችና የዘርፉ ተዋናዮች በየእለቱ የአፍሪካ ቡና እሴት ሰንሰለት የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በመለየት መፍታት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ቡናን ምርታማነት፣ ጥራትና የገበያ ተደራሽነት ለማሻሻል የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ ትቀጥላለች፡፡

የአፍሪካ ቡና የአየር ንብረት ለውጥ፣ የዋጋ ተለዋዋጭነት እና የቁጥጥር ማሕቀፎችን ማጠናከር ያለመቻሉ አህጉሪቱ ከዘርፉ የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝ ያደረጋት መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም ኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በትብብር እንደምትሠራ ያመለክታሉ፡፡ ይህም በአዳዲስ ምርምሮች፣ በኢንቨስትመንቶች እና ስትራቴጂካዊ የፖሊሲ ጣልቃ ገብነቶች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑን ያስረዳሉ።

የበይነ- አፍሪካ የቡና ድርጅት ዋና ጸሐፊ ሶሎሞን ሳቢቲ በበኩላቸው እንዳስታወቁት፤ ድርጅቱ 25 የአፍሪካ ቡና አምራች ሀገራት አባል የሆኑበት ነው፤ የአፍሪካ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተሳተፉበት የፖሊሲ ፎረም በዋናነት በቡና ምርት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን መፍታት በሚያስችሉ ጉዳዮችና ምቹ ሁኔታዎች ላይ መክሯል፡፡ የአፍሪካን ቡና ኢንዱስትሪ በምን መልኩ ትራንስፎርም ማድረግ እንደሚቻልና በተለይም የግሉን ዘርፍ በምን መልኩ መደገፍ እንደሚገባ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

«በአፍሪካ ቡና ላይ እሴት በመጨመር ገቢ ከማሳደግ በዘለለ ለበርካታ ሥራ አጥ አፍሪካውያን የሥራ እድል ለመፍጠር ያግዛል» የሚሉት ዋና ጸሐፊው፣ ለዚህም በዋናነት ሀገራቱ ምርታማነት ማሳደግ ላይ ትኩረት ሊያደርጉ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ በተጓዳኝም በአህጉሪቱ ቡና ገበያ ላይ በሚስተዋለው የዋጋ መዋዠቅ እና የፋይናንስ እጥረት ላይ ያለውን ችግር ለመፍታት ሁሉም የበኩሉን ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅበትም ያስገነዝባሉ፡፡

«እንዲህ ዓይነቱ ጉባኤ ሲካሄድ ለ64ኛ ጊዜ ቢሆንም ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ከመቼውም ጊዜ በላይ የአፍሪካ ህብረት የቡናን ተጠቃሚነት ለማሳደግ ስትራቴጂ ነድፎ እየሠራ ነው» የሚሉት ዋና ጸሐፊው፤ ይህም እንደ ትልቅ እምርታ እንደሚታይ ይናገራሉ፡፡ በአፍሪካ ቡና ላይ እሴት የመጨመሩ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ አስገንዝበዋል፤ ይህም ለአፍሪካ ቡና ገቢ እድገት መሠረት እንደሚጥልና ለቡናው ዳግማ ትንሳኤ ይሆናል የሚል እምነት እንዳላቸው ያመላክታሉ፡፡

በመድረኩ የአውሮፓ የልማት ድርጅት ከፍተኛ ኃላፊዎች መገኘታቸውን አስታውሰው፤ ይህም የአፍሪካ ቡና እሴት ተጨምሮበት በዓለም ገበያ እንዲቀርብ ለሚደረገው አህጉራዊ ጥረት ድጋፍ ለማግኘት እንደሚያስችልም ይገልጻሉ፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ድርጅቱ የአፍሪካ ቡና በዓለም ገበያ ተዋዳዳሪ እንዲሆን ከማድረግ ባሻገር በሀገራቱ መካከል የእርስ በርስ የነፃ ግብይት ሥርዓት እንዲጠናከር እየሠራ ነው፡፡ አፍሪካ ከምታመርተው ቡና አብዛኛው ወደ አውሮፓ የሚላክ ሲሆን፣ ድርጅቱ ጥራት ያለው ቡና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት በትኩረት ይሰራል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ በሌሎች የአህጉሪቱ ሀገሮች የሀገር ውስጥ የቡና ተጠቃሚነት ባሕል እንዲጎለብት የማስተዋወቅ ሥራ ቡና አምራች የአፍሪካ ሀገራት መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ያስገነዝባሉ፡፡ የእሴት ሰንሰለቱን በማጠናከር አህጉሪቱ ከዘርፉ የላቀ ተጠቃሚ እንድትሆንም ሁሉም የየራሱን ሚና መወጣት እንደሚገባው አስገንዝበዋል፡፡

ለዚህም የአህጉሪቱ ከፍተኛ መሪዎች እና ባለሥልጣናት ድጋፍ ሊያደርጉ፤ ቁርጠኝነታቸውን በተጨባጭ ማሳየት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ «በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የታደለች ናት ፤ ምክንያቱም የዓለም ገበያ ቢቀዛቀዝ ያመረተችው ቡና በሀገር ውስጥ ገበያ አያጣም፤ በመሆኑም ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የኢትዮጵያን ተሞክሮ ወስደው በሀገር ውስጥ ቡና የመጠቀም ባሕል እንዲጎለብት ማድረግ ይገባቸዋል» ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ከአምስት ዓመታት ወዲህ በቡና የወጪ ንግድ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገበች መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በዚህም በታሪኳ አይታ በማታውቀው ሁኔታ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘቷን ጠቅሰዋል። ዘላቂ እና ጥራት ያለው ምርትን በማረጋገጥ የአፍሪካን የቡና የወጪ ንግድ ለማሳደግ የተቀናጀ እና ግልፅ ተግባራት አስፈላጊ መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡

ዶክተር አዱኛ እንዳሉት፤ የአፍሪካ የቡና ምርት አሁንም ከፍተኛ የወጪ ንግድ የገቢ ምንጭ ሆኖ በመሪነት የዘለቀ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ግብርና የሥራ ዕድል በመፍጠር እና የኤክስፖርት ገቢ በማስገኘት በአህጉሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም የዘርፉን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ በአፍሪካ ቡና ኢንዱስትሪ ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ ይገባል። ለዚህም የአፍሪካ ሀገራት በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት መሪዎችን ያሳተፉ መድረኮች ቡና አምራች ሀገራት በዘርፉ የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመፍታትና ያሉትን ዕድሎች ለመጠቀም አቅም ይፈጥራሉ።

ኢትዮጵያ ዘላቂ የቡና አቅርቦት ሠንሠለትና የደን አያያዝን ለማጠናከር ቁርጠኛ መሆኗንም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረው፤ ይህም የኤክስፖርት አቅምን እና የንግድ ዕድሎችን እንደሚጨምር ይጠቁማሉ። የአፍሪካ የቡና ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን ዕድገት ለማሳካት የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ ትብብር ማድረግን እንደሚጠይቅም አስገዝበዋል፡፡

በአፍሪካ ቡና አምራች የሆኑት 25ቱም ሀገራት በጋራ ተሰብስበው የፈጠሩት ድርጅት በአህጉር አቀፍ ደረጃ በጋራ ሆነው ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንዳስቻላቸው ዶክተር አዱኛ ያመለክታሉ፡፡ ከሁሉም በላይ በአሁኑ ወቅት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት እየተደረገ ላለው አህጉር አቀፍ ጥረት በጋራ መሥራታቸው በዓለም ላይ ተሰሚነት እንዲኖራቸው ወሳኝ ሚና እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ በአፍሪካ ከሚመረተው የቡና ምርት 12 በመቶው ብቻ ለዓለም ገበያ እንደሚቀርብ ገልጸው፣ ተጠቃሚነቱን ሲታይ ከዓለም 13 በመቶ ደረጃ ላይ መሆኗን ገልጸዋል፡፡

ይህም አፍሪካ በቡና ራሷን መመገብ እንደምትችል እንደሚያመለክት ጠቅሰው፣ አህጉሪቱ ብዙ ጫና ያለባት ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ እንዳልሆነች ያስገነዝባሉ፡፡ ለዚህም አብነት አድርገው « አዳዲስ ሕጎች በሚወጡበት እንዲሁም የዓለም አቀፍ የቡና ዋጋ በሚወርድበት ጊዜ አፍሪካ እንደ አህጉር ተጠቃሚ አይደለችም» በማለት ይጠቅሳሉ፡፡ ሀገራቱ ተባብረው መሥራታቸው የጋራ ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንደሚያስችላቸው ተናግረው በተለይ የአፍሪካ ነፃ ገበያ ቀጣና የፈጠረውን እድል በመጠቀም የእርስ በርስ ግብይቱን ማጠናከር ወሳኝ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ቡና የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ እንዲሆን መደረጉን አመልክተው፤ «በአሁኑ ወቅት ድምፃችንን በጋራ ማሰማት የምንችልበት እድል ስላለ ምርታማነትን ከመጨመር አኳያ፤ በተለይም አርሶ አደሮችን ከማገዝ አንፃር በጋራ መሥራታችን ተጠቃሚ ያደርገናል» በማለት አብራርተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የህብረቱ መሪ ሀገር በሆነችበት ወቅት በርካታ ሥራዎችን ስታከናውን መቆየቷን አስታውሰው፤ በተለይም ቡና አፍሪካ ህብረት የ2063 አጀንዳ ሆኖ እንዲፀድቅ ከፍተኛ ጥረት በማድረጓ በየመድረኩ በሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ ለመነጋገርና የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ማገዙን ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ከምታመርተው ቡና 50 በመቶ የሚሆነውን በሀገር ውስጥ እንደምትጠቀም ዶክተር አዱኛ ጠቁመው፤ «ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ግን ቡና ያመርታሉ እንጂ አይጠቀሙም፤ ለምሳሌ እንደ ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ዩጋንዳ ያሉ ሀገራት 99 በመቶ የሚሆነውን ምርታቸውን ወደ ውጭ ነው የሚልኩት፤ ይህ በመሆኑ የዓለም የቡና ዋጋ ሲወርድ ለኪሳራ የሚዳረጉበት ሁኔታ አለ» ይላሉ፡፡ እነዚህ ሀገሮች በሀገር ውስጥ ቡና መጠቀም የሚችሉበትን እድል ለማስፋት ብዙ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህን ተከትሎም ለውጦች እየታዩ መሆኑን ያመላክታሉ። ኢትዮጵያም ይህንን እድል በመጠቀም የምታመርተውን ቡና ወደ ተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ለማቅረብ እየሠራች ነው ሲሉ ተናግረዋል ፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ከድርጅቱ አባል ሀገራት በተጨማሪ ቡና ተጠቃሚ የሆኑ ሀገራትም የድርጅቱ አባል እንዲሆኑ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፤ ይህም የንግድ ልውውጡን ለማጠናከርም ሆነ ቡናን በተሻለ ዋጋ ለማቅረብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ ሀገራት ጫና ስር የመውደቁንም አጋጣሚ ያጠባል፡፡ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በቡና የወጪ ንግድ እያስመዘገበች ላለችው እምርታ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው፡፡

«በተለይም ከዚህ ቀደም የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ከባድ በመሆኑ ነጋዴዎች ቡና የሚልኩት የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ነበር፤ አሁን ግን ማሻሻያው የነበረውን ችግር ፈትቶታል፤ አሁን ላይ በነፃነት የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙ በመሆናቸው ነጋዴዎች ግብይት ውስጥ ገብተው የሚረብሹበት ሁኔታን ያስቀራል» ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በሀገር ውስጥ የቡና ዋጋ እንዲንር ይደረግ የነበረበትን ሁኔታ በመፍታት በሀገር ውስጥ የቡና ገበያ እንዲረጋጋ ማድረጉን ጠቁመዋል፡፡ ይህም ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን የውጭ ምንዛሬ ከፍ ለማድረግና በጥራት ለማምረት እድል ይሰጣታል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## «ማንም ሰው በግለሰብ ይሁን በማህበር ደረጃ አጀንዳ መላክ ይችላል»

- ኮሚሽነር ሂሩት ገብረሥላሴ
የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር



ፎቶ፦አዩብ ተፈሪ

ኢያሱ መሰለ

**ኢትዮጵያ መልከ ብዙ የሆነች ሀገር ነች። ብሔርን፣ ቋንቋን ፣ ባሕልን፣ ሃይማኖትን፣ አስተሳሰብን፣ የአኗኗር ሥርዓትን እና ሌሎች ብዝሀነትን አቻችላ ለዘመናት ኖራለች። ያም ሆኖ በሕዝቦች አብሮ የመኖር ሂደት ውስጥ የተፈጠሩና ወደፊትም ቢሆን ሲፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችና አለመግባባቶች መከሰታቸው የማይቀር ነው። የአንድ ሀገር ሕዝቦች የሚግባቡባቸው የጋራ ጉዳዮች እንዳሉባቸው ሁሉ የሚለያዩባቸው አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ይኖራሉ።**

**ሕዝቦች ልዩነታቸውን አጥብበው አንድነታቸውን ቢያጠናክሩ ሰላምና ደህንነታቸውን አጽንተው እድገታቸውን ሊያፋጥኑ እንደሚችሉ ይታመናል። ኢትዮጵያ ዛሬ ወደኋላ እንድትጎተት፤ ሕዝቦቿ ተግባብተው እንዳይኖሩና እርስ በእርሳቸው በጥርጣሬ ዓይን እንዲተያዩ ካደረጓቸው ምክንያቶች አንዱ የበዳይና የተበዳይነት ስሜት ነው። ይህን ስሜት ማጥራት፣ መተማመንና መግባባት የሻከረውን የሕዝቦች ግንኙነትም ይሁን የሀገርን ሕመም የሚያክም እንደሆነ በጽኑ ይታመንበታል።**

**ይህን መነሻ በማድረግና ከዓለም ተሞክሮ በመውሰድ የዛሬ ሶስት ዓመት አካባቢ በኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል። አስራ አንድ ገለልተኛ አባላትን ያቀፈው ይህ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ተልዕኮውን ለመፈጸም የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቶ ወደ መጨረሻዎቹ ምዕራፎች ተቃርቧል። ኮሚሽኑ እስከ ዛሬ ያከናወናቸውን የሥራ ሂደቶችና ቀጣይ እቅዶቹን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ምክትል ዋና ኮሚሽነር ሂሩት ገብረሥላሴ ጋር ያደረግነውን ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ!**

**አዲስ ዘመን፡- የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሶስት ዓመታት ቆይታ እንዴት ነበር? ምን ምን ተግባራትን ሲያከናውን ቆየ?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** በኢትዮጵያ ታሪክ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሲቋቋም ይህ የመጀመሪያው በመሆኑ እንደ ሀገር በምሳሌነት የሚጠቀስ ልምድና ተሞክሮ አልነበረም። ኮሚሽኑ የዛሬ ሶስት ዓመት አካባቢ ሥራውን አንድ ብሎ ሲጀምርም ከሀገራዊ መግባባት አንጻር በዓለም ላይ የተሠሩ ሥራዎችን መለስ ብሎ ማየትን፣ መቃኘትንና ማጥናት ቀዳሚ ተግባሩ አድርጎ ነው ወደ ሥራ የገባው። የምክክሩን ዲዛይን ከመሥራታችን በፊት ምን ዓይነት ምክክር ይደረግ? ማንን የሚያካትት ይሁን? ምን ዓይነትን ሂደትን ይከተል? የሚለውን ለመወሰን ኮሚሽኑ የእያንዳንዱን ክልል አውድ ለማጥናት ሞክሯል። ከክልሎች የተገኙ መረጃዎችን በመጭመቅና በመቀመር አሠራሮችን ዘርግቶ ወደ ሥራ ገብቷል።

አውድ በማጥናቱ ሂደትም ሕዝቡን እና ባለድርሻ አካላትን የማሳተፍና የማወያየት ሥራ ተሠርቷል። ምንድነው ከዚህ ምክክር የምትጠብቁት? ሀገራዊ ምክክሩ በምን መልክ ቢካሄድ ይበጃል ትላላችሁ? እናንተ ባላችሁበት አካባቢ ወይም ክልል መካተት አለባቸው የምትሏቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? ምን ምን ጥያቄዎች አሏችሁ? እነዚህን እና መሰል ነጥቦችን በማንሳት አውዱን መረዳት ተችሏል።

የየክልሉ ማህበረሰብ ክፍሎች እንዴት ሊወከሉ እንደሚችሉ፣ በየትኛው የአስተዳደር ደረጃ ሥራችንን መጀመር እንዳለብን አስቀድመን በመነጋገር ነው ወደ ሥራ የገባነው። ለምሳሌ አካታች እንዲሆንና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የሚሳተፉበት እንዲሆን በወረዳ ደረጃ ያሉ ተሳታፊዎችን ማካተት ወሳኝ ነው። ያሉትን ወረዳዎች መረዳት፤ ከነዚህ ወረዳዎች መካተት ያለባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት፤ ተሳታፊዎችን የሚመርጠው ኮሚሽኑ ሳይሆን ማህበረሰቡ ራሱ እንዲሆን ማድረግ፤ የሚሉት አስቀድመው ተሠርተዋል።

ይህንን ሥራ ያግዙናል ያልናቸውን ተቋማት የመለየትና በየወረዳው የመረጣውን ሂደት እንዲያግዙ ማድረግ ተችሏል። በዚሁ መሠረት የአካባቢው እድር ኃላፊዎች፣ አስተማሪዎች፣ የሴቶች ማህበራት፣ የወጣት ማህበራት፣ ማህበረሰቡ የተለየ ከበሬታ የሚሰጣቸው ሰዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ተባባሪ አካል ተደርገው ከተካተቱ በኋላ ከእያንዳንዱ ወረዳ የሚመረጠውን የተሳታፊ መረጣ ሂደት እንዲመሩ ተደርጓል።

በዚህ ሂደትም ኮሚሽኑ ክትትል እያደረገ እና አቅጣጫ እየሰጠ በጥሩ ሁኔታ እንዲከናወን አድርጓል። በአሁን ሰዓትም ከትግራይ እና አማራ ክልል ውጭ የተሳታፊዎች መረጣ ተከናውኗል። በአማራ ክልል ተባባሪ አካላት ተቋቁመው ስልጠና ወስደው ሥራ ለመጀመር ዝግጁ ሆነው እየጠበቁ ይገኛሉ።

የትግራይ ክልል አመራሮች በምክክሩ አስፈላጊነት በጽኑ የሚያምኑ ቢሆንም ክልሉ ቀደም ሲል ከነበረበት ሁኔታ አንጻር ሌሎች ፈጣን ምላሽ በሚፈልጉ ማህበራዊ ችግሮች ላይ የተጠመዱ በመሆናቸው እስከ አሁን ድረስ በሌሎች ክልሎች የተሠሩ ሥራዎችን ማከናወን አልተቻለም። በቀጣይ ግን ተመሳሳይ ሥራዎችን እንሠራለን ብለን እናምናለን።

የምክክሩ ተሳታፊዎች ከተመረጡ በኋላ ያከናወነው ሌላው ሥራ አጀንዳ ማሰብሰብ ነው። ወደ አብዛኞዎቹ ክልሎች በመሄድ ማህበረሰቡ ዛሬ ኢትዮጵያን እያወዛገባት ያለው እና ልንግባባባቸው የልቻልንባቸው አጀንዳዎች እነዚህ ናቸው ብሎ ወስኖ እንዲሰጥ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

ይህ ሂደት ማህበረሰቦች ተመካክረው ፣ ተግባብተውና ተማመነው ክልላችን በዋናነት በምክክሩ ሂደት በነዚህ ጉዳዮች ላይ እንዲነጋገር እንፈልጋለን ብለው ያመኑበትን አጀንዳ የሚሰጡበት ነው። የአጀንዳ ማሰባሰቡ ሥራ ከሶስት ክልሎች ማለትም ከኦሮሚያ፣ አማራና ትግራይ ክልሎች ውጪ በሌሎቹ ክልሎች ተከናውኗል። በኦሮሚያ ክልል ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ ስለተፈጸመ በቀጣይ አንድ ወር ውስጥ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና የክልሉ የምክክር ሥራ የሚከናወን ይሆናል። በቀጣይም በአማራ ክልል ተመሳሳይ ሥራ እንሠራለን ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ እነዚህን ሥራዎች ሲያከናውን ያጋጠሙት ችግሮች ነበሩ? ካሉስ እንዴት ማስተካከል ተቻለ?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** በአንዳንድ ቦታዎች ካለው የቦታ ስፋት አንጻር መጠነኛ የሎጂስቲክ እጥረት ከማጋጠሙ ውጭ ምንም ዓይነት ችግር አላጋጠመንም። በሄድንባቸው ክልሎች ሁሉ ፊቴ ላይ የሚደቀነው የሕዝቡ ጉጉት ነው፤ ሕዝቡ ይህ ምክክር እውን እንዲሆን ያለው ፍላጎትና የጣለብን አመኔታ በጣም የሚደንቅ ነው። ምንም እንኳን ሥራውን ለመሥራት ቁርጠኞች ብንሆንም የበለጠ ግን የሕዝቡ ጉጉት ውስጣችንን ነክቶናል። በሄድንባቸው ቦታዎች ሁሉ ይደረግልን የነበረው አቀባበልና ይሰጠን የነበረው አስተያየት እጅግ በጣም ገንቢ ነው። ለዚህም ሕዝቡንም ይሁን ባለድርሻ አካላትን በኮሚሽኑ ስም ማመስገን እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በመርሃ-ግብራችሁ መሠረት ሥራችሁን በሶስት ዓመት ውስጥ እንደምታጠናቅቁ አሳውቃችሁ ነበር፤ አሁን የቀራችሁ ሁለት ወር ነው፤ በዚህ አጭር ጊዜ የተቀረውን ሥራ ማከናወን ትችላላችሁ? ወይስ እቅዳችሁን ታራዝማላችሁ ?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ ታሪክ ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነት የምክክር ሂደት ተከናውኖ አያውቅም፤ ይህ በጣም ታሪካዊ አጋጣሚና የማይገኝ እድል ነው፤ ይህንን እድል በአግባቡ መጠቀም ስለሚያስፈልግ በጥንቃቄ ልንይዘው ይገባል። ከዚህ አንጻር የኮሚሽኑ አባላት የተሸከምነው ኃላፊነት ከፍተኛ ነው ብለን ስለምናምን በጣም አሳታፊ ለመሆን ሞክረናል፤ በጥንቃቄ ለመጓዝም ጥረናል፤ ይህን ሁሉ ስናደርግ ደግሞ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲቪል ማህበራት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ እና ሌሎችንም ባለድርሻ አካላት እያሰባሰብን፤ እያመካከርን፤ የሠራነውን እያሳወቅን፤ ከእነርሱም ግብዓት እየወሰድን ነው።

ይህ የሥራ ሂደት፣ የሀገሪቱ ስፋትና የሕዝቡ ብዛት ተደማምሮ ጊዜ ወስዷል። ኮሚሽኑ ሠርቻለሁ ለማለት ብቻ የችኮላ ሥራ መሥራት አይፈልግም፤ ውጤታማ የመሆን ጉጉት ስላለው እያንዳንዱን ሥራ በጥንቃቄ ለመምራት ተገድዷል፤ አብዛኛውን ባለድርሻ አካላት አሳታፊ ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት የሥራ ሂደት አድርጓል፤ ባለድርሻ አካላትን ለማነጋገር እና በየአውዱ አካታችነትን ለማረጋገጥ የተደረገው ጥረት፣ የሌሎች ፕሮግራሞች መደራረብ መርሃ ግብሩ በእቅዱ መሠረት እንዳይሄድ ጊዜ ወስደዋል። ጊዜ መውሰዱ ግን ኮሚሽኑ የሚያኮራ ሥራ እንዲሠራ እድል የሰጠ በመሆኑ አናፍርበትም።

በማንኛውም መለኪያ አካሄዳችን ቢፈተሽ ተገቢውን ምርጫ እንዳደረግን የሚመሰክር ነው፤ አሁንም የክልላዊ ምክክሮችን እና ክልላዊ የአጀንዳ አሰጣጥ ሂደቶችን ለመጨረስ በጥሩ እንቅስቃሴ ላይ ነን። በአብዛኛዎቹ ክልሎች አጀንዳ የማሰባሰቡ ሥራ የተከናወነ ሲሆን በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት በኦሮሚያ እና በአማራ ቀሪ ሥራዎችን የምናጠናቅቅ ሲሆን፤ በመቀጠልም በትግራይ ክልል እንቅስቃሴ የምንጀምር ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ከማሳተፍ አንጻር የታሰቡ ወይም የተሠሩ ሥራዎች ይኖሩ ይሆን?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** አዎን ከሀገር ውስጥ የምክክሩን ተሳታፊዎች ከለየን በኋላ፤ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የመሳተፍ ሥራም ይሠራል። ከዚህ ቀደም አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ አውስትራሊያና በሌሎች አህጉሮች ከሚኖሩ ዲያስፖራዎች ጋር ብዙ ንግግሮችን አድርገናል። በዚህም ሥራችንን አሳውቀናል፤ በምን መልክ መሳተፍ እንደሚፈልጉ ጠይቀናል፤ አጀንዳቸውን እንዲሰጡን አሁንም በራችንን ክፍት አድርገንላቸዋል። በሚቀጥለው ሂደትም በምን መልክ ተወካዮቻቸውን እንደሚልኩና እንደሚያሳተፉ ተነጋግረን ተግባራዊ የምናደርግ ይሆናል። ማንም ሰው በግለሰብ ደረጃም ይሁን በማህበር ደረጃ አጀንዳ መላክ ይችላል። ይህ ሁሉ የአጀንዳ አሰባሰብ መጨረሻ ላይ በሀገር ደረጃ ለሚቀረጸው አጀንዳ ግብዓት ያደርጋል የሚል እምነት አለን።

**አዲስ ዘመን፡- በሰላማዊ መንገድ ትግል እናደርጋለን ከሚሉ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ አንዳንዶች በዚህ ሀገራዊ ምክክር የመሳተፍ ፍላጎት እንደሌላቸው ይገልጻሉ፤ እነዚህን የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀረብ ብላችሁ በማነጋገር ወደ ሰላማዊ ንግግሩ እንዲመጡ ምን ዓይነት ጥረት አድርጋችኋል? አሁንም ወደ ምክክሩ እንዲመጡ ምን ምክር መስጠት ትፈልጋላችሁ?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** ኮሚሽኑ ይህንን ኃላፊነት ተረክቦ ሥራ እንደጀመረ ሰሞን አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በገለልተኝነታችን እና በተዓማኒነታችን ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ ውስጥ ገብተው ነበር። ሌላው ቀርቶ በኮሚሽኑ እንድንካተት የተደረገበትን አግባብ ለማመን ይቸገሩ ነበር፤ እውነታው ግን እነርሱ እንደሚያስቡት አይደለም።

ሁላችንም ቢሆን እዚህ ኮሚሽን ውስጥ እንድንካተት የተደረገው በራሳችን ፍላጎት ወይም በመንግሥት አካላት ምርጫ ሳይሆን መስፈርቶችን ያሟላሉ በሚል በሰዎች ጥቆማ እንደተመረጥን ነው የምናውቀው። ሁላችንም አንተዋወቅም፤ እንግዲህ ገለልተኝነታችን የሚታወቀው በምንሠራው ሥራ ነው። እስከ አሁን ምን ሰርተዋል? አካሄዳቸው ምን ይመስላል? የሚለውን ተመልክቶ ነው አመኔታ ማሳደር ወይም ጥርጣሬ መፍጠር የሚቻለው።

በርግጥ መጀመሪያ አካባቢ ከኮሚሽኑ ጋር ለመሥራት ፍላጎት የነበራቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዛታቸው 40 የሚደርስ ብቻ ነበር፤ ከዚያ በኋላ የኮሚሽኑን ሥራ በመከታተልና በመገምገም ራሳቸውን አግልለው የነበሩ ትላልቅ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ በአሠራራችሁ አመኔታ አሳድረናል እያሉ አብረውን መሥራት ጀምረዋል። በአሁኑ ሰዓትም አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር እየሠሩ ይገኛሉ። በጣም ጥቂት የሆኑት ግን አሁንም ወደ እኛ መካተት አልፈለጉም።

በእኛ በኩል በተደጋጋሚ ጥሪ ስናቀርብላቸው ከርመናል፤ በአካልም ተገኝተን ስለጉዳዩ አነጋግረናቸዋል፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ የትጥቅ ትግል የጀመሩ አካላት በሀገራዊ ምክክሩ እንዲሳተፉ አሁንም ድረስ እየጋበዝናቸው እንገኛለን። መሳተፍ ያልፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኮሚሽኑ ገለልተኛ ሆኖ ሀገራዊ ችግሮች በምክክርና በውይይት እንዲፈቱ የሚያደርገውን ትክክለኛ ሂደት እየተረዱ ሲመጡ በመጨረሻው ሰዓትም ቢሆን ሊቀላቀሉን ይችላሉ ብለን እንገምታለን።

ሂደቱን ቀረብ ብለው ሳያዩ ከሩቅ ሆነው አላምነውም ማለት ተገቢ አይደለም። አሳማኝ የሚሆነው ተጠግቶ ፈትሾ ወይም አብሮ ሰርቶ እንዲህ ዓይነት ችግር አለበት እና አብሬ መቀጠል አልችልም ማለት ሲቻል ነው። በተለይም ሰላማዊ ትግል ነው የምንታገለው ብለው የሚያምኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲህ ዓይነት የምክክር መድረክ ማግኘታቸው ዓላማቸውን ሊያሳካላቸው ይችላል።

ኮሚሽኑ በሰላማዊ መንገድ ትግል ለሚያደርጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን የትጥቅ ትግል ውስጥ ለገቡትም ጭምር ጥሪ አድርጓል። ደህንነታቸው ተጠብቆ ምንም ዓይነት ሥጋትና ጥርጣሬ ሳይኖራቸው መጥተው ተነጋግረው እንዲሄዱ መልእክት አስተላልፈናል። ከዚህ አንጻር ከመንግሥትም ጋር ተነጋገረን ፈቃደኝነቱን ገልጾልን

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# «ማንም ሰው በግለሰብ ይሁን ...

ከገጽ 8 የዞረ

በማስ ሚዲያ አሳውቀናል። ምንም ዓይነት የደህንነት ሥጋት ሳይኖርባቸው መጥተው መሳተፍ እንደሚችሉ፤ ሥጋትም ካደረባቸው ይሄንን የሚያመቻቹ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስላሉ በእነርሱ አማካኝነት ተሳትፈው አለን የሚሉትን ጥያቄ በምክክር እንድንፈታው ጥሪ አቅርበናል።

**አዲስ ዘመን፡- በሚዲያ ጥሪ ከማድረግ ባሻገር በእናንተ በኩል በአካል ተገናኝቶ ለመነጋገር ሙከራ ተደርጎ ነበር?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል የትጥቅ ትግል የሚያደርጉ ቡድኖችን ከሚመሩ አካላት ጋር አሉን በሚሏቸው ጥያቄዎች ዙሪያ በቀጥታ የተነጋገርንበት አጋጣሚ የለም፤ ግን መልዕክታችንን ሊያደርሱልን ከሚችሉ ሰዎችና በየክልሎቹ ከሚገኙ ምሁራን ጋር ከግጭት ይልቅ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ መክረናል።

አሁንም በዚህ አጋጣሚ ለእነዚህ አካላት የማስተላልፈው መልዕክት ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮም ይሁን ከሀገራችን ተሞክሮ መገንዘብ እንደሚቻለው በጦርነት የተፈታ ችግር የለም። ከሀገራችን ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው አለመግባባትን በውይይት መፍታት እየቻልን ብዙ ምሁራንና ወጣቶችን ያጣንባቸው መጥፎ አጋጣሚዎች ያስቆጩናል። እዚህ ሀገር አንድ የተማረን ዜጋ ለማፍራት ኢንቨስት የሚደረገው ገንዘብ፣ ልፋትና ድካም እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። በከፍተኛ ልፋትና ድካም ተምረው ለጥሩ ውጤት የበቁ ብርቅና ውድ ዜጎች ተነጋግረን መፍታት በምንችለው የፖለቲካ ጉዳይ ሲሞቱ ለቤተሰብም ይሁን ለሀገር ምን ያህል የከፋ ጉዳት እንደሚያስከትል መረዳት አይከብድም። ወደ ትጥቅ ትግል አስገብተውናል እና አላግባቡንም የሚሏቸውን ጉዳዮቻቸውን ቁጭ ብለው በመመካከር ሊፈቱ የማይችሉበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። በምክክር መድረኩ የሚሰበሰቡትን የኢትዮጵያ ተወካዮች የሚያሳምን ጉዳይ ካላቸው፤ መጥተው በማሳመን ውሳኔ ማግኘት ይችላሉ።

ችግርን በውይይትና በሰለጠነ መንገድ መፍታት በሚቻልበት በዚህ በ21 ኛው ክፍለ ዘመን ወጣትነታቸውና እድሜያቸው ግብታዊ የሚያደርጓቸውን ልጆች እያነሳሱ ማስፈጀት አይጠቅምም። የመነጋገር እድል ባይኖር እና በሮች ሁሉ የተዘጉ ቢሆን እንኳ በሩን ለማስከፈት ማንኳኳት ያስፈልጋል እንጂ ፤ ጦርነትን መፍትሔ ማድረጉ አይጠቅምም።

ማህበረሰባችን በተለያዩ ጨቋኝና አምባገነን ሥርዓቶች ውስጥ ሲያልፍ የኖረ ነው፤ ከዚህ የተነሳ የሚነገረውን ከማመን ይልቅ ይጠራጠራል። እውነት ለመናገር የኮሚሽኑ አባል ሆነን የተመረጥን ሰዎች በዚህ ጉዳይ እጃችንን ያስገባነው በሀገራችን ጉዳይ ያገባናል፤ ሕዝብ አምኖብን ኃላፊነት እስከሰጠን ድረስ ከእኛ የሚደረገውን ማንኛውንም ጥረት አድርገን የሀገራችንን ሰላም እናስጠብቃለን፤ የሕዝባችንን አንድነትና ፍቅር እናጸናለን በሚል እምነት ነው። ይህን ሃሳብ እውን ለማድረግ በምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች እስከ ዛሬም ድረስ በየትኛውም አካል ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አልደረሰብንም፤ እንደውም አይዟችሁ! በርቱ! ከጎናችሁ አለን! የሚሉን በርካቶች ናቸው።

ስለሆነም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሀገራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ የመጀመሪያው የሥነ ልቦና ዝግጅት አሉን የምንላቸውን ችግሮች ተነጋግሮ የመፍታት ፍላጎት ማሳደር ነው። አሉን የምንላቸው ችግሮች እንዲቆዩ የምንፈልግ ከሆነ ግን እንዲህ ዓይነት የውይይትና የምክክር አጋጣሚዎችን የመጠቀም ፍላጎት አይኖረንም። የእውነት ችግሩ እንዲፈታ የምንፈልግ ከሆነ ታዲያ ለምንድነው እንዲህ ዓይነት እድሎችን የማንጠቀማቸው? ከዚህ የተሻለስ በምን ዓይነት መንገድ ነው ልንፈታቸው የምንችለው? አስፈላጊ ከሆነም እኮ መጥተው፤ ተነጋግረው፤ መግባባት ላይ መድረስ ካልቻሉና ጥያቄያቸው በሚያረካ መንገድ ካልተመለሰላቸው ተመልሰው ወደ ጫካ ወይም ወደነበሩበት እንዳይሄዱ የሚከለክላቸው ነገር የለም። የምክክር መድረኩ እስከዚህ ድረስ ነፃነት የሚሰጥ እንጂ ከዚህ ሃሳብ ውጭ ንቅንቅ እንዳትሉ የሚል አለመሆኑ ሁሉም ሊያውቀው ይገባል።

ስለሆነም ይህንን እድል አለመጠቀም ወደፊት የሚያስቆጭ በመሆኑ በሀገራዊ የምክክር መድረኩ ላይ የመሳተፍ ፍላጎት የሌላቸው ነገር ግን ሰላማዊ ትግልን ምርጫቸው ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ በትጥቅ ትግል ውስጥ የገቡ አካላት ቆም ብለው በማሰብ ይህን ተመራጭ መንገድ ሊመለከቱት ያስፈልጋል። አሁንም



ቢሆን አሉን የሚሏቸውን ጉዳዮች ወደ ምክክር መድረኩ ይዘው በመቅረብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ቁጭ ብለው መክረውባቸው እንዲወስኑባቸው ጥሪ አስተላልፋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የምክክር ኮሚሽኑ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤትና በሲቪክ ማህበራት እንዴት እየታገዘ ነው? እንዴትስ ይታገዝ ይላሉ?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** ኮሚሽኑ ይህንን ግዙፍ ሥራ በሀገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ሆኖ እንዲተረጎም በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ግን ይህ ሀገራዊ ምክክር ውጤታማ እንዲሆን የሌሎች ባለድርሻ አካላትም እገዛ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የምክክር መርሃ-ግብሩን በተመለከተ ኢትዮጵያ መላው ሕዝቧን ያሳተፈ ምክክር እያካሄደች መሆኗን ሚዲያዎች ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በውስጥም ይሁን በውጭ ላሉ ዜጎች ተደራሽ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ሚዲያዎች አልፎ አልፎ ኮሚሽኑ የሚያካሂዳቸውን ሁነቶች ብቻ መዘገብ ሳይሆን ለጉዳዩ ትልቅ ትኩረት በመስጠትና ቋሚ ፕሮግራም በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራን ሊሠሩ ይገባል። የሀገር ጉዳይ የእያንዳንዱ ዜጋ ጉዳይ ስለሆነ ሚዲያዎች ራሳቸው የጉዳዩ ባለቤት ሆነው በየጊዜው ሽፋን በመስጠት ወደ ማህበረሰቡም ሆነ ወደሚመለከተው አካል የማስረጽ ሚናቸውን በመወጣት የኮሚሽኑን ሥራ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

ጉዳዩ የኢትዮጵያ የህልውና ጥያቄ ነው፤ ሁሉም ነገር የሚኖረው ሀገር ሲኖር እስከሆነ ድረስ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል። ሁሉም ኃላፊነቱን ካልተወጣ ይህ የያዝነው ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ የሚፈለገው ደረጃ ላይ ሊደርስ አይችልም።

ምሁራንም በሚያውቋቸው ፣ በሚገምቷቸው እና የኢትዮጵያ ሕዝብን ሳያግባቡ የቆዩት እነዚህ ናቸው በሚሏቸው ነጥቦች ዙሪያ ከስሜትና ከግል ፍላጎት የጸዱ፤ እውነትን፣ እውቀትንና ተጨባጭ መረጃን መሠረት ያደረጉ ጥናቶችን በማጥናት አንዳንድ የሚያወዛግቡ ነገሮችን አብላልተው በማብራራትና ብዥታዎችን በማጥራት ኃላፊነታቸውን ሊወጡ፤ ኮሚሽኑንም ከዚህ አንጻር ሊያግዙ ይገባል።

እያንዳንዱ ሰው በጉዳዮች ላይ የየራሱ አቋም አለው፤ ያ አቋሙ በዝምድና፣ በዝንባሌ፣ በዘር፣ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ እንጂ በጥያቄው እውነተኛ መልስ ላይ የተመረኮዘ ላይሆን ይችላል። ህብረተሰቡ እንዲህ ዓይነቱን ኋላቀር አስተሳሰብ ትቶ በእውቀትና በእውነት ላይ የተመሠረተ መረጃ እንዲጨብጥና ራሱን በዚህ መልክ እንዲገነባ ምሁራን እውቀትን የመፈለግ ባሕል ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰርጽ አበክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። አሁን በሚያወዛግቡ ጉዳዮች ዙሪያ ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆኑ ጥናታዊ ጽሑፎችን አዘጋጅቶ የማቅረቡ ሥራ ገና አልተጀመረም፤ ፖለቲካውን የሚያግዙ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል።

የሲቪል ማህበራትም ቢሆኑ በሚያምኑባቸውና በወሰዷቸው አቋሞች ላይ ጥናት እያጠኑ ለሕዝቡ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፤ ሕዝብን የማደራጀት ፣ የማንቃት ፣ የማነቃነቅ ሥራ ሊሰሩ ይገባል፤ እያንዳንዱ ግለሰብም ይሁን ተቋም የሚጠበቅበትን ሲያደርግ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ታገዘ ማለት ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ምክር ቤታቸው ስለሀገርና ስለሕዝብ ሰላምና ደህንነት የቆሙና የተመሠረቱ እንደመሆናቸው የሕዝቦች ተግባብቶ መኖርና የሀገር ደህንነት ጉዳይ ያስጨንቃቸዋል፤ በዚያው ልክ መሥራትም ይጠበቅባቸዋል። ቁጭ ብሎ ተመልካችና ተች መሆን ግን ሁሉንም ሰው ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ አያደርግም። ኢትዮጵያውያን ትልቁ ችግራችን አንዱ አካል ሲሠራ ሌሎቻችን ተመልካች፣ ታዛቢ እና ተቺ መሆናችን ነው። ይህ አስተሳሰባችን ወደ ችግር እየከተተን መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እውነትን መፈለግ፣ የሌላውን የማህበረሰብ ክፍል ወይም የሀገራችን ዜጋ ቁስል ማዳመጥ ፤ ለመረዳት መሞከር፣ የራስን ብቻ አለመፈለግ የመሳሰሉ ባሕሎች እንዲዳብሩ ሁሉም ሚናውን ሲወጣ ሥራችን ውጤታማ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም።

እያንዳንዱ ሰው መረዳት ያለበት ጉዳይ በዚህ ሀገራዊ ምክክር የሚገኘው ውጤት የሚጠቅመው ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጎች ነው። ስለዚህ ሥራውን የኮሚሽኑ ብቻ አድርጎ መመልከት አግባብነት የለውም። ሀገራዊ ምክክሩ እውን የሚሆነው የመላው ሕዝብና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲታከልበት እንጂ ኮሚሽኑ በሚሠራው ሥራ ብቻ አይደለም። ኮሚሽኑ ከእርሱ የሚጠበቁትን እና መሠራት ያለባቸውን ትልልቆቹን ሥራ ያከናውናል፤ እንደ ዜጋ፣ እንደባለድርሻ አካል፤ ሁሉም ኃላፊነቱን ቢወጣ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ይጠቀማሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ከአጀንዳ ማሰባሰብ በኋላ ቀጣይ የኮሚሽኑ የሥራ ትኩረቶች ምንድን ናቸው?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** ከተለያዩ ክልሎች የተሰበሰቡት አጀንዳዎች ቁጥራቸው እጅግ በጣም ብዙ ነው፤ በተለይም ኢትዮጵያን በተመለከተ የተሰበሰቡት አብዛኞዎቹ አጀንዳዎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ናቸው፤ ክልሎችን በተመለከተ የተነሱት ደግሞ እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ ናቸው። በቀጣይ እነዚህን የተሰበሰቡ አጀንዳዎች በመያዝ ከኤክስፐርቶችና ከአማካሪዎች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር አጀንዳዎች ይቀረጻሉ ማለት ነው።

በአጠቃላይ ከተሰበሰቡት አጀንዳዎች መሠረታዊ

**የአጀንዳ ማሰባሰቡ ሥራ ከሶስት ክልሎች ማለትም ከኦሮሚያ፣ አማራና ትግራይ ክልሎች ውጪ በሌሎቹ ክልሎች ተከናውኗል። በኦሮሚያ ክልል ተሳታፊዎችን የመለየት ሥራ ስለተፈጸመ በቀጣይ አንድ ወር ውስጥ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና የክልሉ የምክክር ሥራ የሚከናወን ይሆናል። በቀጣይም በአማራ ክልል ተመሳሳይ ሥራ እንሠራለን ብለን እናምናለን**

ናቸው፤ ለኢትዮጵያ ፋይዳ ይሰጣሉ፤ የምንላቸውን ጉዳዮች አንጥረን በማውጣት፤ የምክክሩ አጀንዳ እንዲሆኑ እንወስናለን። እነዚህ አንኳር አጀንዳዎች ሲመረጡ የተለያዩ መለኪያዎች ይኖራቸዋል። ለምሳሌ በጣም አጣዳፊና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ወይም አብዛኛው ሰው ያነሳቸው ጉዳዮች እየተባሉ እንደየ አስፈላጊነታቸው ሊመረጡ ይችላሉ።

በመጨረሻም እነዚህ የተመረጡ አጀንዳዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገራዊ ምክክሩ የሚነጋገርባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ተብለው ለሕዝቡ ይፋ ይደረጋሉ። ከዚህ በኋላ ሀገራዊ የምክክር ጉባዔው ይጠራል፤ በጉባዔው ላይ በሚካሄዱት ምክክሮች ጥግ እና ጥግ ወይም ዳር እና ዳር ያሉ ወገኖች ወደ መሃል መጥተው አንዱ የሌላውን ሃሳብ እንዲያዳምጥ፤ አዋቂዎችና ምሁራን መሠረታዊ ማስረጃ ወይም እውነታ ላይ የተመሠረቱ ጉዳዮችን በማቅረብ በምክክሩ ሂደት ተሳታፊዎቹ መግባባት ላይ እንዲደርሱ የማድረግ ፤ ማወቅ ያለባቸውን መሠረታዊ ነገር እንዲያውቁ እገዛ የሚያደርጉበት ሂደት ይኖራል።

እንግዲህ ምኞታችን እና ዓላማችን የተራራቁ አስተሳሰቦች የሚታረቁበት እና አንድ የሚያግባባ ቦታ ላይ ደርሰው ውሳኔ እንዲያገኙ ማስቻል ነው። ይህን ስናደርግ የምክክሩ ተሳታፊዎች ኢትዮጵያን በሙሉ የሚወክሉ የማህበር ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት እንደመሆናቸው ውሳኔው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውሳኔ ይሆናል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራዊ ምክክሩ ውጤታማ እንዲሆን ከመንግሥት ምን ይጠበቃል?**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሕግ ማሕቀፍ ኖሯቸው፤ መመሪያና ደንቦች ተቀምጠውላቸው ነገር ግን በዚያው መሠረት የማይከናወኑ አሠራሮች አሉ። እነዚህ ደግሞ በማህበረሰቡ ውስጥ ቅሬታ የሚፈጥሩ ናቸው። ለምሳሌ በሴቶች መብት ጉዳይ ብንመለከት፤ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦቹ ቢኖሩም ሙሉ ለሙሉ ሴቶችን ከማብቃት ወይም ወደ ላይ ከማምጣት አንጻር በበቂ ሁኔታ አይተረጎሙም።

ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትም በሚገባው ልክ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው ወይ? ብለን ብንጠይቅ ጥሩ ምላሽ ላናገኝ እንችላለን፤ እንዲህ ዓይነቶቹ በሰዎች አፈጻጸም ጉድለት ምክንያት የሚነሱ ቅሬታዎችና ችግሮች ወደ ሀገራዊ ምክክሩ በምናደርገው ጉዞ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

እነዚህ በየተቋማቱ ከአሠራር ጉድለት አንጻር የሚፈጠሩ ሰው ሠራሽ ችግሮች በወጣላቸው አዋጅ ፣ መመሪያና ደንብ መሠረት እዚያው በየተቋሙ ውስጥ መፈታት ቢችሉ በሀገራዊ ምክክሩ እንደ አንድ ሀገራዊ አጀንዳ ተደርገው አይታዩም። ስለዚህ መንግሥት የተቋማትን አሠራር እየፈተሸ ከወዲሁ ማስተካከያ በመስጠት ኮሚሽኑ በሌላ ጉዳይ እንዳይወጠር ማገዝ ይኖርበታል።

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊም ይህ ጉዳይ የእኔ ጉዳይ ነው ብሎ መከታተል፤ መሳተፍ፤ ሃሳብ ማመንጨት፤ አጀንዳ መላክ፤ ለምክክሩ ሂደት የሚጠቅሙ ሥራዎችን መሥራት ይኖርበታል።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንግዳ ሆነው በዚህ ወቅታዊና ሀገራዊ ጉዳይ ላይ ቃለ ምልልስ እንድናደርግ ፈቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ!**

**ኮሚሽነር ሂሩት፡-** እኔም አመሰግናለሁ!

ማህበራዊ

# አስኳላ

## «የመምህራን ችግሮች ቢቀንሱም አሁንም መፍትሔን ይሻሉ»

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አሁን አሁን ከአለብን የኑሮ ጫናና የሥራ ቅጥር ሁኔታ አንጻር መማር ፋይዳው እንዲታየን አድርጓል። እንደያውም አንዳንዶች የቅንጦት ተግባር አድርገው ሲወስዱትም ይስተዋላል፡፡ በተለይም ኑሮው አልገፋ ያላቸው ሰዎች ‹‹ተምሬ ሥራ የለኝ፤ ተምሬ የሚከፈለኝ ደሞዝ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፤ ስለዚህም ባልማር ይሻለኝ ነበር›› ሲሉም እናደምጣለን፡፡ ባልማር ኖሮ የብዙዎቹ እሮሮ ከሆነም ሰነባብቷል። ምክንያቱም ሳይማር ነጋዴ የሆነውና የተለያዩ ሥራዎች ላይ የተሰማራው በኑሮው ሁኔታ ልቆ ተገኝቷል፡፡ ቢሆንም ግን ትምህርትን የሚተካው ነገር እንደሌለ ማንም ያውቀዋል፡፡ በትምህርት ያልዳበረ ልምድ ከትርፉ ይልቅ ኪሳራው እንደሚያመዝንም እሙን ነው፡፡

ይህ ምሬት በአግባቡ መቀየር ከሁሉም የተማረ አካል ይጠበቃል፡፡ በተለይም ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በቀጥታ ወደ ሥራው ዓለም ለመሰማራት የሚነሳው አካል ይህንን በተግባር ገልጦ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ ትምህርት አቅም እንደሆነ ማስረዳትም ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህ ደግሞ የትምህርት አውራ የሆነውን መምህር በተለያየ መንገድ ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ ትምህርት የሁሉም ነገር መሠረት እንደሆነም የምናረጋግጠው የሁሉም ሙያዎች አባት የሆነውን መምህር ክብርና ሞገስን ስንሰጠው ነው፡፡ ያለበትን የኑሮ ጫና ስናቀልለት ነገሮች እየተስተካከሉ እንደሚሄዱ መቀበል ይገባል፡፡ በተለይም የትምህርት ስብራት ነው ተብሎ የሚጠቀሰው የትምህርት ጥራት ጉዳይ መፍትሔ የሚያገኘው መምህሩ ችግሮቹን ሳይሆን ተማሪዎቹን እያሰበ ሲሰራ ነው፡፡ እናም ለዚህ ተግባር እውን መሆን ከግለሰቦች የጀመረ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ መንግሥትም ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በርግጥ እንደ ሀገር መምህርን የሚደግፉ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ልዩ ትኩረታቸው ትምህርታቸው ላይ አድርገው መምህራን እንዲሰሩ የቤት ባለቤት የሚሆኑበት እድል ተመቻችቷል፡፡ ተግባሩ ግን እንደ አካባቢው ሁኔታ ይለያያል፡፡ አንዳንዱ የተሠራ የመኖሪያ ቤት ሲያገኝ፤ ሌላው ደግሞ የመኖሪያ ቤቱን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲከራይ ተመቻችቶለታል፡፡ ይህ ከከበደ ደግሞ ተደራጅቶ የሚሰራበትን ሁኔታም ተፈጥሮለታል። እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሉት ደግሞ ሁሉንም አማራጮች ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ ምክንያቱም በከተማዋ ያለው የመኖሪያ ቤት ችግር ለመምህሩ ብቻ ሳይሆን ለከፍተኛ ደሞዝ ተከፋይም የሚቻል አይደለም፡፡

በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ የመምህራን ጉዳይ ያገባኛል ከሚለው አካል ጋር በመነጋገር የመምህራን ቁጥር እጅግ ብዙ በመሆኑ በአንድ አማራጭ ብቻ ፍላጎታቸውን ማሳካት አይቻልምና የተለያዩ አማራጮችን ተጠቅሞ መፍትሔ የሚያገኝበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አንጻርም እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመምህራን ችግሮች ዙሪያ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ምን እንደሚመስሉ በከተማ አስተዳደሩ የመምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ድንቃለም ቶሎሳ ነግረውናል፡፡

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ማህበሩ ብዙን ጊዜ የመምህራንን ጩኸት ማስተጋባት እንጂ የትምህርት ጥራት ላይ ልዩ ትኩረቱን ሰርቷል ለማለት ብዙ አያስደፍርም፡፡ አሁን ግን ሀገርን የማጽናቱ ኃላፊነት የመምህሩ በመሆኑ ግዴታቸውን አውቆ እንዲሰራ የማድረግን ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ አንዱ መምህራንን የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ምን መሥራት አለባቸው የሚለውን ተግባር በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መሥራት ነው፡፡ አሁን ላይ የትምህርት ጥራት ጉዳይ አንገብጋቢና የትምህርት ስብራት ሆኗልና መምህራን ከሁሉም በላይ ይህንን ታሳቢ አድርገው እንዲሰሩ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

የሚያጋጥሟቸውን ችግሮችም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ይፈታል፡፡ በተለይም ከአቅም ማነስ ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች እንደ መምህራን ማህበር በሥልጠና እና መሰል የትምህርት እድሎች ለመሙላት ይሰራል፡፡ በመምህራን አካባቢ የሚታዩ የግለሰብ ችግሮችንም በክትትል ይፈታል፡፡ በተለይም የክፍለ ጊዜ ብክነት፤ ቸልተኝነት፤ ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን በመሥራት ለተማሪው በቂ ጊዜ አለመስጠትን የመሳሰሉ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ለማድረግም ይጥራል፡፡ ይህን እንዲያደርጉ ስናስገድድ ለመምህራን መደረግ ስላለበትም መብትና ጥቅማቸው በመታገል የግድ ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም ከአሏቸው በርካታ ጥያቄዎች መካከል ዋና ዋና የሚባሉትን ለመመለስ እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡ ለሁሉም መምህራን ባይሆንም መፍትሔ የተገኘባቸው ተግባራት እንዳሉም ጠቅሰዋል።

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋነኛ ጥያቄ ተደርጎ የሚወሰደው የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ሲሆን፤ ከተማዋ በርካታ ሕዝቦችን አቅፋ የምትኖር በመሆኗ ቤት የሌለው መምህር እንዳይፈተን ብዙ አማራጮችን በመጠቀም መፍትሔ እንዲያገኝ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ተግባርም በመጠኑ ለተወሰኑ መምህራን እፎይታን ሰጥቶ ያለፈ ነው፡፡ ለአብነት መምህራን በዝቅተኛ ዋጋ ተከራይተው ለመኖር ይረዳቸው ዘንድ በ2009 ዓ.ም አምስት ሺህ መምህራን ኮንዶሚኒየም ቤቶችን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ከዚያም አልፎ በ2014 ዓ.ም መምህራኑ ከኪራይ ተላቀው ቤቱን በራሳቸው ስም እንዲያዘዋውሩት እድል ተመቻችቶላቸዋል፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን አንዳንድ ቤቶች በተለያየ ምክንያት ያለ አግባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ እንደነበር ተደርሶባቸዋል፡፡ ችግሮቹ መምህሩ ቤቱን ከተረከበ በኋላ ሥራውን መልቀቅ፤ ቤቱን እንደ ያዘው ወደ ውጭ ሀገር መሄድና መሰል ተግባራት መፈጸማቸው ነበሩ። ስለሆነም ምንም ያልተጠቀሙ መምህራን እያሉ ያለ አግባብ ቤቱን የያዙት መጠቀም ስለሌለባቸው ቤቱን ከእነርሱ በመውሰድ በ2016 ዓ.ም መጋቢት ወር ላይ ለ435 መምህራን በእጣ እና ችግሮቻቸው ከፍተኛ የሆኑትን መምህራን በመለየት በቀጥታ እንደተላለፍ ተደርጓልም ሲሉ ፕሬዚዳንቱ አንስተዋል፡፡

እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር 33ሺህ መምህራንን ይዞ ለሁሉም የመኖሪያ ቤት ምላሽ በአንድ ዓይነት አማራጭ መስጠት አዳጋች እንደሚሆን የጠቀሱት አቶ ድንቃለም፤ በመምህራን ማህበር በኩል የተለያዩ አማራጮችን የመጠቀም ሥራዎች እንዲከናወኑ ሰነድ መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ከሰነዱ ውስጥ ውሳኔ የተላለፈባቸውና ወደ ተግባር የተገባባቸው ሥራዎች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡ ከተሠሩት ተግባራት መካከልም አንዱ መምህራንን ማህበር ማደራጀት የሚለው ሲሆን፤ 23ሺህ437 መምህራን በ264ማህበራት እንዲደራጁ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ ቅድሚያ ቆጥበን ወደ ሥራው እንገነባለን ያሉ 96 ማህበራት መሆናቸውንም አስረድተዋል፡፡

የመደራጀቱ ሥራ ብዙ መልሶችን የሚፈልግ እንደነበር የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፤ እንደ መምህራን ማህበር ለዚህም ችግር መፍትሔ እንዳገኙ ያስረዳሉ። ለአብነትም መምህሩ ሲቆጥብ በምን ያህል ፐርሰንት እንደሚሆን የተቀመጠው በዋናነት የሚጠቀስ ነው። ይህም ብዙዎችን የእድሉ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን፤ እንደ ሌላው የቤት ቆጣቢ 70 በመቶ ቆጥቦ ሌላውን ከባንክ የሚበደር አይደለም፡፡ 30 በመቶ ቆጥቦ 70 በመቶው ከባንክ በሚገኝ ብድር እንዲሠራ የተመቻቸበት ነው፡፡ ከባንክ የሚገኘው ብድር ተመጣጣኝነት፤ የእፎይታ ጊዜ የሚታይበትም እንዲሆን የተቀመጠ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ ሌላው ለመምህራኑ የተመቻቸ ሁኔታ የተፈጠረበት ተግባር ቆጥበው ይደራጁ ሳይሆን ተደራጅተው ይቆጥቡ የሚለው ውሳኔ ነው፡፡ ይህ እድል ለመምህራኑ አዲስና የቤት የማግኘት መብታቸውን የሚያረጋግጥ መሆኑንም አክለዋል፡፡

እንደ አቶ ድንቃለም ማብራሪያ፤ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሌላው በመምህራን በኩል የሚነሳው ጥያቄ የትራንስፖርት ጉዳይ ሲሆን፤ መምህራን ማህበሩ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ችግሩ እልባት የሚያገኝበትን መንገድ ፈጥሯል፡፡ ይህም መምህራን በነፃ የከተማ አውቶበሶችን እንዲጠቀሙ የተመቻቸበት ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ጡረታ የወጡትን መምህራን ጭምር የሚያካትት ተደርጎ ነው የተፈቀደው። እስከ ዛሬ እነዚህ መምህራን ጡረታ ልክ ሲወጡ መታወቂያቸውን እንዲመልሱ ደረግ ነበር፡፡ ሆኖም ያሉበት ሁኔታ በግልጽ የሚታይ ነውና ችግራቸውን ለመጋራት ሲባል መታወቂያቸውን ሳይመልሱ በዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

> **ለመምህራን ሕክምና አገልግሎት የሚውል ሆስፒታልና ሁለገብ ሕንጻ ለመገንባት እየተሠራ ነው። እንደ ከተማ አስተዳደር ለመምህራን ማህበሩ 3,600 ካሬ ሜትር ቦታ የተሰጠ ሲሆን፤ መሠረቱ ወጥቷል**

የመምህራን ሌላኛው ጥያቄ የደሞዝ እርከንን የሚመለከተው ነው፡፡ 18 ዓመትም ሆነ 40 ዓመት ያገለገለ መምህር በእኩል ደረጃ ይፈረጃል፡፡ ይህ ደግሞ ከታች ያለውንም ሆነ ብዙ ያገለገለውን መምህር የሚያነሳሳ፤ ሙያውን ፈልጎ የሚያገለግል አያደርገውም።

ይልቁንም ለዚህ ደሞዝማ አልገባም የሚል እሳቤ ውስጥ ይከተዋል፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዱ ሥራ የእርከን ማሻሻያ ያስፈልገዋል፡፡ ብዙ ያገለገሉ መምህራንም ዋጋቸው እውቅና ሊሰጠው ይገባል። በአነስተኛ ደሞዝ ጡረታ ወጥተው በብዙ እየተሰቃዩ ነው፡፡ በአገለገሉበት ልክ ደሞዛቸውም እያደገ ሄዶ ጡረታ ሲወጡ አቅም ሊፈጠርላቸው ግድ ነው። በዚህም መምህራን ማህበሩ የዘወትር ጥያቄው አድርጎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

መምህራን ችግሮቻቸው ብዙ ናቸውና ዋና ዋናዎቹ መፍትሔ እንዲያገኙ ይፈለጋል፡፡ ከእነዚህ መካከልም ነፃ ሕክምናን የሚያገኙበት ሁኔታን መፍጠር አንዱ ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም ለመምህራን ሕክምና አገልግሎት የሚውል ሆስፒታልና ሁለገብ ሕንጻ ለመገንባት እየተሠራ ነው፡፡ እንደ ከተማ አስተዳደር ለመምህራን ማህበሩ 3,600 ካሬ ሜትር ቦታ የተሰጠ ሲሆን፤ መሠረቱ ወጥቷል። ይህም ከከተማ አስተዳደሩ ባደረገው 50 ሚሊዮን ብር እየተከናወነ መሆኑን አቶ ድንቃለም አስረድተዋል።

ሆስፒታሉ ሰባት ወለል ከፍታ ያለው ሲሆን፤ ይህንን ይደጉማል የተባለለት ሁለገብ ሕንጻው ደግሞ ዘጠኝ ወለሎች እንዲኖሩት ተደርጎ ዲዛይኑ ተሰርቷል። ሁለገብ ህንጻው የሬዲዮ ስቴሽን፤ የጥናትና ምርምር ማዕከልና ቤተ መጻሕፍት ያለው እንዲሁም ለቢሮ የሚከራዩ ሕንጻዎችን ይይዛል፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ የፋይናንስ ችግር እንደገጠማቸውና ለዚህም መፍትሔ እያፈላለጉ እንደሆነ ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል። አንዱ መምህራን የራሳቸውን ዐሻራ እንዲያሳልፉ እድሉ እየተመቻቸ እንደሆነና ሥራው ከአመራሮች እንደተጀመረም ጠቁመዋል፡፡

ግንባታው ሰፊና ሀገራዊ በመሆኑ በቀላሉ የሚሠራ አይደለም፡፡ ከፍተኛ በጀትን ይጠይቃል። ስለሆነም መምህራን ማህበሩ የተለያዩ አማራጮችን እያፈላለገ ይገኛል፡፡ እንደ ከተማ አስተዳደርም ውሳኔ ተላልፎልን በትብብር የመሥራት አማራጮችን ጨምሮ በፍጥነት ሕንጻውን ለማጠናቀቅ ይሠራልም ብለዋል። ይህ ሆስፒታል እንደ ከተማ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም ብዙ ትርጉም ያለው እንደሆነ የሚናገሩት ፕሬዚዳንቱ፤ በኢኮኖሚው ብቻ ቢታይ ከመምህራን አልፎ ማህበረሰቡን በዝቅተኛ ዋጋ እንዲታከሙ እድል የሚፈጥር ስለመሆኑ ያነሳሉ። መምህራንም ቢሆን ለሕክምና የሚያወጡትን ለሌሎች ግልጋሎቶች እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋልና ጥቅሙን ተረድቶ ለተፈጻሚነቱ ሁሉም ቢተባበር ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

እንደ መምህራን ማህበር ለመምህራን የሚደረጉ ማንኛውም ድጋፍ ከእርሱ ጀርባ ያሉትን ተማሪዎች፤ ወላጅና ቤተሰቦች እንዲሁም ሀገርን ታሳቢ ያደረገ ነውና መምህራን እየተጎዱ የሚቀጥሉበት ሁኔታ በምንም መልኩ አይፈጠርም፡፡ ለዚህም መብትና የጥቅማጥቅም ጥያቄያቸውን ለመመለስ ማህበሩ የተቻለውን ሁሉ ያደርጋልም ብለዋል፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የተራቀቀው የጥፍር ውበት

**ቤዛ እሸቱ**

ለሴት ልጅ የእጅ ጣት ውበት ነው፡፡ አለንጋ ጣት መሆንና አለ ለሴት ልጅ የእጅ ጣት ውበት ነው፡፡ አለንጋ ጣት መሆንና አለመሆን የተፈጥሮ ጉዳይ ነው፡፡ ጥፍሯን ማሳመር ግን ከተፈጥሮም ባሻገር እንክብካቤ ጊዜና ገንዘብ ይሻል፡፡ እናቶቻችን ሂና ተቀብተው እንሾሽላ ሞቀው ጣታቸው ላይ ቀለበት አድርገው ለራሳቸው ለተመልካችም ማራኪ ጣትና ጥፍር እንዲኖራቸው ያደርጉ ነበር፡፡ አሁን ግን ዘመን ተቀይሯል፡፡ ጥፍር ቀለም ተቀብቶ እፍ እያሉ መድረቅ ደረቀ አልደረቀ እያሉ መሳቀቅ እየቀረ መጥቷል፡፡ የአብዛኛው ምርጫ ሺላክ የተሰኘው የማይለቅና ለማድረቅ ማሽን የሚያስፈልገው የጥፍር ቀለም ዓይነት እየሆነ ሄዷል፡፡

አክለሪክ፣ ጄል፣ ኔል ሳሎን የሚባሉ ቃላት በዘመነኞቹ ሴቶች አፍ የሚሰሙ ቃላት ሆነዋል፡፡ አገልግሎቱ ቤት ለቤት፣ ለብቻ ጥፍር ብቻ የሚሰራባቸው ቤቶች እንዲሁም አጠቃላይ ሙሉ የውበት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቤቶች ተበራክተዋል። የመበርከታቸውን ያህልም የሚያስከፍሉት ገንዘብም የበረከተ ነው፡፡ ከእነዚህ የዘርፉ ባለሙያዎች አየር ጤና የሚገኘው ኤዳ የውበት ሳሎን ባለቤት ኤደን ታምራት አንዷ ነች፡፡ ተፈጥሮም የእሷ አያያዝም ታክሎበት ከልጅነቷ አንስቶ ከእኩዮቿ ጎልቶ የሚታይና "ጥፍርሽ ሲያምር" የምትባል ልጅ ነበረች፡፡ በዚህም የተነሳ ለጥፍር እንክብካቤ ለየት ያለ ፍቅር ነበራት፡፡ ያም ቢሆን የሕይወቷ ዘርፍ ሌላ ይመስል ነበር፡፡ በትምህርቷ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ በኮምፒዩተር ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ አላት። ከግል ኮሌጅ በቢዝነስ አስተዳደር ሁለተኛ ዲግሪ ይዛለች፡፡ የተለያዩ ሥራዎችን ብትሰራም አብዛኛውን የቅጥር ሕይወቷ በግል ትምህርት ቤት በመምህርነት አሳልፋለች፡፡

የራስ ሥራ መሥራት የሚል ሃሳብ ነበራት፡፡ ለዚህም የመረጠችው በራሷ ጥፍር ውጤታማነት ያስመሰከረችው ጥፍርን መንከባከብን ነው፡፡ ለዚህም የጥፍርና የሜካፕ ሥራ አጭር ሥልጠና ወሰደች፡፡

‹‹የጥፍርና የሜካፕ ትምህርቱን በወሰድኩበትና ሥራውን በጀመርኩበት መሃል የዓመት ከስድስት ወር ልዩነት ነበር›› የምትለው ኤደን፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችን በማየት ራሷን ከዘመኑ ሥራዎች ጋር ታስኬድ ነበር፡፡ ያም ቢሆን ወደሥራው እንደገባችም ደንበኞችን በክፍያ ከመሥራት ይልቅ በመንገድ የሚያልፉ ሰዎችን በነፃ በመሥራት እጅ መፍታቷን ታስታውሳለች፡፡ በነፃ ተሰርተው



ሥራዋን የወደዱት ሰዎች በገንዘብ የሚሰሩ ሰዎችን እያመጡላት፣ እነሱም ቀጣይ ደንበኛ እየሆኑ ቀጥለዋል፡፡ በማህበራዊ ሚዲያዎች የሥራዋን ውጤት በተከታታይ መልቀቋን ተከትሎ አሁን እሷን ብለው ከሩቅ የሚመጡ ደንበኞች አፍርታለች፡፡

በጥፍርና በሜካፕ ሥራዋ እሷን መርጠው የሚሄዱት ደንበኞቿ ለጥፍርና ለሜካፕ ብቻ ከምንመጣ ለምን የውበት ሳሎን አትከፍቺም የሚል ጥያቄ በረከተ፡፡ አሁን አየር ጤና በሚገኘው ኤዳ የውበት ሳሎን እሷ ጥፍርና ሜካፕ ስትሰራ የጸጉር ሥራውን በባለሙያዎች ታሰራለች፡፡ ሰዎች ሥራው የሚያረካ ካገኙ አንድ ቦታ መሥራት ምርጫቸው ነው ትላለች፡፡ በአንድ ቦታ የልባቸው ካልደረሰ ድካም ቢሆንም የተለያየ ቦታ ሄደው እንደሚሰሩ ምስክር ነች፡፡

እሷ ጋር ጥፍር የሚሰሩት አብዛኞቹ ከተፈጥሮ ይልቅ በዘመኑ ቴክኖሎጂ ማጌጥ ምርጫቸው ነው፡፡ የተፈጥሮ ጥፍራቸውን እንክብካቤ ማግኘትና ጥፍር ቀለም የሚቀቡ ደንበኞቿ አነስተኛ ናቸው ትላለች፡፡ የሚለጠፉ፣ ጄል የሚሞሉና አክለሪክ የሚሰሩ ይበዛሉ፡፡ ልጥፍ በፋብሪካ የተዘጋጀ አርቴፊሻል ጥፍርን ለዛ በተዘጋጀ ማጣበቂያ ማጣበቅና የመረጡትን የጥፍር ቀለም መቀባት፣ ቁመቱን እንዲሁም ቅርጹን ማስተካከልን ያካትታል። ልጥፍ ጥፍር ቀለል ያለ ሲሆን እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ ይቆያል፡፡ በርካታ ሰዎች የእጃቸውን ጥፍር የሚለጠፉ ቢሆንም በርካቶች የእግር ጥፍራቸውን መለጠፍ ምርጫቸው ነው፡፡ የእግር ጥፍር ላይ ሲሆን ረዥም ጊዜ እንደሚቆይ ትናገራለች፡፡

እሷ ጋር የሚመጡት ደንበኞች በብዛት ምርጫቸው ጄል መሆኑን የምትናገረው ባለሙያዋ፤ ጄል ሲሆን አርቴፊሻል ጥፍር እንደሚጣበቅና ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀ ኬሚካል አርቴፊሻል ጥፍሩ ላይ ይደረጋል፡፡ ኬሚካሉን ለማድረቅ የተሞላው ጥፍር ዩቪ ላይት የሚባል መሳሪያ ውስጥ ገብቶ ይደርቃል፡፡ እንደሰውየው ፍላጎትና ሁኔታ ቢለያይም በብዛት ከሁለት እስከ ሦስት ወር ይቆያል፡፡ ይህን ያህል እንዲቆይ በመሃል መሞላት (ሪፊል) መደረግ አለበት ትላለች፡፡ ለዚህም የተሠራው ሰው ውሃ ውስጥ በጣም የሚቆይ ከሆነ ጥፍሩ የማደግ እድል ስላለው ቶሎ ሪፊል ይፈልጋል፡፡ ቢፈጥን በ20 ቀን ቢዘገይ በአንድ ወር የድጋሚ ሙሌቱ ይደረጋል ትላለች፡፡

አክለሪክና ጄል ሁለቱም ተጨማሪ ጥፍር የሚያስፈልጋቸውና የሚሞሉ በመሆናቸው አንድ ይመሳሰላሉ ትላለች፡፡ ሆኖም አክለሪክ ዱቄት (ፓውደር) በመሆኑ ያለምንም መሳሪያ ይደርቃል፤ ጄል ግን ለመድረቅ ዩቪ ላይት የሚሰኝ ማሽን ያስፈልገዋል፡፡ የመቆየትና የውበት ሁኔታቸው ተመሳሳይ ቢሆንም አክለሪክ ሲሰራ ከባድ ሽታ ስላለው በአብዛኛው ደንበኞቿ ዘንድ ጄል ተመራጭ ነው፡፡ የሚሰሩት ጥፍር ቁመት ቅርጽ እንዲሁም የሚቀቡት የጥፍር ቀለም ከለርና ዲዛይን ከዚህ ቀደም ከሰራችው መሃል መርጠው ወይም ደንበኛው ይዞት የመጣውን ምርጫ ትሠራለች፡፡ በእንቺ ምርጫ ሥሪን የሚሉም ሆነ ከማህበራዊ ሚዲያ ያዩትን ሥራ እንደምርጫቸው እንደምትሠራ ትገልጻለች፡፡

የጾም ወቅት ላይ ሥራው የሚቀዘቅዝበት ሲሆን ሠርግ የሚበዛበት ጥር ደግሞ በርካታ ሰው ይሠራል ትላለች፡፡ ዓርብ፣ ቅዳሜና እሁድ ደንበኛ ጥፍር የሚሰራ ሰው ቁጥሩ ይጨምራል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## «ደረሰኝ ባይቀበሉም ሒሳብ ይክፈሉ»

**ዋስልኝ አየለ**

ከሳምንት በፊት ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ወሰን አካባቢ የሚገኝ አንድ አነስተኛ ሆቴል ገባን፡፡ ገብተንም ምግብ አዘዝን፡፡ ማወራረጃውንም ተጠቀምን፡፡ በመጨረሻም አስተናጋጇን ሒሳብ ሥሪልን አልናት፡፡ ደረሰኝ ስንጠብቅ መጥታ ሒሳቡን ነገረችን፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነት ነገር ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል፡፡

የነገረችን ሒሳብ ከተጠቀምነውም ሆነ ከቤቱ አንፃር የተጋነነ ሆነብን፡፡ ብሩን ከሰጠናት በኋላ፤ ‹‹ይሄኛው ይህን ያህል ቢሆን፣ ይሄኛው ይህን ያህል...›› እያልን የተጠቀምነውን ደመርነው፡፡ ሌላ ቦታ ከምናውቀው አንፃርም ሆነ ከወቅቱ ተለዋዋጭ የዋጋ ሁኔታ ጋር አገናዝበን ስንደምረው ከከፈልነው ሒሳብ ጋር ተራራቀ፤ ቤቱም ያን ያህል የተለየ የሚባል አይደለም፡፡ እኔ አንዴ ሆኗል ብዬ ዝም ብልም ጓደኛዬ ግን አላስቻለውምና አስተናገጇን ድጋሚ ጠራት፡፡ ‹‹ደረሰኝ አምጭልን›› አላት፡፡ ችግሩ ግን ቤቱ ደረሰኝ አልነበረውም። ‹‹ደረሰኝ የለንም›› ስትል እኔም ነገሩ አላማረኝምና ‹‹እንዴት ይህን የሚያክል ቤት ያለ ደረሰኝ ይሠራል?›› አልኳት። ምክንያቱ እሷም አልገባትም መሰለኝ ባለቤቱን ልጥራላችሁ አለችን። እኛም ቢመጣም ምናልባት ተበላሽቶብን ነው ወይም አዲስ ስለሆንን ነው ከማለት ያለፈ ምንም አይለንም ብለን በቸልተኝነት ተይው ብለናት ወጣን፡፡

አሁን ግን ሳስበው ግዴለሽ መሆናችን ልክ አልነበረም፡፡ በእንዲህ ዓይነት ግዴለሽነት ነው ሕገ ወጥ አሠራሮች የሚለመዱት፡፡ በተናጠልም ሆነ እንደ ሀገር ጉዳታቸው እየተለመደ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ የእንዲህ ዓይነት ትንንሽ ግዴለሽነቶች ናቸው ትልልቅ ጥፋቶችን የሚፈጥሩት፡፡

አንድ ገጠመኝ ልጨምርና ወደ ጥቅል ትዝብቴ ልሂድ፡፡ በአንድ ወቅት መገናኛ አንድ ካፌ ውስጥ ሦስት ሆነን የሚበላ ነገር አዝዘን በላን፡፡ ሒሳቡን የከፈለው አንደኛው ልጅ ብቻ ስለሆነ ሁለታችን ሒሳቡንም መልሱንም ልብ አላልነውም፡፡ የሰጣት የሁለት የሁለት መቶ ብር ኖቶች ነበር፡፡ በሒሳቡ መሠረት መልሱ ውስጥ መቶ ብር መኖር ነበረበት፡፡ ልጁ ከመቶ ብር በታች ያሉ የ10 ብር ኖቶችን ከመልስና ደረሰኝ ማምጫ ማህደሩ ውስጥ ካወጣ በኋላ መልሱ ልክ አለመሆኑ ገባው፡፡ ወዲያውኑ ጠርቶ 100 ብር አስጨመራት፡፡

ሊያጋጥም የሚችል ስህተት ነው በሚል ልብ አላልነውም ነበር፤ በኋላ ግን አብረውን የነበሩት ሁሉ እንዲህ አይነት ማጭበርበሮች የተለመዱ መሆናቸውን ገጠመኞቻቸውን እያነሱ ነገሩን፡፡ ሰዎች መልስ ሲያነሱ ልብ አይሉትም በሚል ሆን ብለው ያደርጋሉ ይባላል። የሁለት መቶ ብር ኖት ደግሞ ለዚህ መዘናጋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

በርግጥ ስህተት አያጋጥምም አይባልም፤ ሁላችንም እንሳሳታለን፡፡ ዳሩ ግን ሆን ተብለው የሚደረጉ ካሉ ግን በቤቱ ውስጥ እምነት ማሳጣት ነው፡፡ ለአስተናጋጆችም ቢሆን ጉርሻ ጭምር የሚያሳጣ ይሆናል፡፡ መልሱን ልብ ሳይሉ ያነሱታል በሚል መጓጓት ውስጥ ከገቡ ችግር ነው፤ ምክንያቱም ልብ የሚል ደንበኛ ከተገኘ ተሳስታ ነው ብሎ በየዋህነት ከሚያስበው ይልቅ ሆን ብለው ለማጭበርበር ነው ብሎ የሚጠራጠረው ይበዛል፡፡ ስለዚህ እዚህ ላይም ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

ወደ ደረሰኞች እንሂድ፡፡ በብዙ የአገልግሎት (ሰርቪስ) ቤቶች ‹‹ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሒሳብ አይክፈሉ›› የሚሉ ማሳሰቢያዎችን በየግድግዳው ላይ እናያለን፡፡ ሆኖም ግን ደረሰኝ ባይቀበሉም ሒሳብ ይክፈሉ እየሆነ ነው፡፡

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(3) መሠረት የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ ደረሰኝ እንዲሰጥ ይገደዳል። ካለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ የወንጀል ቅጣቱ በሕግ ተደንግጓል፡፡

የግብር ከፋይነት ደረጃቸው ባይታወቅም፣ መቼም እነዚህ ካፌዎችና ሆቴሎች ግብር ከፋይ አይሆኑም ተብሎ አይገመትም፡፡ በርግጥ የግብር ከፋይነት ደረጃ የሚተመነው በቤቱ ዓይነትና ስም ሳይሆን በካፒታላቸው መጠን እንደሆነ ባለሙያዎች ይነገራሉ፡፡ ምናልባት ደረሰኝ የማይሰጡ ቤቶች የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ ከሆኑ ደረሰኝ ለመቁረጥ ላይገደዱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ ዳሩ ግን የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ ከሆነና ደረሰኝ ከሌለው ግን በዚያ ልክ የተጋነነ ዋጋ ሊያስከፍል አይገባውም፡፡ ስለዚህ ገና ለገና ደረሰኝ የለንም ብለው ያጭበረብሩበታል ማለት ነው፡፡

ተገልጋዩ የሚያየው የቤቱን ሁኔታ ብቻ ሊሆን ይችላል፤ በርግጥ የሚሰጡት አገልግሎትም ጥሩ ሊሆን ይችላል፡፡ ዳሩ ግን ከግብር ከፋዮች በላይ ማስከፈል ደግሞ ዝርፊያ ነው ማለት ነው፡፡ ዋናው ችግር ግን ምናልባትም ደረሰኝ መቁረጥ የሚገባቸው ሆነው ማንም አስቦት ሊጠይቀን የሚችል የለም በሚል እያጭበረበሩበት ነው፡፡

አንድ የንግድ ቤት ፈቃድ አውጥቶ ሥራ ሲጀምር መሟላት ያለባቸውን ሕጋዊ ሁኔታዎች አሟልቶ ነው፡፡ ምናልባት ግዴለሽ ያልሆነ ሰው ቢያጋጥማቸው ሊቀጡ ወይም ንግድ ቤታቸው ሊዘጋባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ለትንሽ ማጭበርበር ብለው ትልቅ ኪሳራ ውስጥ ሊገቡ አይገባም፡፡ ምናልባትም ሆን ብለው ለማጭበርበርም ላይሆን ይችላል፤ በግዴለሽነት ከሆነም፣ በተራ ግዴለሽነት ኪሳራ ላይ መውደቅ የለባቸውም፡፡

ግዴለሽነት ብቻ ነው ብሎ ለመገመት ግን ይከብዳል። ምክንያቱም የሚያስከፍሉት ሒሳብ ደግሞ የተጋነነ ነው። የተጋነነ ሒሳብ ክፈል የተባለ ሰው ደግሞ ደረሰኝ መጠየቁ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም አስተማማኙ ደረሰኙ ነው፡፡ ገና ለገና የኑሮ ውድነቱ በየዕለቱ ይጨምራል ተብሎ መሆን ካለበት በላይ መሆን የለበትም፡፡ ደረሰኝ አለመቁረጣቸው ሳያንስ የተጋነነ ዋጋ ማስከፈላቸው እንደ ግለሰብም፣ እንደ ሀገርም እያከሰሩ ነው፡፡

ብዙዎቻችን ሕጋዊ መብቶችን የመጠየቅ ችግር አለብን፡፡ ይሉኝታ እንዳለ ሆኖ በብዛት ግን ግዴለሽነት ነው፡፡ ከአገልግሎት ሰጪው ቤት ግድግዳ ላይ ‹‹ደረሰኝ ሳይቀበሉ አይክፈሉ›› የሚል ጽሑፍ እናያለን፤ ችግሩ ግን ጽሑፉን እንደማንኛውም የግድግዳ ላይ ጥቅስ እንጂ እንደ ሕጋዊ ግዴታ እያየነው አይደለም፡፡

ለመሆኑ ግን አንድ ትልቅ ቤት ያለ ደረሰኝ የተጋነነ ሒሳብ የሚጠይቀው በምን ድፍረት ይሆን? ተገልጋዩ ዜጋ መብቱን የማይጠይቅ ግዴለሽ ነው በሚል መተማመን ይሆን ወይስ ቢጠይቅም የመጣው ይምጣ በሚል ይሆን?

ከዚሁ ከደረሰኝ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ካፌዎች የምታዘበው ነገር ደግሞ፤ ደረሰኝ በእጅ ጽሑፍ የሚሰሩ አሉ፡፡ ምክንያታቸው መብራት ጠፍቶ ነው የሚል ነው። ችግሩ ግን ለማጭበርበር ስለሚያመች በተደጋጋሚ የሚጠቀሙትም እንዳሉ ነው ቅሬታ የሚነሳው፡፡ ለማጭበርበር ብለው የሚያደርጉ ካሉ፤ አንዱ ደፋር የጠየቃቸው ዕለት ጉድ ይፈላል፡፡ ለምሳሌ፤ በዚያ አካባቢ መብራት አለመጥፋቱን ካወቀና መብራት ሳይጠፋ በእጅ ጽሑፍ ከቆረጡ የምርም እያጭበረበሩ ነው ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሕጋዊ ግዴታዎችን የመጠየቅ ልምድ ይኑረን፡፡ ይህን የምለው ራሴን ጭምር ተወቃሽ በማድረግ ነው፡፡ እንደ ሀገር ያለውን ሁኔታ የሚቀይረው የግለሰቦች ጥረት ነውና ሕግ አክባሪም አስከባሪም እንሁን!

# እየተዘነጋ የመጣው የቅድመ ጋብቻ ኤች አይ ቪ ምርመራ

**ነፃነት አለሙ**


በኢትዮጵያ ከ600ሺህ በላይ ሰዎች ከኤች አይቪ ቫይረስ ጋር እንደሚኖሩ ከጤና ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያሳያል። በዓመት ከሰባት ሺህ በላይ ሰዎች ለቫይረሱ ተጋላጭ እንደሚሆኑ የጠቆመው መረጃው፤ በየዓመቱ ከ10 ሺህ በላይ ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸውን እንደሚያጡ ይገልጻል።

በጤና ሚኒስቴር የኤችአይቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ያደታ እንደሚሉት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለይም ከእናት ወደ ልጅ የሚተላለፍ የኤች አይቪ ቫይረስን ለመከላከል አራት ዋና ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠው እየሠራ ነው።

የመጀመሪያው ማንኛዋም እድሜዋ ከ15-49 የሆነች ሴት ስለ ኤች አይቪ ግንዛቤ እንዲኖራት ማስቻል ፣ ሁለተኛው ከእርግዝና በፊት ራሳቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ፣ ሶስተኛ ቫይረሱ በደሟ ውስጥ ከተገኘ ወደ ፅንሱ እንዳይተላለፍ ክትትል እንድታደርግ ማስቻል እና አራተኛው ከወለዱ በኋላ ለእናትና ለልጁ ምን አይነት ጥንቃቄ መደረግ አለበት የሚል መሆኑን ያስረዳሉ።

ከጋብቻ በፊት መመርመር ዋነኛና ትልቁ ተግባር መሆኑን የጠቆሙት ሥራ አስፈጻሚው፤ አብዛኞቹ እናቶች ኤች አይቪ ፖዘቲቭ መሆናቸውን የሚያውቁት በመጀመሪያ እርግዝና ላይ መሆኑን ይገልጻሉ። የዚህ ዋና ምክንያትም ከጋብቻ በፊት ተመርምሮ አለመጋባት ሊሆን እንደሚችል ይገመታል ብለዋል።

ይህንንም ለመከላከል ወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ላይ በግንዛቤ ማስጨበጫና በባህሪ ለውጥ ዙሪያ



መስራት እንደሚገባ አመልክተው፤ ኤች አይቪ እንደጠፋ የሚቆጥሩና ከጋብቻ በፊት መመርመር ግዴታ እንዳልሆነ የሚገልጹ መኖራቸውን ጠቁመዋል። በበሽታው ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ቲክቶክን ጨምሮ የተለያዩ የሚዲያ አማራጮችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ። ከዛ ባሻገር የሃይማኖት ተቋማት ድጋፍም እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ህብረት ምክትል ፕሬዚዳንት የሆኑት መጋቢ ሰንበቱ ባሼ በበኩላቸው፤ በእኛ ስር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ተጋቢዎች ለመጋባት ፍቃድ ሲጠይቁ እስከ ስድስት ወር ድረስ እናቆያቸዋለን ይላሉ። በዛ ወቅትም ኤች አይቪ ተመርምረው ውጤታቸውን እንዲያመጡ እንደሚደረግ ጠቁመው፤ አሁን ላይ ሌሎች አጀንዳዎች እየበዙ ከመምጣታቸው አኳያ እንደ ከዚህ በፊቱ በጉዳዩ ላይ ንቃት የመፍጠሩ ነገር ግን በእኛም በኩል ተቀዛቅዟል ሲሉ ያስረዳሉ።

አዲስ ተጋቢዎችን በተመለከተ ግን ጥንቃቄ እናደርጋለን የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በስድስት ወር ቆይታቸው ከሚሰጣቸው ትምህርቶች አንዱ ስለኤች አይቪ መሆኑን ይጠቁማሉ። የእምነቱ አስተምህሮቱም ግንኙነት የሚፈቀደው በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንደሆነም አንስተዋል። ሌሎች ተቋማትም የእኛን ተሞክሮ ቢወስዱና ቢሰሩበት የስርጭት መጠኑን መቀነስና አስቀድሞ መከላከል ያስችላል ብለዋል።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ቀርቷል በሚያስብል ሁኔታ ወደ ቤተክርስቲያኗ ለመጋባት የሚመጡ ሰዎች የምርመራ ወረቀት ስለመጠየቃቸው ሰምተው እንደማያውቁ የገለጹት ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መምህር የሆኑት መጋቢ ሀዲስ እሸቱ አለማየሁ ናቸው።

እንደእርሳቸው ገለጻ፤ እንደከዚህ ቀደሙ በቤተክርስቲያኗ አስገዳጅ ተብሎ የኤች አይቪ የምርመራ ወረቀት እየተጠየቀ አይደለም። ይህም እንደሀገር ለበሽታው ከተሰጠው ትኩረት ጋር ተያያዥ እንደሆነ ይገልጻሉ። እንደ ድሮ በሬድዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በተለያዩ ክበባት በኤች አይ ቪ ዙሪያ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች እንደሌሉ የገለጹት መምህሩ፤ አሁን ላይ ያለው ሁኔታ ግን በሽታው ጨርሶ ጠፍቷል የተባለ ያህል መሆኑን ያስረዳሉ።

የማህበረሰብ ጤናን በተመለከተ የሚካሄዱ ዘመቻዎች የአንድ ሰሞን ብቻ የማድረጉ ነገር ተገቢ እንዳልሆነም በመግለጽ፤ መንግሥትም ሆነ ሃይማኖት ሕዝብ ሲኖር ነውና የሚኖሩት ኤች አይ ቪ ላይ ብቻ ሳይሆን አሁን እየተስፋፉ የመጡትን ተላላፊ ያልሆኑ እንደልብ፣ ካንሰር፣ ስኳርና ደምግፊት የመሳሰሉ በሽታዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ ሊሠራ እንደሚገባ አመልክተዋል።

## በኦሮሚያ ክልል መንግሥት እና ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በበኩላቸው፤ የሰላም ጥሪውን ተቀብለው ለመጡት ምስጋና አቅርበዋል።

ከጦረኞች በላይ ጦርነትን የሚያባብሱት ስለጦርነት የማያውቁ ናቸው ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ እኔ ካለኝ ልምድ አንፃር ጦርነት ጎጂ በመሆኑ የሰላምን መንገድ መርጣችሁ በመምጣታችሁ ልትመሰገኑ ይገባል ብለዋል። ይህ አይነቱ ተግባር በሌሎች አካባቢዎችም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

በመርሀ-ግብሩ ላይ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ጋዜሊ አባ ሲመል የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን ኮምሽነር ሌተናል ጄነራል ዲሪባ መኮንን የኢትዮጵያ መከላከያ መረጃ አመራሮች አባገዳዎች ሀደ ሲንቄዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና ታዋቂ አትሌቶች ተገኝተዋል።

# ዓለም አቀፍ

## ኤድስ እንደያዘው ከ32 ዓመታት በፊት ለዓለም የተናገረው አሜሪካዊው

ኤድስ ከሞት በላይ በሚፈራበት ዘመን ስሙ ሲጠራ በርካቶች በፍርሃት የሚሸበሩበትን ሁኔታ ለማስወገድ ከ36 ዓመታት በፊት ነው የዓለም የኤድስ ቀን መታሰብ የጀመረው። በወቅቱ አሜሪካዊው የሜዳ ቴኒስ ሻምፒዮና አርተር አሽ ተመርምሮ በሽታው እንዳለበት የተረዳበት ወቅት ነበር።

ከበሽታው ጋር ተያይዞ በነበረው አድልዎ እና መገለል በተለይም ኤድስ ከተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ጋር በመያያዙ፤ አርተር ለዓመታት ያህል የጤናውን ሁኔታ ምሥጢራዊ አድርጎት ነበር። ስለበሽታው ከተናገረ በኋላ በፊር ቀዳጅነት ግንዛቤ ለመፍጠር የተለያየ ጥረቶችን አድርጎ ነበር።

ከ32 ዓመታት በፊት ሚያዝያ ወር ላይ አርተር የተለያዩ መገናኛ ብዙኃን በተገኙበት አዳራሽ ገባ።ሁሉም ካሜራቸውን ደግነው ነበር።በዚህች ወቅት በአሜሪካ ዴቪስ ካፕ ለተሰኘው ሽልማት የተመረጠ የመጀመሪያው ጥቁር መሆን ስለነበረው ሚና፣ ወይም በታላላቆቹ ዌምበልደን፣ ዩኤስ ኦፕን እና አውስትራሊያ ኦፕን የሜዳ ቴኒስ ውድድሮች ፈር ቀዳጅ ጥቁር አሸናፊ ስለመሆኑ አልነበረም።

በወንዶች የነጠላ ሻምፒዮና ውድድር የመጀመሪያ ጥቁር ሆኖ በታሪክ የተመዘገበው አርተር በልብ ህመም ምክንያት በርካታ ቀዶ ህክምናዎች አድርጎ ነበር።እነዚህን ቀዶ ህክምናዎች ተከትሎ በ36 ዓመቱ ነበር ከስፖርቱ ራሱን ያገለለው።ይህም በዚህ አዳራሽ ከመገኘቱ ከ12 ዓመታት በፊት ነው።

አርተር በግርማ ሞገሱ፣ በርቱዕ አንደበቱ፣ በጉብዝናው እና በስፖርታዊ ጨዋነቱ በውድድር ላይ ብቻ ሳይሆን ከሜዳ ውጪም ተወዳጅ ነበር።ኤድስ ገዳይ መሆኑ እና በበርካቶች ዘንድ እንደ ሞት መልዕክተኛ በሚታይበት በዚያ ወቅት ሚዲያው ስለአርተር ጤና ጭምጭምታዎችን ሰምቷል።

የአርተር የልጅነት ባልንጀራ እና የዩኤስኤ ቱደይ ጋዜጠኛ ዳግ ስሚዝ ስለሰማው ጭምጭምታ ፊት ለፊት አፋጠጠው።አርተር በማግስቱ ከአውሮፓውያኑ 1988 ጀምሮ እሱ እና የቅርብ ወዳጆቹ ብቻ የሚያውቁትን ምሥጢር በይፋ ተናገረው።“በኤድስ ተይዣለሁ አለ” የያዘው በአውሮፓውያኑ 1983 በቀዶ ህክምና ወቅት በተለገሰው በቫይረሱ በተበከለ ደም እንደሆነም ያለውን



በስጋት ገለጸ።

አሜሪካ በልገሳ የሚሰጥ ደምን መመርመር የጀመረችው አርተር ከተያዘ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በአውሮፓውያኑ 1985 ነው።አርተር የተናገረው አስደንጋጭ ዜና ሀገሪቱን ሁሉ ከፍተኛ መሸበር ውስጥ የከተተ ነበር።ከህመሙ በተጨማሪ ሌላ አነጋጋሪ የሆነው ጉዳይ የግል መረጃን እና የሰዎችን መረጃ የማጋለጥ የፕሬስ ሥነ ምግባርን የተከተለ ነው የሚለው ነበር።

አርተር በዚህ ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ “እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንድገባ መደረጌ በጣም የሚያበሳጭ ነው። የግል መረጃዬን ለመጠበቅ እንድዋሽ ልደረግ ነበር” ሲልም ተቸ። “የእኔን የጤና ሁኔታ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አስገዳጅ የሆነ የህክምናም ሆነ አካላዊ ሁኔታ አልነበረም” ሲልም ተናገረ።

አርተር በኋላ ላይ ‘ደይስ ኦፍ ግሬስ’ በሚል ርዕስ ባሳተመው ማስታወሻ ‘ግላዊ መብቱ መከበር ነበረበት በሚል ከ700 በላይ ደብዳቤዎች ለዩኤስኤ ቱደይ መድረሱን አስፍሯል። በተጨማሪ 95 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ጋዜጣው የአርተርን ህመም ያጋለጠበትን አቋም አጥብቀው ተቃውመዋል።

አንዳንድ የኤድስ ተሟጋቾች አርተር ህመሙን መደበቁን ፤ እንደእሱ ያሉ ያገቡ ባለትዳሮች በኤችአይቪ ኤድስ ላይ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ እመርታ ማሳየት ይችሉ ነበር ሲሉ ተችተውታል።አርተር ስለበሽታው ይፋ ከማድረጉ ከአምስት ወራት በፊት የኤችአይቪ ቫይረስ በደሙ እንዳለ ያሳወቀው ታዋቂው አሜሪካዊው የቅርጫት ኳስ ተጫዋች ማጂክ ጆንሰንን ከተነሳበት ጥያቄዎች መከላከል ይችል እንደነበር ያሰፈረ ደብዳቤ ለጋዜጣው ተልኳል።


በጋዜጣዊው መግለጫ ላይ በኤችአይቪ መያዙን በተረዳበት ወቅት ለምን በይፋ እንዳልተናገረ በተጠየቀበት ወቅት ስጋቱን ገልጾ ነበር።“መልሱ ቀላል ነው። በዚያ ጊዜ በኤችአይቪ መያዜን ይፋ ማድረግ በጣም ከባድ ነበር። ከባለቤቴ ጋር የቤተሰባችንን ግላዊ መብት በዘላቂነት ይጎዳዋል በሚል በምሥጢር ለመያዝ ወሰንን” ብሏል።

በዚሁ መግለጫ ስለበሽታው ለአምስት ዓመት ልጁ ካማራ እንባ ስለተናነቀው መናገር አልቻለም። ባለቤቱ ጂኒ እሱን ወክላ አነበበች።የዩኤስ ኤ ቱደይ የስፖርት አርታኢ ጂን ፖሊሲንሲኪ የአርተርን በኤችአይቪ መያዝ ይፋ ያደረገው ጽሁፍ እንዲታተም ያሳለፈው ውሳኔ የሚፀፀትበት ጉዳይ አይደለም።

“አርተር በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከተከሰቱ ታላላቅ አትሌቶች አንዱ ነው። በዓለም ዘንድ ስመ ጥር ነው። በወቅቱ ለሞት በሚዳርግ ህመም መያዙ ታወቀ። ለ25 ዓመታት ጋዜጣን እንደ መምራቴ ይህ ዜና ነው” ሲል ለቢቢሲ በቅርቡ ተናግሯል።የፀፀት ስሜት ተሰምቶት እንደሆነ ሲጠየቅም “በጭራሽ አይሰማኝም። የፀፀት ስሜት ተሰማኝ ማለት በወቅቱ ውሳኔዬ የተሳሳተ ነበር ማለት ነው። ስህተት አልነበረም” ብሏል።

አርተር ኤድስ እንዳለበት ለዓለም ከገለጸ ከሶስት ወራት በኋላ በለንደን ተገኝቶ ነበር።በዚያን ወቅት ‘ፋይቲንግ ባክ’ ለተሰኘው የቢቢሲ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቃለ መጠይቅ በተደረገለት ወቅት “የሆነ ወቅት ላይ ለሕዝብ ይፋ እንደማደርግ አውቅ ነበር። ቫይረሱ በተገኘብኝ ወቅት ጤናዬ ጥሩ ስለነበር በዚህ ሳልረበሽ ሥራዬን ለመቀጠል ወሰንኩ። በዚያን ጊዜ አደባባይ መውጣት ማለት የሚያስከትለው መዘዝ ቀላል አልነበረም” ሲል ምላሽ ሰጥቷል። አርተር የግላዊ መረጃን የመጠበቅ መብትን በተመለከተ በተደጋጋሚ ጋዜጠኞችን ሞግቷል።

# ስፖርት



# መቻል በአፍሪካ ሚሊታር ስፖርት ውድድር በአትሌቲክስ ሁለተኛ ሆኖ አጠናቀቀ

**አስማየሁ ግዛው**

የአፍሪካ ጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ስፖርታዊ ፌስቲቫል ከኅዳር 11/2017 ዓ.ም ጀምሮ በናይጄሪያ አስተናጋጅነት ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ በአትሌቲክስ ስፖርት ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈው መቻል ስፖርት ክለብ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ አጠናቋል።

ሁለተኛው የአፍሪካ ጦር ኃይሎች ስፖርት ፌስቲቫል በናይጄሪያ ዋና ከተማ አቡጃ ከመላው አፍሪካ በተወጣጡ የሚሊታሪ ስፖርተኞች መካከል ለአስር ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ ሲጠናቀቅ መቻል ስፖርት ክለብ በአትሌቲክስ ተሳትፎ አመርቂ ውጤትን በማስመዝገብ ውድድሩን አጠናቋል። ውድድሩ አንድ ጊዜ ተካሂዶ ለረጅም ዓመታት መቋረጥ በኋላ ዘንድሮ ለሁለተኛ ጊዜ በተካሄደበት ወቅት መቻል በመጀመሪያው የውድድሩ ተሳትፎ ጥሩ ውጤትን በማስመዝገብ በአትሌቲክስ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ማጠናቀቅ ችሏል። በዚህም በአትሌቲክስ ውድድር ተሳትፎን ማድረግ የቻለው መቻል ስፖርት ክለብ 17 ሜዳሊያዎችን ሰብስቦ በድል አጠናቋል።

ኢትዮጵያን በውድድር መድረኩ ወክሎ ለመጀመሪያ ጊዜ የተካፈለው መቻል ጠንካራ አትሌቶችን አሰልፎ ደማቅ የሆነ ውጤትን በማስመዝገብ በአትሌቲክስ ከኬንያ ቀጥሎ በሁለተኝነት ሲያጠናቅቅ፤ በአጠቃላይ ደግሞ አምስተኛ ደረጃን ይዞ ውድድሩን ፈጽሟል። በተለያዩ የሩጫና ሜዳ ተግባራት ላይ የተሳተፉ የክለቡ አትሌቶች ከፍተኛ ትንቅንቅን በማድረግ በመጀመሪያው ተሳትፎ ተፎካካሪ እንዲሆንና ደረጃ ሰንጠረዥ ውስጥ ገብቶ እንዲያጠናቅቅም አድርገዋል። በዚህም በተለያዩ የአትሌቲክስ ውድድሮች 7 የወርቅ፣ 8 የብርና 2 የነሐስ ሜዳሊያን በመሰብሰብ በጥቅሉ 17 ሜዳሊያዎችን ይዞ በመጀመሪያው ተሳትፎው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ፈጽሟል።

በአምስት ሺ እና ሦስት ሺ ሜትር መሰናክል መቻልን ወክላ የተወዳደረችው ሃምሳ አለቃ ወርቅውሃ ጌታቸው ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ኢትዮጵያን ማስጠራት እንዲሁም ክለቧ በውጤት ታጅቦ እንዲያጠናቅቅ ትልቅ ተጋድሎን አድርጋለች። አትሌቷ ከፍተኛ ፉክክርን ባስተናገዱት እነዚህ ሁለት ውድድሮች ልምድና ችሎታዋን ተጠቅማ ክለቧ ሁለት ሜዳሊያዎች እንዲያገኝ ትልቅ የሆነ ሚናን ተጫውታለች። ሃምሳ አለቃ ትዕግስት ግርማ በ1500 ሜትር ሶስተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ለክለቧ ስታስመዘግብ፤በወንዶች አሎሎ ውርወራ ምክትል አስር አለቃ ነነዌ ጌንዳቦ አራተኛውን፣ በሴቶች ሱሉስ ዝላይ ምክትል አስር አለቃ በፀሎት አለማየሁ አምስተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ አስመዝግባለች። ስድስተኛው የወርቅ ሜዳሊያ የተመዘገበበት ሌላው የሜዳ ተግባር ሲሆን፤ በሴቶች ጦር ውርወራ አስር አለቃ ብዙነሽ ታደሰ አሸናፊ ሆናለች። በተጨማሪም በውድድሩ መጠናቀቂያ ቀን 4 በ400 ሜትር ዱላ ቅብብል ውድድር ሰባተኛው የወርቅ ሜዳሊያ መመዝገብ ችሏል።

በወንዶች ጦር ውርወራ ምክትል አስር አለቃ ኡታጌ ኡጉላ ሁለተኛ በመውጣት የብር ሜዳሊያን አስገኝቷል። በሴቶች አሎሎ ውርወራ ምክትል አስር አለቃ ዙርጋ ኡስማን ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ለክለቧ የብር ሜዳሊያ ማስመዝገብ ችላለች። በወንዶች 1500 ሜትር ሃምሳ አለቃ ደጀኔ ተሾመ ሁለተኛ በመውጣት የብር ሜዳሊያ አስገኝቷል። አስር አለቃ በዓለም ላይ ሹመት እንዲሁ ሁለተኛ ወጥቶ የብር ሜዳሊያ ካስመዘገቡት አትሌቶች መካከል ነው።

በሴቶች 400 ሜትር ፍጻሜ ምክትል አስር አለቃ ራሔል ተስፋዬ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ በማጠናቀቅ የነሐስ ሜዳሊያ አስመዝግባለች። በጉጉት በተጠበቀው የ500 ሜትር ወንዶች ውድድር ምክትል አስር አለቃ መሰረት ሙሉ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ የነሐስ ሜዳሊያን ማስመዝገብ ችሏል።

በዘንድሮው የጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ጨዋታዎች አልጄሪያ፣ ካሜሩን፣ ግብፅ፣ ኢትዮጵያ፣ ጋና፣ ኬንያ፣ ሞሮኮ፣ ደቡብ አፍሪካ እና አስተናጋጇ ናይጄሪያ ከተሳታፊ ሀገራት መካከል ይጠቀሳሉ።

የውድድሩ ዓላማ በአህጉሪቱ ለሚገኙ የሚሊታሪ ስፖርተኞች የውድድር ዕድል መፍጠር ሲሆን፤ አትሌቲክስን ጨምሮ በቅርጫት ኳስ፣ ቦክስ፣ እግር ኳስ፣ ጎልፍ፣ እጅ ኳስ፣ ጁዶ፣ ውሃ ዋና፣ ቴኳንዶ፣ መረብ ኳስና በሌሎችም ስፖርቶች መከናወን ችለዋል።

የአፍሪካ ጦር ኃይሎች (ሚሊታሪ) ስፖርታዊ ውድድር በርካታ ስፖርቶችን በማካተት ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በተወጣጡ ሚሊታሪ አትሌቶች መካከል የሚካሄድ ውድድር ነው። የመጀመሪያው የአፍሪካ ሚሊታሪ ስፖርት ውድድር እአአ በ2002 ከዓለም አቀፉ ሚሊታሪ ካውንስልና ከአፍሪካ ሚሊታሪ ስፖርት ተቋም ጋር በትብብር በኬንያ ናይሮቢ አስተናጋጅነት ተካሂዶ ናይጄሪያ የውድድሩ አሸናፊ ነበረች።

በናይጄሪያ አስተናጋጅነት በተካሄደው ስፖርት ፌስቲቫል ኢትዮጵያን ጨምሮ በአጠቃላይ ከ25 የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡ 1 ሺ በላይ ስፖርተኞች በ19 የስፖርት ዓይነቶች ተሳታፊ ሆነዋል። የስፖርት ፌስቲቫሉ ሲጠናቀቅ አስተናጋጇ ናይጄሪያ የውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊ ሆና አጠናቃለች። 3ኛው የመላው አፍሪካ የጦር ኃይሎች የስፖርት ፌስቲቫልና ውድድር በኢትዮጵያ ወይም ኢኳቶሪያል ጊኒ ይካሄዳል ተብሏል።

በውድድሩ የመከላከያ ሠራዊት የስነ ልቦና ግንባታ ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጀኔራል እንዳልካቸው ወልደኪዳንና የመቻል ስፖርት ክለብ ዳይሬክተር ብርጋዲየር ጀኔራል ኑሩ ሙዘይን የታደሙ ሲሆን፤ በናይጄሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ለቡድኑ አባላት የእራት ግብዣ አድርገዋል።


# Beeksisa Caalbaasii

Waajjirri Maallaqaa Go/Sh/Bahaa bara bajataa 2017tti seektaroota baajanni isaanii isa jalatti bulaniif gaaraajota Magaalaa Adaamaa keessatti argaman sadarkaan isaanii (salphaa sadarkaa 3ffaa) ta'an caalbaasii ifaatiin gatii harkaa dorgomsiisee tajaajija suphaa konkolaataa argachuu barbaada. Haaluma kanaan dorgomtoonni ulaagaa armaan gadii guutuu danda'an akka dorgoman affeera.

1. Dorgomtnonni Heyyama Hojii daldalaa haaromfame kan qabanii fi ragaa kan dhiyeessan ta'uu qabu.
2. Dorgomtoonni Galmaa'aa TIN kan ta'anii fi kaffalaa taaksii dabalata qabeenyaa /VAT/ galmaa'aa kan ta'an kanaafiis gagaa dhiyeessuu qabu.
3. Dorgomtoonni kanfalaa gibira bara hojii 2016 ta'uu isaanii waraqaa qulqullinaa Abbaa Taayitaa Galiiwwanii irraa kennamu dhiyeessuu qabu.
4. Dorgomtoonni waraqaa ragaa sadarkaa gahumsaa Garaajii kan ibsu Ejensii Geejjibaa irraa kan kennameef dhiyeessuu qabu.
5. Dorgomtoonni Weeb-saayitii Galmee dhiyeessummaa Biiroo Maallaqaa Federaalaa irratti kan galmaa'anii fi yeroo ammaa weeb-saayitii irratti galma'aa ta'uu isaanii kan ibsu ragaa koppii isaa qabsiisuu kan danda'an ykn Biiroo Maallaqaa Naannooleetti Galmee dhiyeessitootaa irratti kan galmaa'an ta'ee, kanaafis ragaa dhiyeeffachuu qabu.
6. Dorgomtoonni sanada caalbaasii irratti Sirreeffama, Haqamaa fi Laaqama taasisuu hin qaban. Kana malees, gatii kennan irratti haqamaa yoo taasisan kufaa ta'uu beekuu qabu.
7. Dorgomtoonni sadarkaa gahumsa garaajii Dhaabbata Suphaa Konkolaataa Salphaa sadarkaa 3ffaa ta'uu beekuu qabu.
8. Dorgomtoonni kamiyyuu gatii harkaa Tajaajila suphaa konkolaataa sanada caalbaasii Waajjirri Maallaqaa Go/Sh/Bahaa qopheesse irratti guutuu qabu.
9. Dorgomtoonni caalbaasicha gufachiisuuf yaalan caalbaasiin ala kan ta'an ta'ee, qajeelfama bittaa Mootummaa 02/2004 fi akkaataa labsii lakkoofsa 157/2002 tiin kan gaafataman ta'uu isaa beekuu qabu.
10. Dorgomtoonni caalbaasichi erga banameen booda sanada caalbaasii irratti jijjiirama ykn fooyya'iinsa gochuu ykn caalbaasii keessaa bahuu kan hin dandeenye ta'uu beekuu qabu.
11. Dorgoman kamiiyyuu tajaajila gatii harkaa suphaa konkolaataa gosa hojii hunda irratti gatii baqqee/ tokkoo/ dhiyeessuu qaba.
12. Dorgommiin caalbaasii kan gaggeeffamu ulaagaa dirqamaa (must met criteria) fi qajeelfama dorgomtootaa erga guutee gara faaynaansitti darbee qabxiin gatii tokkoon tokkoon ida'amee gatii ida'ama walii galaatin gatii xiqqaa kan fide mo'ataa caalbaasichaa ta'uu isaa beekuu qabu.
13. Dorgomaan kamiiyyuu dhaabbatichi /Garaajichi/ wabummaaf kan ta'u Inshuraansii seera qabeessa ta'e dhiyeeffachuu qaba.
14. Dorgomtoonni gatiin caalbaasii ji'a Sadii (3) tiif ragga'ee kan turu ta'uu isaa beekuu qabu.
15. Dorgomaan caalbaasicha dorgomee moo'ate mana hojii waliin waliigaltee waggaa tokkoof kan turu kan mallatteessu ta'ee gatiin ittin moo'ates waggaa tokkoof ragga'ee kan turu ta'uu isaa beekuu qabu.
16. Dorgomtoonni Caalbaasicha irratti moo'atan Tajaajilli Suphaa Konkolaataa irratti moo'atan Qulqullinaan yoo hojjechuu baatan irra deebi'anii baasii isaanitin kan hojjetan ta'uu beekuu qabu.
17. Dorgomtoonni caalbaasicha irratti hirmaatan konkolaattonni mootummaa kan argaman Magaalaa Adaamaa keessa waan ta'eef, caal-baasii suphaa konkolaataa kana irratti jaarmiyaan dorgomu barbaadu kamiiyyuu dhaabbanni gaaraajii isaanii Magaalaa Adaamaa keessatti kan argaman qofa ta'uu isaa fi Magaalaa Adaamaatiin ala dorgomuu kan hin dandeenye ta'uu beekuu qabu.
18. Dorgomtoonni sanada caalbaasii irra kan taa'e sirritti dubbisanii hubatanii sanada caalbaasichaa fi gatii harkaa ittiin dorgoman guutu qabu. Kana yoo ta'uu baate dogongora uummamu kaamiyyuu itti gaafatammummaa kan fudhatu dorgomaa ta'uu beekuu qaba.
19. Dorgomaan kamiiyyuu sanada caalbaasii irratti maqaa /dhaabbata/ isaa fi teessoo isaa qixa sirriin ibsee chaappaa dhaabbatichaa itti dhahuun sanada caalbaasiii hunda irrattii mallatteessee chaappaa itti dhahuun sanada caal-baasii Orijinaala fi kooppii adda addatti poostaan saamsudhaan dhiyeessuu qaba.
20. Dorgomaan kamiiyyuu caalbaasicha irratti hirmaachuuf, kabachiisa caalbaasii CPO Qar. 30,000 (kuma soddoma) qabsiisuu qaba. Haa ta'u malee, Dorgomicha kan kufan yoo ta'e, kufuun isaanii erga mirkanaa'ee CPO kabachiisa caalbaasiidhaaf qabsiisan yeruma sanitti deebi'aaf.
21. Dorgomtoonni Sanada caalbaasii ittiin dorgoman maallaqa hin deebine Qar. 500 (dhibba shan) kaffaluun beeksifni caalbaasii kun Gaazexaa Addis Zamaniin guyyaa bahe irraa eegalee guyyoota hojii 15 (kudha shan) walitti aansuudhaan sanada caalbaasi Waajjira Maallaqaa Godina Shawaa Bahaa biiroo lakkoofsa 15 tti dhiyaachuun bitachuu ni danda'u.
22. Sanadni caalbaasii beeksifni kun Gaazexaa Addis Zamaniin guyyaa bahe irraa eegalee guyyoota hojii 15 (kudha shan) walitti aansudhaan sa'aati 2:30 hanga 11:30 tti gurguramuun dorgomtoonni sanadni caalbaasii guyyaa beeksifni caalbaasichaa bahe irraa eegalee hanga guyyaa hojii guyyaa 16 ffaa (guyyaa kudha jahaffaa) hanga sa'a 6:00 tti saanduqa caalbaasichaaf qophaa'e keessa galchuun guyyuma kana sa'a 6:00 tti saamsamee sa'a 8:30 tti iddoo dorgomtoonni ykn bakka bu'oonni caalbaasicha irratti hirmaachuu barbaadan argamanitti banama.
23. Dorgomaan moo'ate caalbaasii suphaa konkolaataa fi gatii harkaa mo'achuun erga beekamee kabachiisa walii galtee %10 CPO qabsiisuu qaba.
24. Dorgomtoonni kamiyyuu sanada caalbaasii irratti ibsa, sirreeffama, yaadaafi gaaffii yoo qabaatan sanadni caalbaasii osoo hin banamin guyyaa 5 (shan) dura waajjirichaaf dhiyeessuu qabu. Kanamalees waajjirichi sanada caalbaasii irratti sirreeffama ykn yaadni fooyya'iinsaa yoo jiraate sanadni caalbaasii osoo hin banamin guyyaa 5 (shan) dura dorgomtoota kan beeksisu ta'uu qabu. Haa ta'u malee guyyaa jedhame kana booda sirreeffama taasifamu, yaadas ta'ee gaaffiin dhiyaatu fudhatama kan hin qabne ta'uu beekamuu qaba.
25. Dorgomtoonni sanada bitachuu yoo dhufan ragaa hayyama daldalaa fi ragaa gahumsa sadarkaa ogummaa isaanii ibsu dhiyeeffachuu qabu.
26. Waajjirri Maallaqaa Godina Shawaa Bahaa filannoo biraa yoo argate caalbaasicha gartokkeen ykn guutumaa guututti haquudhaaf mirgi isaa kan eegame ta'uun isaa beekamuu qaba.

**Hubachisaa;**

- Dhaabbanni dorgomu kamiiyyuu ulaagaa ittiin dorgoman guutumaa guututti qixa sirriin mirkaneeffatee hubachuu qaba. Yoo kana ta'uu baate dogongora uummamu kamiifiyyuu sirreeffamni kan hin godhamne ta'uu ibsina.
- Dorgomtoonni Gatiin dhiyyeessan VAT duraa ta'uu isaa fi VAT booda ta'uu isaa iffattii sanada caalbaasii gatiin irratii dhiyaatuu irratii ibsuu qabu.

**Teessoon:- Magaalaa Adaamaa Mana Marii Daldalaa fuuldura**

**Lakkofsa Bilbilaa +251222114336 Bilbiluun dubbisuu ni dandeessu**

**Bul/Mot/Na/Oromiyaatti Waajjira Maallaqaa Go/Shawaa Bahaa**